አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

በከተቤ መምህራን ትምህርት ክሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ተማሪዎች በተፃፉ ተራኪ ሙሁድ-አሀደች ውስጥ የዲስኩር አመልካቾች ሥርጭትና ተግባር ትንተና

ጌታቸው እንዳለማው

ሰኔ፣ 1987 ዓ.ም.

በከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ተማሪዎች በተፃፉ ተራኪ ውሁድ-አህደች ውስጥ የዲስኩር አመልካቾች ሥርጭትና ተግባር ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት

ለአማርኛ ማስተማር /TEAM/ ኤም.ኤ.ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ ጥናት

በ
ጌታቸው እንዳለማው
ሰኔ፣ 1987 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

በከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ
ተማሪዎች ተራኪ ውሁድ-አህደች
ውስጥ የዲስኩር አመልካቾች
ሥርጭትና ተግባር ትንተና

በ

ጌታቸው እንዳለማው

ሰኔ፣ 1987 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

ይሲሳማ አገሬ
አማካሪ

ፈርማ

ሶፎንያስ ሀይሉ (ዶ/ር)
ፈታኝ

ፈርማ

ኃ/ሚካኤል አሰፋ (ዶ/ር)
ፈታኝ

ፈርማ

ፈታኝ

ፈርማ

ምሥጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ስለቸኝ ደከመኝ ሰይሉ ያለሰለሰ የሙያ ድጋፍና ምክር ለሰጡኝ አማካሪዬ ለዶ/ር እሬጋ ኃይለ ሚካኤል ልባዊ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በጥናት ርዕሰ መረጣና አቅጣጫ መያዝ ከፍተኛ የሙያ ምክርና እገዛ ለእደረጉልኝ መምህሬ ለዶ/ር ባየ ይማምና የጥናቱን ውጥንና ያዘጋጀኋቸውንም ልዩ ልዩ የጽሁፍ መመሪያዎች ረቂቅ በማንበብ ጠቃሚ ምክርና ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዶ/ር ገብረመድህን ስምዖን ያለኝ አክብሮትና ምሥጋና የላቀ ነው።

መረጃ ለመሰብሰብ ለተባበረኝ ለኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል፣ በተለይም በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ከቡር ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሰውተው ተማሪዎችን በማስተባበርና ድሁፎችን በማስፃፍ ከፍተኛ ትብብር ላደረጉልኝ ለኮሌጁ መምህራን ለእቶ ጌታሁን አማረና ለእቶ አለም እሸቱ ከልብ የመነጨ ምሥጋና አቀርባለሁ። የጥናቱን የመጀመሪያ ረቂቅ በማንበብ የበኩላቸውን እገዛና ድጋፍ ላደረጉልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራን ለእቶ ሞገስ ይገዙና ለእቶ ጌትነት ትዕዛዙ ምሥጋናዬ ይድረሰቸው።

ከሁሉም በላይ ጭንቀቴ ጭንቀታቸው ሆኖ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በተግባርም በሞራልም ከጐኔ ያልተለዩኝና የረዱኝ ጒደኞቼ፣ እቶ ሰሎሞን ተሰማ፣ እቶ ፈቃደ ሥላሴ ለማ፣ እቶ ደመወዝ አድማሱ፣ እቶ ማረው አለሙ፣ እንዲሁም ስታትስቲካዊ የሆኑትን ሥራዎች በሙሉ ተሰማሚ ዘዴ በመፈለግና በመሥራት የረዳኝ ጒደኛዬ እቶ ተስፋዬ ስመላ ምንጊዜም ከልቤ ማህደር ተፅፈው ይኖራሉ፤ ያለኝም ምስጋና እጅግ! እጅግ የላቀ ነው።

የተማሪዎችን ድርሰት በማረም ለረዱኝም ለእቶ ገበየሁ እሥራቴ፣ ለእቶ ግርማ እውግቼው፣ ለእቶ ታሪኩ ፋንታዬ፣ ለእቶ ሙሉጌታ ደሰለኝ፣ ለእቶ ሥዩም ከበደ፣ ለእቶ በድሉ ዋቅጅራ፣ የተለያዩ ጽሁፎችን በመተየብ ለተባበሩኝ፣ ለወ/ት ጽለት እድነውና ለወ/ሮ ንጋት ብሩ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም እጅግ አስቸጋሪ የሆነውን የእጅ ጽሁፌን ሰለቸኝ ደከመኝ ሰትል በመኪና ለቀረጻችልኝና ለአራበችልኝ ለወ/ት አፀደ ቢረጋ ከፍያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ማ ው ጫ

ገጽ

ምስጋና i

የሠንጠረዥ ዝርዝር v

የሥዕላዊ መግለጫዎች ዝርዝር vi

አሕፅሮተ-ጥናት (Abstract) vii

ምዕራፍ አንድ፣ መግቢያ 1

1.1. የስያሜ ቃላት የአጠቃቀም ግለጫ 1

1.2. የጥናቱ ዳራ 3

1.3. የጥናቱ ዓላማ 5

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት 6

1.5. የጥናቱ ወሰን 7

1.6. ምህፃረ ቃላትና ልዩ ልዩ ምልክቶች 8

1.6.1. ምህፃረ ቃላት 8

1.6.2. ልዩ ልዩ ምልክቶች 8

ምዕራፍ ሁለት፣ ክለሳ ድርሰናት፣ 9

2.1. የጽሁፍ ቋንቋ፣ ጭብጥና ግጥምጣሜ 9

2.1.1. የጽሁፍ ቋንቋ 9

2.1.2. ጭብጥና የጭብጥ መስፈፉት 11

2.1.3. ግጥምጣሜና ግጥምጥምነት 16

2.1.4. የግጥምጣሚ አከላት 19

2.2. ዲስኩር አመልክቾች 20

2.2.1. ሰዋሰዋዊ አመለካከት 20

2.2.2. ተግበራዊ አመለካከት 24

ምዕራፍ ሦስት፣ የጥናቱ ዘዴ 30

3.1. የመረጃ ምንጭ 30

3.2. የጥናቱ መረጃ 31

3.2.1. የጽሑፍ መረጃ 31

3.2.2. የጽሁፍ መመሪያ አዘገጃጀት..... 31
3.2.3. ጽሁፎቹ የተጽፉበት ሂደት..... 32
3.2.4. የጽሁፎች አስተራረም ሂደት..... 33
3.2.4.1. ቅድመ-እርማት ክንውን..... 33
3.2.4.2. የጽሁፍ እርማት መመሪያ አዘገጃጀት..... 34
3.2.4.3. የእርማት ሂደት..... 35
3.3. የመረጃ አተናተን ስልት..... 35
3.3.1. ዓይነታዊ ዘዴ..... 35
3.3.2. መጠናዊ ዘዴ..... 36
ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ ውጤትና ትንተና፤..... 37
4.1. ሥርጭተ-ዲስኩር አመልክቾች..... 38
4.1.1. አጠቃላይ የዲስኩር አመልክቾች
ብዛትና ሥርጭት..... 38
4.1.1.1. ውሁድ-አሀድ እንድ..... 38
4.1.1.2. ውሁድ-አሀድ ሁለት..... 40
4.1.1.3. ውሁድ-አሀድ እንድና ሁለት..... 42
4.1.2. የዲስኩር አመልክቾች አገባባዊ ሥርጭት..... 45
4.1.2.1. (ነገር) ግን..... 45
4.1.2.2. (እ)ና..... 46
4.1.2.3. (ይሁን) እንጂ..... 47
4.1.2.4. ስለዚህ(ም) 47
4.1.2.5. ከዚያ(-)..... 48
4.1.2.6. ደግሞ 48
4.1.2.7. -የተነሳ 49
4.1.2.8. ወይ(ም/ስ) 50
4.2. የዲስኩር አመልክቾች ዝርዝር ዲስኩራዊ
ተግባራትና የጭብጥ መዋቅር..... 51
4.2.1. የ(ነገር) ግን" ተግባራት..... 51
4.2.2. የ(እ)ና" ተግባራት..... 60
4.2.3. የ(ይሁን) እንጂ" ተግባራት..... 72

4.2.4. የ"ስለዚህ(ም)" ተግባራት..... 77
4.2.5. የ"ከዚያ(–)" ተግባራት..... 82
4.2.6. የ"ደግሞ" ተግባራት..... 86
4.2.7. የ"–የተነሳ" ተግባራት..... 91
4.2.8. የ"ወይ(ም/ስ)" ተግባራት..... 94
ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና ጠቋሚ አስተያየት..... 99
5.1. ማጠቃለያ..... 99
5.1.1. የዲስኩር አመልካቾች ብዛትና ድግግሞሽ 100
5.1.2. የዲስኩር አመልካቾች አጠቃላይ ተግባራት 102
5.1.3. የዲስኩር አመልካቾች ተግባራት
ምድቦች አከፋፈል..... 104
5.1.4. የዲስኩር አመልካቾችና የሰዋሰው
መስተጋብር..... 105
5.1.5. ዲስኩር አመልካቾችና የጭብጥ መዋቅር. 106
5.2. ጠቋሚ አስተያየር 107
5.2.1. የዲስኩር አመልካቾችን በሚመለከት 107
5.2.2. የጽሀፈት ትምህርትን በሚመለከት 108
– ዋቢዎች.. 109
– አባሪዎች 116
– አባሪ ሀ. የዲስኩር አመልካቾች ሥርጭት 116
– አባሪ ለ. የስታትስቲካዊ ስሌቶች፤ ናሙናዎችና ውጤቶች 118
– አባሪ መ. ልዩ ልዩ መመሪያዎች 130
– አባሪ ሠ. የዲስኩር አመልካቾች አከፋፈል 137
– አባሪ ረ. የተማሪዎች ተራኪ ውሁድ–አሀዶች ናሙናዎች 140

የሠንጠረዦች ዝርዝር

ገጽ

1. በው.እ.-1፣ መከከለኛ ሥርጭት ያላቸው ዲስኩር አመልካቾች 38
2. በው.እ.-1፣ የ"ደግሞ"፣ የስለዚህና የወይ(ም/ስ) ንጽጽር 39
3. በው.እ.-1፣ የ"ግን"ና የ"(እ)ና" ንጽጽር 39
4. በው.እ.-2፣ ዝቅተኛ ሥርጭት ያለቸው ዲስኩር አመልካቾች 40
5. በው.እ.-2፣ የ"ግን"፣ የ"(እ)ና"ና የ"ከዚያ" ንጽጽር 41
6. በው.እ.-2፣ የ"ግን"ና የ"(እ)ና" ንጽጽር 41
7. የው.እ.-1 እና የው.እ.-2 የ"ከይ ስኪር" ውጤቶች ንጽጽር 42
8. የደረጃ ተቀዳድሞ (ρ) "ማትሪክስ" 43
9. የ"ከሮምበክ እልፋ" የእስተማማኝነት ግምት 44
10. የ"ግን" ሥርጭት ከተግበሩ እኪያ 60
11. የ"(እ)ና" ሥርጭት ከተግበሩ እኪያ 72
12. የ"እንጅ" ሥርጭት ከተግበሩ እኪያ 76
13. የ"ስለዚህ" ሥርጭት ከተግበሩ እኪያ 82
14. የ"ደግሞ" ሥርጭት ከተግበሩ እኪያ 90
15. ከተግበራቱ እኪያ የዲስኩር አመልካቾች ምድቦች ክፍፍል 105

የሥዕላዊ መግለጫዎች ዝርዝር

	ገጽ
1. የዲ ኔሽ (1974) የጭብጥ መዋቅር ሞዴሎች	13-14
2. የ"ግን" የመከድ ዝምድና የጭብጥ መዋቅር	53
3. የ"ግን" የንጽጽር ዝምድና የጭብጥ መዋቅር	55
4. የ"(እ)ና" የተለጣጥቆ ዝምድና የጭብጥ መዋቅር	65
5. የ"(እ)ና" የምክንያት ዝምድና የጭብጥ መዋቅር	68
6. የ"ስለዚህ" የምክንያት ዝምድና የጭብጥ መዋቅር	78
7. የ"ከዚያ" የተለጣጥቆ ዝምድና የጭብጥ መዋቅር	85
8. የ"–የተነሳ" የምክንያት ዝምድና የጭብ መዋቅር	95

አሕጽሮተ-ጥናት

(ABSTRACT)

ዲስኩር አመልካቾች በውሁድ-አሀድ አላባዎች መካከል ያለውን ዝምድና ለእንባቢው በይፋ የሚያውጁ ናቸው። የዚህ ጥናት ዓላማም በተማሪዎች ጽሑፋዊ ተራኪ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ የገቡትን ቃላዊና ሐረጋዊ ዲስኩር አመልካቾች ሥርጭትና ተግባር መተንተን ነው። ለጥናቱም የተመረጠው የከተቤ መምህራን ትምህርት ከሌጅ ሲሆን፣ መረጃ ሰጪዎቹም በከሌጁ የሚማሩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ የሁለተኛ ዓመት የዲፕሎማ ተማሪዎች በሙሉ ናቸው። እነዚህም ተማሪዎች ሁለት ሁለት ጽሁፍ እንዲጽፉ ተደርጎ ለጥናቱ መረጃ የሚሆኑ 38 ጽሑፋዊ ተራኪ ውሁድ-አሀዶች ተሰብስበዋል።

በ38ቱም ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ዲስኩር አመልካቾች 498 ጊዜ ተደጋግመው ገብተው ተገኝተዋል። ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውና በሁለቱም ውሁድ-አሀዶች ውስጥ የሚገኙት፣ (ነገር)ግን፣ (እ)ና፣ (ይሁን)እንጂ፣ ስለዚህ(ም)፣ ከዚያ(-)፣ ደግሞ፣ -የተነሰና ወይ(ም/ስ) ሆነው ተገኝተዋል። እነዚህ ስምንት ዲስኩር አመልካቾች በሁሉም ጽሁፎች ውስጥ 391 ጊዜ ተደጋግመው በገቡበት ሁኔታ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ በሰባት ባለሙያዎች ታርመዋል። በእራሚያቹም መካከል ያለውን ስምምነትና "ውስጣዊ አይለዋወጤነት" ለማረጋገጥ የ"ክሮምባክ አልፋ (r_{α})" የአስተማማኝነት ቀመር ተግበራዊ ሆኗል።

የዲስኩር አመልካቾቹ ሥርጭት የ"ካይ ስኴር" ውጤቶች ተነፃፅረው በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት (χ^2=55.52፣ P<.05) እንዳለ የተገኘው ውጤት አመልክቷል። በዲስኩር አመልካቾቹ ሥርጭት ረገድ በሁለቱ ውሁድ-አሀድ መካከልም ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል።

በውሁድ-አሀዶችም ውስጥ ያሏቸው ተግባራት፣ የማከልን፣ የምክንያትን/የሰበብን፣ የንጽጽርን፣ የልየታን፣ የማረምን፣ የተለጣጥቆንና የአማራጭን ዝምድናዎች ማመልከት ነው። እነዚህ ተግባራት በአራት ዋና ምደቦች-ማለትም፣ በልየታ (ንጽጽር፣ ልየታ፣ ማረም)፣ በአከላ (ማከል፣ አማራጭ)፣ በጊዜ-ጠቀስና (የጊዜና የደርጊት ተለጣጥቆ) በሰበባዊ (ምክንያት፣ ሰበብ) የዝምድና ምደቦች ሊመደቡ ችለዋል። እንድ ዲስኩር አመልካችም የተለያዩ ዝምድናዎችን ስለሚያመለክት በተለያዩ ምድቦች ውስጥ ተደጋግሞ ሊመደብ እንደሚችል ጥናቱ አሳይቷል።

በመጨረሻም በጥናቱ ሂደትና ውጤት ከታዩት አጠቃላይ ሁኔታዎች በመነሳት ዲስኩር አመልካቾችንና፣ የግጥምጣሜን ትምህርት በሚመለከት ጠቋሚ አስተያየቶች ቀርበዋል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የስያሜ ቃላት የአጠቃቀም ግለጫ (Definition of Operational Terms)

በዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት እንዲህ ዓይነቱ የአማርኛ ቋንቋ ጥናት በራሱ በአማርኛ ቋንቋ ሲቀርብ የመጀመሪያ ይመስላል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ቁልፍ የሆኑ ቃላትና ሐረጋት ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉመው ሲቀርቡ ከእንግዳነታቸው የተነሳ የንባቡን ከንውን ከማደናቀፋቸውም በላይ ሊተላለፍ የተፈለገውንም መልዕክት በተሟላ ሁኔታ እንዳይተላለፍ ሊያደርጉት ይችላሉ።

ስለዚህ በጥናታዊ ጽሁፉ ውስጥ በተደጋጋሚ በጥቅም ላይ የሚውሉትን የሙያና የስያሜ ቃላትና ሐረጋት ተግባራዊ ግለጫ (Definition) አስቀድሞ መግለጹም ሆነ መረዳቱ ጠቃሚ ይሆናል። በዚህ ንኡስ ክፍልም የእነዚህ ቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ግለጫ በፊደል ተራቸው ቅደም ተከተል መሠረት ቀጥሎ ቀርቧል።

ሀ. መስተፃምር (Conjunction):-በዲስኩር ውስጥ ተጠየቃዊ ዝምድናን ለማመልከት የሚያገለግል የቋንቋ አካል ነው። እንደ ሃሊዴይና ሀሰን (1976) አገላለጽ "አራት ዓይነት ተጠየቃዊ ዝምድናዎች—አካይ፤ ልየታ፤ ሰበባዊና ጊዜ-ጠቀስ—አሉ።" እነዚህን ዝምድናዎች በይፋ (Explicitly) ለማመልከት የሚገቡትን ቅጣይ ምዕላዶች፤ ቃላትና ሐረጋት በሙሉ የሚያጠቃልል ስያሜ ነው።

ለ. ውሁድ-አሀድ (Text):- በሥነልሳን፣ ማንኛውም በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ያለን ምንባብ (Passage) ያመለክታል። በሌላ አገላለጽ እንደሐረግና ዐረፍተ ነገር ሰዋሰዋዊ አካል ያልሆነ በጥቅም ላይ ያለ (Language in use) ቋንቋ አሀድ ነው። በአጭሩ መጠኑ ውሱን ያልሆነ—አጭርም ረጅምም ሊሆን የሚችል—አንድ የተዋሀድ ምሉዕ መልዕክት (Unified Whole) የሚያስተላልፍ ትርጊሜያዊ አሀድ ነው (ሃሊዴይና ሀሰን፣ 1976፤ ናታል፣ 1982)። ስለውሁድ-አሀድ የሚደረግ ጥናትም የውሁድ-አሀድ ሰዋሰው (Text Linguistics) ተብሎ ይታወቃል (ፋሰልድ፣ 1990)። በዚህ ጥናት ውሁድ-አሀድ የሚያመለክተው በጽሁፍ የሰፈረውን የተማሪዎች ጽሁፍ ይሆናል።

መ. ዐውድ (Context):- ውሁድ-አሀድ የሚነገርባቸውን የቋንቋና የገጠመኝ (Experiential) አካባቢዎች የሚያመለክት ስያሜ ነው። የቋንቋ ዐውድ (Linguistic Context) የሚያመለክተው በውሁድ-አሀዱ ውስጥ የገቡትን ቃላት፣ ዐረፍተ ንግግሮችና (Utterances)፣ ዐረፍተነገሮች አቀነጃጀት ነው። የገጠመኝ ዐውድ (Experiential Context) ደግሞ ውሁድ-አሀዱ የሚነገርበትን /የሚፃፍበትን የገሃዳዊውን ዓለም አካባቢ ያመለክታል (ብራውንና ዩል፣ 1983፤ ኑናን፣ 1993 ይመለከቷል)። በዚህ ጥናትም ውስጥ ዐውድ እንደ አገባቡና እንደሁኔታው የቋንቋም የገጠመኝምም ሊሆን ይችላል።

ሠ. ግጥምጣሜ (Cohesion):- በእንድ ዲስኩር ውስጥ በጥገኛ ሐረጎችና በዐረፍተ ነገሮች መከከል ያሉትን ልዩ ልዩ ዝምድናዎች ለማመልከት በይፋ የሚገቡ መደበኛ አያያዦች (Formal Links) ለምሳሌ:- መስተፃምር፣ ጥቆማ (Reference)፣ መተክት (Substitution)፣ ወዘተ. ናቸው (ኑናን፣ 1993)። እንደ ሃሊዴይና ሀንሰንም (1976:27) ገለፃ፣ "በቋንቋ ሥርዓት ውስጥ ያለ ውሁድ-አሀድን ከሚገነቡት አካላት (Components) እንድ ክፍል ነው።" በዚህ ጥናት ውስጥ በጥቅም ላይ የዋለውም በዚሁ ግለፄ መሠረት ነው።

ረ. ግጥምጥምነት (Coherence):- እንድ ዲስኩር እንደማይዘመዱ ዐረፍተ ነገሮች ስብስብ ሳይሆን በእንድነት እንደተያያዘ እንድ ሙሉ አካል አድርገን የምንገነዘብበትን ሁኔታ የሚገልጽ ስያሜ ነው። በሌላ አገላለጽ በውሁድ-አሀዱ ውስጥ የገቡት ዐረፍተ ነገሮች በሁሉም ረገድ ተዘምደውና ተዋህደው በእንድነት እንድ ሙሉ አሀድ መፍጠራቸውን የሚያመለክት ቃል ነው።

ሰ. ዲስኩር (Discourse):- በተገቢ ዐውድ ውስጥ እንድ ሙሉ መልዕክት ለማስተላለፍ የተነገረ ወይም የተፃፈ መስተጋብር (Interaction) ወይም የቋንቋ እፍልቆት (Language Production) ነው። በአጭር አገላለጽ "በመስተጋብራዊነት የሚቀርብ ተግባቦታዊ ሂደት ነው" (ዊደውሰን፣ 1984፤ ኑናን 1993)። በአገራችን ሁኔታ "ዲስኩር" የሚለው ቃል ተዘውትሮ በጥቅም ላይ የሚውለውም ሆነ የሚታወቀው ለንግግር (፣ "ዲስኩር"፣ "ደስከረ"፣ "ዲስኩረኛ" እንዲሉ) ብቻ ነበር። በዚህ ጥናት ውስጥ ግን በጥቅም ላይ የዋለው ከላይ በተገለጸው መሠረት ሆኖ በአብዛኛው በጽሁፍ የቀረበውን ያመለክታል። እንዳንድ ጊዜም ከውሁድ-አሀድ ጋር በተለዋዋጭነት ይገባል።

ሸ. የዲስኩር ትንተና (Discourse Analysis):- ቋንቋ በተነገረበት /በተፃፈበት ሁኔታ በውስጡ ያሉትን ተመሳሰሎዎች (Regularities) ና በህሪያት (Features) ለይቶ ለማመልከት የሚደረግ

ጥናት ነው። እንደ ዊደውሰን (1979) አገላለጽም ዐረፍተ ነገሮች ማህበራዊ ክንዋኔዎችን በመከወን ሂደት ውስጥ ለተግባቦታዊ ጠቀሜታ የዋሉበትን ሁኔታ ለማጥናት የሚደርገውን ጥረት ያመለክታል። በዚህ ጥናትም ውስጥ የተማሪዎችን ተራኪ ውሁድ-አሀድ መሠረት በማድረግ የዲስኩር አመልካቾችን አገልግሎት ለመተንተን የሚደረገውን ጥረት ያመለክታል።

ቀ. ዲስኩር አመልካቾች (Discourse Markers):- በውሁድ-አሀድ ውስጥ ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ተግባራዊ ጠቀሜታ (Functional Value) የሚያመለክቱና ፀሐፈው ምን ለማለት እንደፈለገ የሚጠቁሙ ቃላትና ሐረጋት ናቸው (ናታል፣ 1982)። እነዚህም ቃላትና ሐረጋት (ለምሳሌ:- ስለዚህ፤ ሆኖም፣ ይሁን እንጅ... የመሰሰሉት) እንዱ የግጥምጣሜ አካላት (Cohesive Devices or Cues) ወዘተ. ተብለው ይታወቃሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ የሚያመለክቱት በተማሪዎች ጽሁፎች ውስጥ የገቡትን መስተፃምራንና መስተፃምራዊ ዝምድናን የሚያመለክቱትን ቃላትና ሐረጋት ነው።

1.2. <u>የጥናቱ ዳራ</u>

በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ለመግባባት የሚፈጠረው ዲስኩር የሀሳብ ወይም የይዘት ግጥምጥምነት እንዲኖረው ያስፈልጋል። እስከአሁን ድረስ ተለይተው ከሚታወቁት "የዲስኩር ማዋቀሪያ አካላት" መከከል ዲስኩር አመልካቾች ይገኙበታል። እነዚህና ሌሎች የዲስኩር ማዋቀሪያ አካላት በተገቢ ቦታቸው ካልተኙ የተግባቦት (Communication) ችግር ይከሰታል (ታይለር፣ 1992)።

ተማሪዎች በንግግርም ሆነ በጽሁፍ የሚያፈልቁት ዲስኩር ግጥምጥምነት ያለው ይሆን ዘንድ ስለግጥምጥምነት መሠረተ ሀሳቦችና ስለመገጣጠሚያ አካላት መማራቸው አስፈላጊ ነው (ጋዲይሲ፣ 1984)። ከነዚህ የመገጣጠሚያ አካላት ውስጥ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው የዲስኩር አመልካቾች አንዱ ናቸው። ስለዚህ እነዚህን የዲስኩር አመልካቾች ለተማሪዎች በተግባር ለማለማመድና በተገቢው ሁኔታም እንዲጠቀሙበት ለማገዝ በቅድሚያ አመልካቾችን በተገቢው መንገድ በማጥናት ለይቶ በዝርዝር ማወቅ ጠቃሚ ነው።

ከዚህ አንፃር በአማርኛ ቋንቋ ዲስኩር ትንተና አኳያ የተካሄዱ ጥናቶች በበቂ ሁኔታ አሉ ለማለት አይቻልም። ያሉትም በውጭ ሰዎች የተደረጉ ከሁለት ወይም ከሦስት ያልበለጡ ሥራዎች ናቸው። ከነዚህም ጥናቶች የብሌዚ (1984) "የአማርኛ ተራኪ ዲስኩር ትንተና" እና የጋሰር (1984) "የአማርኛ '-ም' ና '-ስ'፤ ሥነ ምዕላድ፣ ጭብጥና ግሙት ዕውቀት" የተሰኙት በቅርብ የሚገኙና የሚጠቀሱ ናቸው።

የብሌዚ (1984) ጥናት በተራኪ ውሁድ-አሀዶች ላይ የተካሄደ ትንተና ይሁን እንጂ፣ ስለዲስኩር እመልከቾች ያነሰው ወይም የሰጠው ሀሳብ የለም። የጋሰርም (1984) ጥናት ምንም እንኪን በ"-ም" እና "-ስ" ቅጣይ መስተፃምራን አገበብ፣ አጠቃቀምና ተግበራት እንዲሁም ከጭብጥና ከግሙት-እውቀት አንፃር በለቸው ሚናና ዝምድና ላይ የተከሄደ ትንተና ቢሆንም ከነዚህ ቅጣዮች ውጪ ስለሌሎቹ የአማርኛ ቋንቋ ዲስኩር እመልከቾች--ስለቃለዊና ስለሐረጋዊ ዲስኩር እመልከቾች ወይም መስተፃምራን-- ያቀረበው ትንተናና የጠቆመው ሀሳብ የለም። ከነዚህ ምሁራን ጥናት ውጪ በአማርኛ ቋንቋ ዲስኩር ላይ የተደረገ ጥናት ለመኖሩ ምንም የተገኘ ማስረጃ የለም። ስለዚህ ስለዲስኩር እመልከቾች የተደረገ ጥናት አለመገኘቱ ወይም ጪርሰ አለመኖሩ በራሱ አንድ ችግር በመሆኑ ለዚህ ጥናት መነሸ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በየጊዜው በየደረጀውና በተለያዩ ቦታዎች በሚደረጉ መደበኛም ሆኑ ኢመደበኛ ትምህርታዊ ስብሰባዎች "የዘመኑ ተማሪ እይጽፍም፤ ቢጽፍም ሀሳቡን አሰክቶና አገጣጥሞ በጽሁፍ የመግለጽ ችግር አለበት" እየተባለ ተደጋግሞ ይነገራል። የዚህ ጥናት አቅራቢም በተለያዩ ቦታዎች ባሉ ሁለተኛ ደረጀ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ በማስተማር በቆየቸው አሥራ ስድስት አመታት የተገነዘበውና ያየው ይህንኑ ችግር ነው።

ለችግሩ ግን ብዙ ጊዜ እንደ መፍትሔ ተደርጉ የሚወሰደው ለተማሪዎች ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ማስተማር ነው። ይህን በተመለከተ በ1984 ና 85 ዓ.ም. በሥራ ላይ የዋሉትን የሁለተኛ ደረጀ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያዎችንና መርሐ ትምህርቶችን ለአብነት ያህል መመልከት ይበቃል። የሰዋስው ሕግጋትን ብቻ ማወቅ ደግሞ ለችግሩ መሠረታዊ መፍትሔ ሊሆን አይችልም (ጋዲይሲ (1984) ንና ከፍለ ማሪያም (1988)ን ይመለከቷል)።

በተማሪዎች ድርሰቶችም ላይ የተደረጉ የዲግሪ ማሟያ ጥናቶች የሚገልጹት በአመዘኙ የተማሪዎቹ ድርሰቶች በርካታ ስህተቶች ያሉበቸው መሆናቸውን ነው። አለማየሁ ፀጋዬ (1986:69) በቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ ከታዩት በርካታ የስህተት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ "አጣማሪዎችን በተገቢ መዋቅራዊ ቦታቸው አለመጠቀም እንደሆነ" ይጠቅሳሉ። ከዚህ በሸገር ግን ስለዲስኩር እመልከቾች(የጥናታቸውም ይዘት ስለማይፈቅድላቸው)ተግበርና አጠቃቀም ያቀረቡት እንዳችም ትንተና የለም። ለችግሩ የሰጡትም የመፍትሔ ሀሳብ ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት መፍትሔ በየደረጀው የተግበራዊ ሰዋሰው ትምህርት ማስተማር ነው።

ከላይ በተገለጸው መሠረት ችግሮቹን ለመቅረፍ ጥረት ቢደረግም አሁንም በለመወገዳቸው ለተሸለ መፍትሔ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለችግሩ መከሰት ሰበብ ይሆናሉ ተብለው ከሚገመቱት ውስጥ ደግሞ እነዚሁ ቀደም ብለን የጠቀስናቸው ዲስኩር እመልከቾች(አጣማሪዎች

ወይም መስተፃምራን) ተጠቃሾች ናቸው። ስለሆነም ከሰዋሰው ባሻገር በጽሁፋዊ ዲስኩር ውስጥ ያላቸውን አገልግሎት ማጥናትና ማስተማር ችግሩን ይቀርፈዋል የሚል እምነት አለ።

የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በሙከራ ጥናት ወቅት ለዳራዊ-ቅኝት የዚህን ጥናት መረጃ ሰጪዎች፣ እነዚህን ዲስኩር አመልካቾች (መስተፃምራን-) በሁለተኛ ደረጃም ሆነ በከሌጅ ቆይታቸው እንዴትና በየትኛው ትምህርት ሥር እንደተማሯቸው በጽሁፍ መጠይቅ አማክይነት ጠይቂቸው ነበር። በተገኘውም ምላሽ መሠረት ሁሉም ተማሪዎች እነዚህን ዲስኩር አመልካቾች— መስተፃምራን— በሰዋሰው ትምህርት ሥር እንደተማሯቸው አመልክተዋል። እነዚህ የቋንቋ አካላት ደግሞ ሙሉ በሙሉ በሰዋሰው ሊታቀፉና ሊተነተኑ(የተወሰኑት በሌላ ሰዋሰዋዊ አገልግሎታቸው ሊተነተኑ ይችላሉ-) እንደማይችሉና መታየት ወይም መጠናት ያለባቸውም በሰዋሰው ሳይሆን በዲስኩር ጥናት እንደሆነ በዬ ይማም (1987) በመጽሐፋቸው ውስጥ ይጠቅሳሉ።

ይህ ከሆነ ደግሞ እነዚህ ዲስኩር አመልካቾች በተገቢው ዘርፍ መጠናታቸው ተገቢ ይሆናል። በመሆኑም ይህ በተማሪዎች ላይ የሚታየው የጽሕፈትና የእነዚህ የቋንቋ አካላት አጠቃቀም ችግር ለዚህ ጥናት መከሄድ ሌላው መነሸ ምክንያት ነው።

በአጠቃላይ ከላይ በተገለጹት ምክንያቶችና ለዋናው ጥናት ፈር ለመቅደድ በተከሄደው የሙከራ ጥናት በተገኘው መረጃ መሠረት የአማርኛን ጽሁፋዊ ዲስኩር አመልካቾች ማጥናት ወቅታዊና አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም ይህ ጥናት በክተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ተማሪዎች ተራኪ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ከሚገኙት ቃላዊና ሐረጋዊ ዲስኩር አመልካቾች የተወሰኑትን ብቻ (ዝርዝራቸው በ (1.5) ተገልጿል) ከተግባራቸው ከአገባባቸውና ከሥርጭታቸው አኳያ ይተነትናል።

1.3. የጥናቱ ዓላማ

ከላይ በ(1.2) እንደተጠቀሰው ዲስኩር አመልካቾች ሰዋሰዋዊ አለባዎች አይደሉም። ከተግባራቸው አንፃር በጥቅሉ ሲታዩ የሰዋሰው አለባ ሰይሆኑ የትርጓሜ አካላት ናቸው። ምክንያቱም በአንድ ውሁድ-አሀድ ውስጥ የሚተለለፍን መረጃ (ሀሰብ) እንድነትና ዝምድና በይፋ የሚያመለክቱ በመሆናቸው ነው (ዝርዝሩን በ(2.1.3) ና በ(2.1.4) ይመለከቷል)። የዚህም ጥናት አነሰስ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ተራኪ ጽሁፎች ውስጥ ያሉትን ቃላዊና ሐረጋዊ ዲስኩር አመልካቾች ለይቶ በማመልከት ከገቡበት ውሁድ አሀዳዊ-ዐውድ አኳያ ያላቸውን ሥርጭትና ተግባር ለይቶ ለማወቅ ነው።

የጥናቱም ዋና ዓላማ በከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ የዲፕሎማ መርሐግብር የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በየፈርቀው ተራኪ ውሁድ-አሀደች ውስጥ በብዛት ደጋግመው የተጠቀሙባቸውን ዲስኩር አመልካቾች-መስተፃምራን-በመለየት ከገቡበት ዐውድ አኳያ ሥርጭታቸውንና አገልግሎታቸውን ማጥናትና መተንተን ነው።

ከዚህ ዐብይ ዓላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሂደት ለመመለስ ይሞክራል፤

1ኛ. በተማሪዎቹ ተራኪ ውሁድ-አሀደች ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተደጋግመው የገቡት ቃላዊና ሐረጋዊ ዲስኩር አመልካቾች የትኞቹ ናቸው? ሥርጭታቸውና አጠቃቀማቸውስ እንዴት ነው?

2ኛ. በልማዳዊ የሰዋስው መፃሕፍት ውስጥ (ዝርዝሩን በ(2.2.1) ይመለከቷል) ከተጠቀሰው "ቃላትንና ሐረጋትን፣ ዐረፍተ ነገሮችንና ዐረፍተነገሮችን... ከማያያዝ" የተለየ ምን ዓይነት ተግባር አላቸው? የተለየ ተግባርስ ካላቸው ምን ምን ናቸው?

3ኛ. በተማሪዎቹ ውሁድ-አሀደች ውስጥ ተደጋግመው በገቡት ዲስኩር አመልካቾች የተገለጹት ዲስኩራዊ ተግባራት በተወሰኑ ምድቦች ሊከተቱ ይችላሉ?

ጥናቱ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ በተማሪዎቹ ውሁድ-አሀደች ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተደጋግመው የተገኙትንና በሁለቱም ውሁድ-አሀደች ውስጥ በጋራ የሚገኙትን ዲስኩር አመልካቾች ይተነትናል። ወደፊትም በመስኩ ምን መደረግ እንደለበት የበኩሉን ጠቋሚ ሀሳብ ይሰነዝራል።

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ከሚከተሉት ሁኔታዎች አኳያ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው።

1.4.1 ለጽሁፈት ትምህርት መሻሻል በተለይም ለዲስኩር አመልካቾች አጠቃቀምና አገባብ ትምህርት የአቅሙን ጠቃሚ መረጃ ያስገኛል፤

1.4.2 የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሚያስለጥኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፤ ዕጩ መምህራንን ሲያስለጥኑ ለሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት ይዘትና አቀራረብ መደበር የበኩሉን የመረጃ ድጋፍ ይሰጣል፤

1.4.3 በሥራ ላይ ያሉት መምህራንም ቀደምት የሰዋስው መፃህፍት ስለመስተፃምራን-ዲስኩር እመልከቾች-አገልግሎት ከሰጧቸው ውሰኔዎች ባሻገር በውሁድ-አሀድ ውስጥ ስለሚኖራቸው ተግባራት ተረድተው በተግባር ለተማሪዎቻቸው እንዲያለማምዱ ጠቋሚ ሀሳብ ይሰጣል፤

1.4.4 በሌሎችም የዲስኩር ዘርፎችና ዓይነቶች ውስጥ የሚታዩትን ዲስኩር እመልከቾች ለማጥናትና ለመተንተን መምህራን እንዲነሳሱ ይገፋፋል፤ በዚህ ጥናትም ከተደረሰበት ውጤት ጋር በማነፃፀር በወጥነት የአማርኛን ዲስኩር እመልከቾች በዝርዝር ለይቶ ለማወቅ በሚደረግ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፤

1.4.5 በእጠቃላይ በዲስኩር ትንተና ረገድ ሌሎች ጥናቶች እንዲደረጉ ያበረታታል፤ ያነሳሳል፤ በሌሎች ደረጃዎችም ለሚካሄዱ ጥናቶች በመነሻነት ያገለግላል።

1.5. የጥናቱ መሰን (Delimitation)

የጥናቱ ዓላማ በተማሪዎቹ ጽሁፎች ውስጥ ተደጋግመው የገቡትን ዲስኩር እመልከቾች ተግባርና ሥርጭት መተንተን እንደሆነ ከላይ ተጠቅሷል። ስለዚህ ይህ ጥናት:-

- በውሁድ-አሀደቹ ውስጥ የተገኙትን ዲስኩር እመልከቾች በሙሉ አይተነትንም። ምክንያቱም ሁሉንም ዲስኩር እመልከቾች በአንድ ጊዜ ለማጥናት አዳጋች ከመሆኑም በላይ የጊዜ የማቴሪያልና የመሰሰሉት ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች በመኖራቸው ጥናቱ አቅሙ አልፈቀደም።

- ጥናቱ የሚመለከታቸው ቃላዊና ሐረጋዊ የሆኑትን ዲስኩር እመልከቾች ብቻ ሲሆን እነዚህም በክፍል (3.2.4.1) በተገለጸው መሠረት በድግግሞሻቸው መጠን ከፍተኛነትና በሁለቱም የተማሪዎቹ ውሁድ-አሀደቹ ውስጥ በመገኘታቸው የተመረጡት ብቻ ናቸው።

- በሌላ በኩል ጥናቱ የተነሳበት ዓላማ ቀደም ሲል የተገለጸው በመሆኑ ሌሎች የዲስኩር አላባዎችንና ዘርፎችን አይመለከትም። ከተለየ የሙያ ትውረትም አኳያ (ለምሳሌ:- ከአእምሮት (Cognitive)አእምሯዊ ምስል (Schema) ትውረት ወዘተ. እንፃር) ትንታኔ አያደርግም።

- ጥናቱ የተካሄደው ከጠቅላላ ሥነ ልሣን መሠረተ ሀሳቦች አንፃር ሲሆን በተጨማሪም ዲስኩር እመልከቾቹ ከጭብጥ ጋር ያላቸውንም ዝምድናና ግንኙነት ለመተንተን ይሞክራል።

- ጥናቱ የተማሪዎቹን ተራኪ ውሁድ-እሀደች የተጠቀመባቸው በመረጃነት እንጂ የተማሪዎቹን የድርሰት ወይም የጽሀፈት ችሎታ ለመመዘን አይደለም። ስለሆነም ጥናቱ በዚህ ረገድ የተማሪዎቹን ችሎታ አይመለከትም፤ አይተነተንምም፤ ጽሁፎቹም በባለሙያዎች የታረሙት ከዲስኩር እመልከቾቹ አገባብና አጠቃቀም ትክክለኛነት አኳያ ብቻ ነው።

1.6. <u>እህጽሮተ ቃላትና ልዩ ልዩ ምልክቶች፤</u>

1.6.1. <u>እህጽሮተ ቃላት፤</u>

-መሐ. :- መስተዋድዳዊ ሐረግ

-ስሐ. :- ስማዊ ሐረግ

-ውእ. :- ውሁድ-እሀድ

-ዓ.ም. :- ዓመተ ምህረት፤ በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ለሚጻፉት ብቻ የሚያገለግል

-ዐ.ነ. :- ዐረፍተ-ነገር

-ግሐ. :- ግሳዊ ሐረግ

-ዲ.እ. :- ዲስኩር እመልከች

-ጥ.ዐ.ነ. :-ጥገኛ ዐረፍተ-ነገር

-ጭው. :- ጭብጣዊ-ውቅር (thematic pattern)

1.6.2. <u>ልዩ ልዩ ምልክቶች</u>

/ :- ወይም፤ እማራጭ ቃል/ሐረግ

( ) :- እማራጭ ሀሳብ

(-) :- በዲስኩር እመልከቾች ለይ ቀሬ (optional) የሆነ ቃል/ሐረግ መኖሩን ያመለክታል።

[ ] :- በትንተናው ውስጥ የሚጠቃለሉ ተመሳስሎዎችን በህግ መሰል ቀመር ለማመልከት ሲፈለግ መከተሪያ ሆኖ የሚገባ

- - :- ማብራሪያን ወይም የተዘወተረን ቃል/ሐረግ ያመለክታል

- :- ጥምር ቃል መመሥረቻ

... :- የቀረ ሀሳብ መኖሩን ያመለክታል

_:- ተተኪሪውን ዲ.እ. ያመለክታል

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሰናት

በዲስኩር ትንተና ውስጥ የሚነሱት የቋንቋ ጉዳዮች በርካታ ናቸው። በጥቅሉ ሲታይ ግን የዲስኩር ትንተና የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ነው። ይህም ቋንቋ ለልዩ ልዩ ተግባራት ሲነገር /ሲጻፍ የሚያሰያቸውን ልዩ ልዩ በህርያት ማጥናት ነው (ስታስብ፤ 1983፤ ብራውንና ዩል፤ 1983፤ ፋውለር፤ 1990፤ ማክርቲ፤ 1991፤ ሃች፤ 1992፤ ኑናን፤ 1993)። ከዲስኩር ትንተና ዘርፎች አንዱ የውሁድ-አሀድ ጥናት (Text analysis) ነው። ቀደምት የውሁድ-አሀድ ጠበብት የሰዋሰውን ዘዴ በማስፋፋት ዐረፍተ ነገሮችን እንድነት እያይዘው ወደ ውሁድ-አሀድነት የሚለውጧቸውን የመገጣጠሚያ ቁርኝቶች (Cohesive Ties) አጥንተዋል (ኤንኪቪስት፤ 1985:23)። ከዚያም ወዲህ እነዚሁ የቋንቋ አካላት በልዩ ልዩ አቅጣጫ መጠናት ቀጥለዋል።

ይህም የአሁኑ ጥናት ቀደም ሲል በክፍል አንድ እንደተጠቀሰው በተማሪዎች ተራኪ ውሁድ-አሀዶች ላይ ተመሥርቶ የዲስኩር አመልካቾችን ይተነትናል። ለትንተናውም ይረዳ ዘንድ ትውረታዊና (Theoretical) ተዛማጅ የሆኑ ጽሁፎች በዚህ ክፍል ተቃኝተዋል። በመጀመሪያው ንኡስ ክፍል ስለጽሁፍ ቋንቋ፤ ስለጭብጥ (Theme) ስለግጥምጣሜና ግጥምጥምነትና ስለግጥምጣሜ አካላት በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለዲስኩር አመልካቾች እስከ አሁን ድረስ ያሉት ሰዋሰዋዊና ተግባራዊ (Functional) አመለካከቶች ተዘርዝረዋል።

2.1. የጽሁፍ ቋንቋ፤ ጭብጥና ግጥምጣሜ

2.1.1. የጽሁፍ ቋንቋ (Written Language)

የጽሁፍ ቋንቋ በውሁድ-አሀድ ውስጥ በጽሕፈት ብቻ ተቀናብሮ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል አንድ የቋንቋ ተግባራዊ ዓይነት (Functional Variety) ነው(ሃሊዴይ፤ 1985b:43)። በመሆኑም የጽሁፍ ቋንቋ አውድ ከንግግር ቋንቋ አውድ የተለየ ነው። በንግግር ወቅት "ከቋንቋው በተጨማሪ ኢልሣናዊ (Non-Linguistic) በሆኑ አካላት" ለይም እናተኩራለን። በጽሁፍ ቋንቋ ግን ለእነዚህ ሁሉ ዕድሉ የለም (ኩክ፤ 1989:93፤ ኑናን፤ 1993:10)።

ከዚህ ሌላ በንግግር ቋንቋና በጽሁፍ ቋንቋ መካከል ያለው ልዩነት "የመረጃ እምቅነት (Information Density)" ነው። አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ "ጽሁፋዊ ቋንቋ እምቅ (Dense) ንግግራዊው ደግሞ ዘርዘራ (Sparse)" ነው (ሃሊዴይ፤ 1985b: 62፤ ኑናን፤ 1993: 11)። በተጨማሪም የጽሁፍ ቋንቋ መዋቅራዊ ውስብስብነት ያላቸውን ሐረጎችና ዐረፍተ ነገሮች ይይዛል (ኑናን፤ 1993)። በሌላ

በኩልም ድሁፋዊ ቋንቋ በተነጋሪው (Addressee) ላይ ባለው ግምት ወይም ጥያቄ ከንግግር ቋንቋ ይለያል (ስዌልስ፣ 1990፤ ኑናን፣ 1993)።

ስለሆነም ፀሐፊዎች የአንባቢዎቻቸው ዳራዊ እውቀት (Background Knowledge) ያለበትን ሁኔታ ማወቅ ወይም መገመት ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም ጽሁፎቻቸውን በማንበብ በኩል አንባቢዎቻቸው ያለባቸውን ችግር መገመት መቻል ይኖርባቸዋል። በተመሣሣይ ሁኔታም "ጥሩ አንባቢዎች አጠያቂ ፀሐፍት (Interrogative Authors) በመሆናቸው" የፀሐፊው አስተሰሰብ ወይም ገለፃ ወዴት እንደሚያመራ መገመትና ማወቅ ይጠበቅባቸዋል (ዊደውሰን 1984:48፤ ስዌልስ 1990:62)።

ከላይ ከተገለጸው መረዳት እንደሚቻለው ፀሐፊው የአንባቢውን ስሜትና ፍላጐት እየተከታተለ ለማሪምና ለማስተካከል የሚችልበት ሁኔታ የለም። ስለዚህ "የአንባቢውን ፍላጐት ለማሟትና መልዕክቱን በትክክል ለማስተላለፍ ጊዜ ወስዶ ቃላት ይመርጣል፤ የፃፈውን መላልሶ ያነባል፤ አስፈላጊም ሲሆን የፃፈውን እንደገና ይለውጣል፤ ያስተካከላል" (ብራውን፣ 1978:27፤ ብራውንና ዩል፣ 1983:5)።

በእጠቃላይ ፀሐፊው፣ አንባቢው (የእሱ አንባቢ) አለው የሚለውን ዳራዊ እውቀትና ምን ዓይነት አዲስ መልዕክት ማስተላለፍ እንደለበት አስቀድሞ ማወቅና መወሰን አለበት። የጽሕፈት ተግባር "ፀሐፊው የሁለቱንም ተሳታፊዎች (Interlocutors) ሚና የሚጫወትበት ልውውጣዊ ተግባር ነው። ይህ ድርብ ሚና ነው እንግዲህ ጽሕፈትን በጣም ከባድ የሚያደርገው" (ዊደውሰን፣ 1984:48-49)።

አንባቢውም የጽሁፉን መልዕክት በአግባቡ መተርጐም (Interpret) የሚጠበቅበት ተግባር ነው። የዲስኩር አተረጓጐም (Interpretation) ዐረፍተነገሮች በጽሁፋዊው ውሁድ-አሀድ ውስጥ በገቡበት አኪኋን ለየብቻቸው በተናጠል የያዙትን ሀሳብ ማወቅ ብቻ አይደለም። ምክንያቱም ዊደውሰን እንደሚሉት "ዐረፍተ ንግግሮቹ (Utterances) የቀረቡበት የቋንቋና የሌሎች ኢቋንቋዊ አውዶች በጋራ፣ በአገልግሎት ላይ የዋለውን ቋንቋ መልዕክት ምሉዕነት ያስገኛሉ" (ዊደውሰን፣ 1979:128-129)።

ከዚህ በመነሳት የዲስኩር ተንታኙም ዋና ዓላማ በዲስኩሩ ውስጥ በሚታዩ "ተመሳሳሎዎች (Regularities)፣ ፍቺዎች (Meanings) እና ተግባሮች (Functions)" መከከል ያለውን ዝምድና ማሳየትና መተርጐም ነው (ኑናን 1993:7)። ኑናን አክለውም እንደሚገልጹት "የዲስኩር ተንታኞች፣ ውሁድ-አሀድ ገንቢ አካላትን(Text Forming Devices) ያጠናሉ። ዓላማቸውም እነዚህ የቋንቋ አላባዎች በተነገሩበት ዐውድ ውስጥ ለቋንቋው ተጠቃሚዎች እንዴት መግባባት እንደሚያስችሏቸው ማሳየት ነው።"

ሪቾጁልስም (1982:56) በበኩላቸው ከዐረፍተነገር በላይ የሆነ ዲስኩር በሚተነተንበት ወቅት የግጥምጣሜ ዕሰቤ (Concept of Cohesion) ጠቃሚ እንደሆነ ይገልፃሉ። በአጠቃላይ ጽሀፌት ተግባቦታዊ ክንዋኔ እንደመሆኑ መጠን ጽሁፋዊ ተግባቦትም በተፈጥሮው በግጥምጣሜና በግጥምጥምነት መከከል ከፍተኛ ተደጋግፎ ይጠይቃል (ሂደውሰን፣ 1979፤ 1984)።

የውሀድ-አሀደችም ጥናት፣ እንደፋሰልድ (1990) አገላለጽ፣ ዋና መለዮ ባህርያት የግጥምጣሜና የግጥምጥምነት ሀሳቦች (Notions) ናቸው። እነዚህም መለዮ ባህርያት በውሀድ-አሀደች ውስጥ ለሚኖረው የውሀደት ስሜት (Cense of Unity) እስተዋጽኦ የሚያደርጉ እመልክቾች ናቸው።

2.1.2. ጭብጥና የጭብጥ መስፋፋት (Theme and Thematic Progression)

የዲስኩር ትንተና ከመዋቅራዊነትና ከለዋጭ ሰዋሰው (Structural and Transformational Grammer) ትንታኔ በተለየ ሁኔታዊውን (Eventual)፣ አውዳዊውን (Cntextual) እና ነባራዊውን (Objective) ፍቺ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከአብይ ሐረግ (Clause) በላይ በሆኑ የቋንቋ አሀደች (Linguistic Units) ና በእነሱም ተለጣጥቆ (Sequence) ላይ ያተኩራል (ሌዝበርግ እና ሂልፈርቲ፣ 1978: 47፤ በተጨማሪ የናታልን (1982:80-81) እራት የፍቺ ዓይነቶች ከዚህ ጋር ያገናዝቧል)።

የቋንቋዎች የዐረፍተነገር ሰዋሰዋዊ መዋቅር በግተ (በለቤት ግስ፣ ተሳቢ- SVO)፣ በተግ፣ ግበተ ወዘተ. ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ እንግሊዝኛ በግተ (SVO) ቋንቋ ነው (ማካርቲ፣ 1991:51)። አማርኛ ደግሞ በተግ (SOV) ቋንቋ ነው (ጋሰር፣ 1984:51)። የየቋንቋው የዐረፍተነገር መዋቅር የተለያየ ቢሆንም እንደፀሐፈው (እንደተናጋሪው) ትኩረትና ፍላጐት ደግሞ አወቃቀሩ ሊወሰን ይችላል። በዚህ መሠረት አንዳንድ የዐረፍተነገር አላባዎች ከመደበኛ መዋቅራዊ ቦታቸው ተነስተው ወደ ዐረፍተ ነገሩ (ሐረጉ) ግንባር ወይም ፊት ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ። ይህም የዐረፍተነገር አላባዎችን ወደሐረጉ ግንባር የማምጣት ሂደት ግንበራ *(Fronting) ተብሎ ይታወቃል (ማካርቲ፣ 1991፤ ኑናን፣ 1993)።

ግንበራ የዐረፍተነገሩ የ"ስለ"ነት /Aboutness/ ጣጣ ሲሆን ይህም በፀሐፈው የቀረበው ይዘት እንዴት እንደቀረበና ትኩረቱም ምን እንደሆነ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም በሐረጉ-በዐረፍተነገሩ- ግንባር ላይ ያሉት ወይም "በሐረጉ ግራ-መጪ ረሽ (Left-most) ላይ ያሉት" አካላት ጭብጥ /Theme/ ይባላሉ (ብራውንና ዩል፣ 1983:45-46)።

---

* ግንበራ የሚለው ቃል ግንባር ከሚለው ቃል የተገኘ ነው፤ "ግንባር"፣ "ገነበረ"፣ "ግንበራ" እንዲሉ።

ጭብጥ ከሚይዘው ሥፍራ አኳያ ከዐረፍተነገሩ ሰዋስዋዊ ባለቤት ስማዊ ሐረግ (ስሐ) ጋር ሊምታታ ይችላል። በእርግጥም የዐረፍተነገሩ ባለቤት ስሐ የዐረፍተ ነገሩ ጭብጥ ሊሆን ይችላል። ይህ ግን የግድ ና/ወይም ሁልጊዜ የሚሆን እይደለም። እንደሃሊዴይ (1985) አገላለጽም ጭብጥ "የዐረፍተ ንግግሩ ወይም የዐረፍተነገሩ የመልዕክት መነሻ-መለያ-ነጥብ (Point of Departure) ነው።"

ስለዚህ የዐረፍተ ነገሩን ባለቤት ስሐ በግንባር-በመነሻ-ላይ እስከመጣ ድረስ ጭብጥ አድርጉ መውሰድ ይቻላል። ባለቤት 'ስሐ'ው ግን በዐረፍተነገሩ መነሻ ላይ ካልመጣ ጭብጥ የሚሆነው ማንኛውም በዐረፍተነገሩ ግንባር-መነሻ-ላይ የመጣው የዐረፍተነገር አካል ነው (ማክርቲ፣ 1991)። ማክርቲ አክለውም ሲያብራሩ በብዙ የዓለም ቋንቋዎች የዐረፍተነገሩ ግንባር-መጀመሪያ ቦታ- ዋናው ሀሳብ የሚጠቀስበት ቦታ ነው። ምንም እንኳ አክሰሰቱ ከቋንቋ-ቋንቋ የሚለያይ ቢሆንም ጭብጥን በመነሻ ላይ የማምጣት ልማድ ሁለንባዊ (Universal) በህርይ ነው። (ለተጨማሪ ማብራሪያ ሃሊዴይ፣ 1985a፤ ዲኔሽ፣ 1974 ይመለከቷል)።

እንዳንድ ጊዜ በዐረፍተነገር ውስጥ ከባለቤት ስሐሌላ ከእንድ በላይ የሆኑ አሳቢዎች ወደግንባር የሚመጡበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ቅደም ተከተላዊ እገባበቸውን ማጤን ተገቢ ይሆናል። በመሆኑም በቅድሚያ የሚገኘው የውሁድ-እሀዴን ቅደም ተከተላዊ አካሄድ የሚያመለክተው ውሁድ-እሀዳዊ ጭብጥ (Textual Theme) ነው። ሁለተኛው ደግሞ የፀሐፊውን አቋም ወይም አዝማሚያ የሚያመለክተው ውስጠ-ሰባዊ (Interpersonal) ጭብጥ ሲሆን ሦስተኛውና የመጨረሻው፣ የይዘቱ አካል የሆነውን ዋነኛ ርዕሰ-ነገር (Topic) የያዘው ይዘታዊ (Ideational) ጭብጥ ነው። በጭብጥ ውስጥ ሁልጊዜ የሚኖረው ግን ይዘታዊው ጭብጥ ነው። ውሁድ-እሀዳዊውና ውስጠ-ሰባዊው ጭብጦች ሊኖሩም ላይኖሩም ይችላሉ፤ የግድ አይደሉም (ለዝርዝሩ ሃሊዴይ፣ 1985a፤ ማክርቲ፣ 1991፤ ኑናን፣ 1993 ይመለከቷል)።

ከጭብጥ ሌላ በዐረፍተነገር ውስጥ የሚገኘውና ጭብጡን በዝርዝር ለመግለጽ ወይም ለማጉልመስ የሚገባው አካል-ቃል ወይም ሐረግ-አንቀጽ ወይም ሐተታ-ጭብጥ (Rheme) ነው። ይህም ስያሜ ጭብጡን ተከትሎ የሚገባው ማንኛውም የዐረፍተነገር አካል በሙሉ ተለይቶ የሚታወቅበት መጠሪያ ነው (ዲኔሽ፣ 1974:106፤ ብራውንናዩል፣ 1983:127፤ ሃሊዴይ፣ 1985a:38፤ ማክርቲ፣ 1991:55 እና ኑናን፣ 1993:46)።

የዲስኩር ጭብጦች በሁለት መንገዶች ሊያድጉ ይችላሉ። በሂንድስ (1982:310) ገለፃ መሠረት እንደኛው፣ ተከታዩ ጭብጥ የመጀመሪያው-የቀደመው-ጭብጥ እቻ ሆኖ ሲዋቀር የሚታየው ጭብጣዊ ውቅር 'ጭው' (Themetic Pattern) ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተከታዩ ጭብጥ

የመጀመሪያው ጥብጥ ንኡስ ክፍል ወይም ማብራሪያ ሆኖ ሊዋቀር የሚታየው ጥው ነው። በመሆኑም በውሁድ-አሀዱ ውስጥ የሚገኙት ዐረፍተነገሮች ተያይዘው አብረው መነገራቸው አይቀሬ ነው። ተያይዘው አብረው የመነገራቸው ምክንያት ግን ቋንቋዊ ግንኙነት ብቻ አይደለም። እንበቢው ስለዓለምም ካለው ዕውቀት ጋር የተያያዘ ነው (ኩክ፣ 1989፤ ስታብስ፣ 1983)። ስለዚህ ፀሐፊው መረጃውን ሲያዋቅር በእንበቢው ዘንድ መኖር እለበት ወይም ይኖራል የሚለው ግሙት-ዕውቀት (Assumed Knowledge) መኖሩ አስፈላጊ ነው (ኑናን፣ 1993)።

የጥብጥ መዋቅር (Thematic Structure) እንደ ፀሐፊው ትኩረትና ግለሚ ምርጫ በተለያየ መዋቅር ሊዋቀር እንደሚችል ቀደም ሲል ተገልጿል። በተያያዘ ውሁድ-አሀድ ውስጥ በሚገኙ ዐረፍተነገሮች ውስጥ የሚታየው የጥብጥ አደረጃጀት ጥብጥ (=ጭ)+ እንቀጽ (=እ) ጭ+እ፣ ጭ+እ... እየሆነ የሚሄድ ነው። ዴኔሽ (1974) በጥናታዊ ጽሁፋቸው እንዳቀረቡት፣ በጽሁፍ (በንግግርም ቢሆን) የሚቀርቡት ዐረፍተ-ንግግሮች ጥብጦችና እንቀጾች በሦስት ዓይነት መንገድ ተዋቅረው ሊቀርቡ ይችላሉ። እነሱም ይህ የአሁኑ ጥናት ለትንታኔ የሚጠቀምባቸው ስለሆኑ ሦስቱም እማራጮች (Options) እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

1ኛ/ ጭው -1* ቀላል ጐንዮሽ ጭው፤ /Simple liniar thematic Progression/



2ኛ/ ጭው -2 ተከታታይ (ተመሣሣይ) ጭ ያለው ጭው፤

/Continuous-Constant-themes/



---

* ቁጥር የተሰጣቸው በዚህ ጥናት አጥኚ ነው። ቅደም ተከተላቸው ግን የደራሲው ነው።

** ጭ= ጭብጥ (rheme) እ= እንቀጽ(theme) ማለት ነው።

3ኛ/ ጭው -3 ምሥርት 'ጭ'ዎች ያሉት ጭው፤

/TP with derived TS/



(ምንጭ፤ ዲ ኔሽ፣ 1974:118 - 119)

(ለተጨማሪ ዝርዝር ጋሰር፣ 1984:56 እና ማክርቲ፣ 1991:55-56 ይመለከቷል)።

እዚህ ላይ ከላይ ስለቀረቡት 'ጭው'ዎች ትንሽ ማብራሪያ መስጠት ተገቢ ነው።. ጭው-1 እንደ ዲ ኔሽ አገላለጽ በጣም የተዘወተረና መሠረታዊ የሆነ የጭው ዓይነት ነው። ይህ ጭው በየዐረፍተነገሩ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ 'አ' የሚቀጥለው ዐረፍተነገር 'ጭ' እየሆነ የሚያድግበት ጭው ነው (ዲ ኔሽ፣ 1974)። እንዲህ ዓይነቱም ውቅር የአንድን ነገር ሂደት ለመግለጽ በጣም ጠቃሚ ነው። "በአማርኛም ውስጥ የተዘወተረ ውቅር ነው" (ጋሰር፣ 1984:57)።

ጭው -2 ደግሞ ውቅሩ እንደሚያመለክተው አንድ 'ጭ' ሰይለዋወጥ (አገላለጹ ግን አንድ ላይሆን ይችላል) በተከታታይ ዐረፍተነገሮች ውስጥ 'ጭ' በመሆን ከተለያዩ 'አ'ዎች ጋር ተያይዘ የሚነገርበት ውቅር ነው። በሌላ አባባል ጭብጡ አንድ ሆኖ በተለያዩ ዐረፍተነገሮች ውስጥ የተለያዩ 'አ'ዎች እየገለጹት የሚቀርብበት ውቅር ነው (ዲ ኔሽ፣ 1974)። በአማርኛም ውስጥ ለጭው -2 የሚስማማው እንደ ጋሰር (1984) አገላለጽ ዐረፍተነገሩ እንድ ገሃዳዊ በለቤት ኖሮት በውስጡ ግን የተለያዩ ነገሮችን ለማመልከት ተከታትለው የገቡ ግሶች ያለበት መዋቅር ነው።

ሦስተኛውና የመጨረሻው ጭው -3 እንድ ዐብይ ጭብጥ ("Hyper theme") አለ። ከዚህ ጭብጥ በመነሳት የተለያዩ ጭብጦች እየተመሠረቱ የየራሳቸውን 'አ'ዎች በመያዝ የሚዋቀሩበት ጭው ነው። ምሥርት 'ጭው'ዎች ግን እንዴት እንደሚለጣጠቁ የሚወሰነው የሚገለጸው ርዕሰ-ጉዳይ (Subject-matter) ይሆናል (ዲ ኔሽ፣ 1974)። እንዲህ ዓይነቱም የሀሳብ አስተዳደግ ለአካላዊ ገለፃ (Physical Description) በጣም ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ጭብጦቹ በሙሉ በመገለጽ ላይ ያለው ነገር አካላት ናቸው። ይህም ውቅር "በአማርኛ ውስጥ ተደጋግሞ የሚታይ ነው" (ጋሰር፣ 1984)።

ጋሰር (1984: 51-106) ከላይ የተመለከትናቸውን 'ጭው'ዎች ተጠቅመው ከፍቅር እስከመቃብር ና ከእርእያ መጻህፍት ሃምሳ ሃምሳ ገጸች በመረጃነት በመውሰድ የአማርኛን መስተፃምራዊ ቅጣዮች (Conjunctive Particles) '-ም' እና '-ስ'ን መዋቅራዊ ስርጭት፣ ዲስኩራዊ አገልግሎትና በአንባቢው ወይም በአድማጩ ዘንድ ያላቸውን አተረጓጐም ተንትነዋል። በጥናታቸውም መሠረት '-ም' እና '-ስ' በአተረጓጐማቸው አንባቢው ወይም አድማጩ ቀደም ብሎ ያውቀዋል ተብሎ ወደሚታሰበው ግሙት-ዕውቀት ይጠቁማሉ። በግሙት- እውቀቱና በአዲሱ መረጃ መካከልም ያለውን ዝምድና ያመለክታሉ። የሚያመለክቱትም ዝምድና '-ም' ሁልጊዜ የቀጣይነትን (Continuity) '-ስ' ደግሞ የኢቀጣይነትን (Discontinuity) ዝምድና ነው። ይህም በህርይ ሁለቱን ቅጣዮች ይለያያቸዋል (ገጽ 51፣ 63-64፣ 66-69)።

በጋሰር ትንታኔ መሠረትም እነዚሁ ቅጣዮች የሚገቡት በስሞች፣ በተውላጠስሞች፣ በቅጽሎች፣ በተውሰከ ግሶችና በአንዳንድ ጥገኛ ዐረፍተነገሮች ላይ ነው። በአገባብም የሚገኙበት ቦታ ከሌሎች ቅጣይ ምዕላዶች መጨረሻ ላይ ነው። በአገባባቸውም የዐብይ ሐረጉን (clause) ጭብጥ ያመለክታሉ። ጭብጡም አዛማጅ ሐረግ (Relative Clause) ወይም ቅጽል ያለበት ስሑ ከሆነ ቅጣዮቹ የሚገቡት በአጉላማሹ (Modifier) ላይ ነው። ጭብጡ ግን ዐብይ ሐረግ ከሆነ ቅጣዮቹ የሚገቡት በሱ ላይ ነው። አለበለዚያም በመነሻ ላይ በሚገኘው ዋና (Salient) ስሑ ላይ ይሆናል። እነዚህ ቅጣዮች በዚህ ሁኔታ የሚገቡ ቢሆኑም "በእውነተኛ መስተፃምራን (እና፣ ግን) ላይ ፈጽሞ አይገቡም" (ጋሰር 1984:61-62)። ይህ የመጨረሻው ሀሳብ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። ምክንያቱም "እናስ፣ እናም..." የመሰሰሉት አበባሎች እንዴት እንደሚታዩ የገለጹት ነገር የለም።

ጋሰር በዚሁ ጥናታቸው እያንዳንዱ ቅጣይ በተለያዩ አገባቦች የሚያስገኘውንም ትርጉም አመልክተዋል። በዚህ መሠረት ቅጣይ '-ም' በአብዛኞቹ ስሞች፣ ተውላጠ ስሞችና ቅጽሎች ላይ ሲገባ እንደየሁኔታው "(እ)ና and፣ ደግሞ also፣ በምላሹ inturn... የሚል አተረጓጐም እንደሚኖረው ተገልጿል። በመጣኞችም (Quantifiers) ላይ ሲገባም ይኽን ያህል-this many/much- የሚል አተረጓጐም አለው። በተጨማሪም በኢውስኖች (ማን፣ ምን፣ የት...) ላይ ሲገባ ደግሞ "ማንም-any body- ምንም- anything-፣ የትም- anywhere..." የሚል አተረጓጐም ይኖረዋል። በዚህ ጊዜ ግን አብሮት የሚነገረው አሉታዊ ግስ ነው (ገጽ 62፣ 69-83፣ 85-90)።

ቅጣይ '-ስ' ደግሞ በአንፃሩ በስሞች፣ በተውላጠ ስሞችና በቅጽሎች ላይ ሲገባ "ኋት አበውት" (What about) የሚል አተረጓጐም ይኖረዋል (62፣ 83-85፣ 90-96)። በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ዝርዝር አገባቦቻቸውና አተረጓጐማቸው "በጭው በቀረበው መረጃና በቅጣዮቹ '-ም' እና '-ስ' በቀረበው መረጃ መካከል መስተጋብር መኖሩን" ጋሰር አክለው ይገልፃሉ (64)።

2.1.3. ግጥምጣሜና ግጥምጥምነት

ውሁድ-አሀድ በአገልግሎት ላይ ያለ ቋንቋ አሀድ ሲሆን እንደ ዐቢይ ሐረግና እንደ ዐረፍተነገር ሰዋሰዋዊ አይደለም። በመጠኑም (Size) ሊገለጽ አይችልም (ሃሊዴይና ሐሰን፣ 1976:1)። ሃሊዴይና ሐሰን በተጨማሪ እንደገለጹት "ውሁድ-አሀድ ትርጊሜያዊ አሀድ ነው። ስለዚህ ከዐረፍተነገር ጋር ያለው ዝምድና በቅርጹ ወይም በመጠኑ ሳይሆን በመከሰቻ አካልነቱ ነው። በመሆኑም ውሁድ-አሀድ ዐረፍተነገሮችን የያዘ-የዐረፍተነገሮች ስብስብ-ሳይሆን በዐረፍተነገሮች የተከሰተ (Manifestation) ነው" (1976:2)።

በውሁድ-አሀድ ውስጥ የሚገኝ ግጥምጣሜ ከመዋቅር በሻገር በሌላም ላይ ይመሠረታል። ግጥምጣሜ የሚለው አመለካከት-በነሃሊዴይ አመለካከት መሠረት-በተለይ ኢመዋቅራዊ የውሁድ-አሀድ ዝምድናዎችን ነው የሚያመለክተው። ኤንኪቪስት (1985:23) በጥናታቸው እንደሚገልጹት የመጀመሪያው የውሁድ-አሀድ ሰዋሰው (Text Linguistics) ዐረፍተነገሮችን እያይዘው ወደ ውሁድ አሀድነት የለወጧቸውን የመገጣጠሚያ ቁርኝቶች ለመተንተን ጥረት አድርገዋል። እንዲህ ዓይነቱም ሥራ "የዐረፍተነገር-መካከል-ሰዋሰው (Inter-sentential-grammer) ተብሎ" ይታወቃል። ትውረታቸው ዐረፍተነገር-ምዕከል-ትውረት (Sentence-based theory) ነው።

በውሁድ-አሀድም ግጥምጥምነት ትንተና ቴክኒክ ውስጥ የሀሊዴይና ሀሰን (1976) ሥራ ከተግበራዊ ሥነልሳን (Applied Linguistics) እንፃር ተጠቃሽ ሥራ ነው። የእነሱም ሥራ"የግጥምጣሜ ትውረት (Cohesion Theory) በመባል ይታወቃል" (ከሬል፣ 1982 : 480)። የግጥምጣሜ አሰቤ ትርጊሜያዊ (semantical) ነው። ምክንያቱም በውሁድ-አሀዱ ውስጥ ያለውን የፍቺ ተዘምዶ ያመለክታል። ግጥምጣሜም የሚመሠረተው "አንድ የዲስኩር አካል አተረጓጐም ከሌላው አካል ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ሲመሠረት ነው" (ሃሊዴይና ሀንሰን፣ 1976:4)። ይህም አንዱ አለሌላው በበቂ ሁናቴ ሊገለጽ አለመቻሉን ያመለክታል።

ግጥምጥምነት በእንፃሩ፤ ዴይክ (1977:93) እንደሚሉት፣ የዲስኩር ትርጊሜ ባህርይ ነው። የሚመሠረተውም የአያንዳንዱ ዐረፍተነገር አተረጓጐም ከሌሎች ዐረፍተ ነገሮች አተረጓጐም ጋር ባለው ዝምድና ላይ ነው። ኩክ (1989:4) በበኩላቸው ግጥምጥምነት "የመጀመሪያው ምንባብ የሌለው ሁለተኛው ግን ያለው ትርጉማዊና ውሁዳዊ የመሆን ብቃትና ለተግባቦትም (Communication) የሚያስፈልግ ችሎታ እንደሆነ" ይገልጻሉ። ስለሆነም ግጥምጥምነት የማንኛውም የአንድ መዋቅራዊ ደረጃ ውጤት አይደለም (ስቾፍሪን፣ 1985:62)።

ውሁድ አሀዱን የገነቡት ዐረፍተነገሮች ሰዋሰዋዊ መሆን አለባቸው። ነገር ግን ሰዋሰዋዊ ዐረፍተነገሮች ብቻቸውን ለውሁድ-አሀዱ ስሜት መስጠት (sense) ማረጋገጫ አይሆኑም።

ከእያንዳንዱ "ዐረፍተነገር መዋቅርና ፍቺ በሸገር እያንዳንዱ ዐረፍተነገር እንዴት እርስ በርስ እንደሚዛመድ" ማወቅ ተገቢ ነው (ኑናን፤ 1993:2)። እንደ ኑናን አገላለጽ ውሁድ-አሀድ ገንቢ የሆኑ ቃላት/ሐረጋት ፀሐፊውን በዐረፍተነገሮች መካከል ወይም በዐረፍተነገሮች ድንበር ላይ ዝምድና ለመመሥረት የሚያስችሉ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ዐረፍተነገሮችን በውሁድ-አሀድ ውስጥ እንድነት ለማቆላለፍ የሚያግዙ ናቸው።

በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚገኙት የእነዚህ አከላት ዝርዝር ገለፃና ትንተና በሃሊዴይና ሀንሰን (1976) መጽሐፍ ውስጥ ተመልክቷል። በዚህ መጽሐፍም ትንታኔ መሠረት እምስቱ የግጥምጣሜ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፤ ጥቆማ (reference)/በብራወንና ዩል፤ 1983 እጠራር Co-reference/፤ መተካት (substitution) መግደፍ (ellipsis)/ሃሊዴይ፤ 1985a በኋለኛ ሥራቸው መግደፍንና መተካትን እንድ ለይ መድበዋቸዋል/፤ መስተፃምርና ቃላዊ ግጥምጣሜ (lexical cohesion)። የዚህ የእሁኑ ጥናት ትኩረት የሆኑት የግጥምጣሜ አከላት መስተፃምራን በሚለው ሥር የሚመደቡት ሲሆኑ ዝርዝራቸውም በክፍል (2.2.) ቀርቧል።

ከላይ ለማሰየት እንደተሞከረው ግጥምጣሜም ሆነ ግጥምጥምነት የትርጓሜ አከላት ናቸው እንጂ፤ የእንድ መዋቅር ውጤት ብቻ አይደሉም። በኑሃሊዴይና በደጋፊዎቻቸውም እምነት የግጥምጥምነት መሠረቱ ግጥምጣሜ ነው። ስለዚህ እንድ ውሁድ-አሀድ ግጥምጥምነት አለው የሚበለው የግጥምጣሜ አለባዎችን በተገቢው ቦታ ከያዘ ብቻ ነው። ይሁንና ይህ እመለከከት ደጋፊዎች እንዳሉት ሁሉ ተቃዋሚዎችም አሉት። ተቃዋሚዎቹም (ለምሳሌ:- ከራል፤ 1982፤ ናታል፤ 1982፤ ዊደውሰን፤ 1977፤ ኑናን፤ 1993) "ግጥምጣሜ ግጥምጥምነት አይደለም" ወይም "የግጥምጥምነት መሠረት አይደለም" በሚለው መሠረተሀሰብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ከራል (1982) ግጥምጣሜ ግጥምጥምነት አለመሆኑን ለማሰየት እእምሯዊ የዕውቀት ምስል (schema) ትውረት እኪያ በቀረቡት ጥናት የኑሃሊዴይን (1976) የግጥምጣሜ ትውረት ሄሰዋል። ይህንኑም የጥናታቸውን መሠረታዊ ጭብጥ በመግቢያቸው ላይ በሚከተለው እኪኋን ገልጸውታል።

> የዚህ ወረቀት ዓላማ የግጥምጣሜን ትውረት እንደ ውሁድ-አሁድ ግጥምጥምነት መለኪያ መወሰድ መሄስ ነው። ቀጥሎም ከእእምሯዊ የዕውቀት ምስል ትውረት እንፃር... ግጥምጣሜ የግጥምጥምነት መለኪያ ተደርጎ መወሰዱ እግበብ አለመሆኑን በማሰየት ንበብ በውሁድ-አሀዱና በእንበቢው መካከል ያለ መስተጋብራዊ ሂደት መሆኑን ማረጋገጥ ነው (ገጽ 479)።

ካሬል እከለው እንደገለጹት ግጥምጣሜ ምንም እንኪ የትርጊሜ ዝምድናን ቢያመለክትም እንደ ሃሊዲይና ሀሰን (1976) አመለካከት የግጥምጥምነት ጉዳይ አይደለም። ግጥምጣሜ የሚያመለክተው ውሁድ-አሀዱ እንዴት እንደትርጊሜ አካልነት እንደሚዋቀር ነው "ለማንኛውም አእምሯዊ የዕውቀት ምስል ለሌለው ሰው ውሁድ-አሁዱ ግጥምጥምነት ሊኖረው አይችልም" (ካሬል 1982:481-483)። ስለዚህ የግጥምጣሜ ትውረት ብቻውን የግጥምጥምነት መለኪያ ሊሆን አይችልም።

ኑናንም (1993:63) እንደዚሁ ግጥምጣሜ ለግጥምጥምነት ወይ በቂ አይደለም፤ ወይም ከእነአካቴው አስፈላጊ አይደለም፤ አያያዡች በሌሉበት ሁኔታ ያለውን ግጥምጥምነት እንዴት እንረዳዋለን? ሲሉ ይከራከራሉ። ኑናን ዊደውሰንን እና ኤድሞንድሰንን በመጥቀስ እነዚህ ተመራማሪዎች በተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎቻቸው ውስጥ የግጥምጣሜ አመልካቾች ሰይኖሩ ዲስኩሩ እንዴት ግጥምጥም ሊሆን እንደሚችል በተለያዩ ምሳሌዎች ማስረዳታቸውን ያስገነዝባሉ። እንዲያውም እንደ ኤድሞንድሰን አመለካከት "በትውረት ደረጃ ግጥምጥምነት የሌለው ውሁድ-አሁድ መፍጠር አስቸጋሪ እንደሆነና ዐውድ ከተፈጠረለትም ግጥምጥም ሊሆን" እንደሚችል ያስረዳሉ።

ይህም በመሆኑ ግጥምጣሜ ከውሁድ-አሀዱ ውስጥ ፍችን ፈልፍሎ ለማግኘት (to infer) ከሚረዳውና በውሁዱ-አሀድ ውስጥ የገቡት ዐረፍተ ነገሮች ተግባር ምን ምን እንደሆነ ከሚገልጸው ከግጥምጥምነት ያነሰ ደረጃ ተደርጉ ይወሰዳል (ዊደውሰን፤ 1978 ና ከንድሊን፤ 1979- በእነካሬል (1988:162) እንደተጠቀሰው)።

ጽሁፉዊውን ዲስኩር ለመረዳትና ለመተረጉም የሚነሳ ሰው ኑናን፤ (1993) እንደሚሉት ፀሐፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ፍቺና ተግባራዊ ዓላማ (functional purpose) ጉን ለጉን መገንዘብ መቻል ይገባዋል። ምክንያቱም ዐረፍተ ነገሮች የሚዘመዱት በጋራ በሚጋሩት ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በዲስኩሩ ውስጥ በሚከውኑትም ተግባር ጭምር ነው።

ስቴፈንሰን (በካሬል 1982:485 እንደተጠቀሰው) እንደሚሉት ደግሞ የግጥምጣሜ አለባቻች በውሁድ-አሀዱ ውስጥ የግጥምጥምነት ሁኔታዎች እንዳሉ ያሳያሉ እንጂ ሙሉ በሙሉ ሁኔታዎቹ የሚረጋገጡት እንበቢው በተገቢው ሁኔታ የተገለጸውን ሀሳብ በአእምሯዊ የዕውቀት ምስሉ ለይቶ ሲገነዘብ ብቻ ነው።

እዚህ ላይ የተቃውሞ አስተያየቶቹን እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል። ዐረፍተነገሮች በላዕላይ አመልካቾች (surface markers) ላይያያዙ ይችላሉ። ነገር ግን ዐረፍተነገሮቹ በተገቢ ዐውድ ውስጥ በመነገራቸው ብቻ ውሁድ-አሀዱ ግጥምጥምነት ያለው ሊሆን ይችላል። ስለሆነም

ግጥምጣሜ የግጥምጥምነት መሠረት አይደለም። ከሆነም "የግጥምጥምነት ውጤት ነው። ግጥምጥም ውሁድ-አሀድ ግጥምጣሜ ሊኖረው ይችላል፤ ግን የግድ አይደለም (ከራል፣ 19182:486)።

ግጥምጥሜ የግጥምጥምነት መሰረት አይደለም ማለት ግን ስለግጥምጣሜ ማጥናት አያስፈልግም ማለት እንደልሆነ ከራል በአጸንኦት ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ ይላሉ ከራል፤

> የግጥምጣሜ ጥናት ብቻ በራሱ ለድርሰትና ለንባብ ችግር እንደመፍትሔ መወሰድ የለበትም። ግጥምጥምነትንም ለመማር የግጥምጣሜን ትውረቶች ከሌሎች የግጥምጥምነት ዋና ዋና ትውረቶች ጋር መማር ተገቢ ነው (ገጽ 486)።

2.1.4. **የግጥምጣሜ አካላት**

(cohesive devices)

የግጥምጣሜ አካላት በላዕላይ ደረጃ ጥሩም አልጥሩም ግጥምጥምነት አለ የሚያሰኘው ውሁድ-አሀዱ በተገቢው ዐውድ ውስጥ በመነገሩና በሌሎችም ሁኔታዎች መሟላት መሆኑ ከላይ ተገልጿል። ስለሆነም የግጥምጥጣሜ አካላት ግጥምጥምነቱን ከመፍጠር ይልቅ በውሁድ-አሀዱ ልዩ ልዩ አካላት መከከል ያለውን ዝምድና ይፋ የሚያደርጉ ናቸው። በተጨማሪም ለእንባቢው ያለውን ተዛምዶ የሚያመለክቱና የንባቡን ክንውን የበለጠ የሚያመቻቹ (facilitators) ናቸው (ስታብስ፣ 1983፤ ናታል፣ 1982፤ ዊደውሰን፣ 1979ና 1984፤ ኑናን፣ 1993)።

ለእንባቢ የንባብ ችግሮች መበራከት ምክንያት ይሆናሉ ተብለው የተለዩት በህርያት እንደኛ ዕሳቤ ሁለተኛ መድብለቃላትና የዐረፍተነገር መዋቅር ሦስተኛ፣ የግጥምጣሜ አካላት፣ አራተኛ የዲስኩር አመልካቾች ናቸው (ናታል፣ 1982:82-83)። ስለሆነም የግጥምጣሜ ጥናት ውሁድ-አሀድን ከዘፈቀደ የዐረፍነገሮች ስብስብ የሚለዩትን በህርያት ለማወቅና ለማስተማር እስከለመ ድረስ ጠቃሚ ኢትም እግበብነትም አለው (ዊደውሰን፣ 1979)።

በዚህ እንፃር ሃሊዴይና ሀሰን (1976) ያዩዋቸው የግጥምጣሜ አመልካቾች በዐረፍተነገሮች መከከል የሚገኙትን ብቻ ነው። ናታል (1982) ግን በዐረፍተነገሮችም ውስጥ የሚገኙትን የዲስኩር አመልካቾች በጥናታቸው ውስጥ አስገብተዋቸዋል። በመሆኑም ዐረፍተነገሮች የተዋቀሩበት ሂደት በእንባቢው የሀሳብ ተዋረዳዊ ሂደት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ስለዚህ ጥሩ ፀሐፊ መልዕክቱን ለማስተላለፍ ዐረፍተነገሮቹን ሲያዋቅር "በቀዳሚውና በተከታዩ -በእዲሱ-ሀሳብ መከከል ያለው የሀሳብ ተያያዥነት ግልጽ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል"።

ለዚህም ግልጽነት ከሚረዱት አካላት መከከል ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዲስኩር አመልካቾች ይገኙበቸዋል። ከዚህ አኳያ ከሮምቤ (1985:5) ዊንተርን (1977) በመጥቀስ ሁሉም

ቋንቋዎች በዲስኩር አሀዶች (discouse units) መካከል ያለውን ትርጊሜያዊ ዝምድና በይፋ ለመግለጽ የሚረዱ በርካታ ቃላትና አባባሎች (expressions) እንዳሏቸው ያብራራሉ። እነዚህ ቃላትና አባባሎች ለአውዳዊው ፍቺ መከሰቻ የሆኑትንና በአሀዶቹም መካከል ያሉትን ዝምድናዎች በግልጽ ያመለክታሉ።

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙትን እነዚሁኑ ቃላትና አባባሎች ከሮምቤ እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

> ..."እልዘ"፣ "ከንሲድ"፣ "..."ከንሽርስሊ"፣ ..."ኔሽር ዘሌስ"፣ "ሶ"፣ "ዜር ፎር"፣ ወዘተ. የመሰሰሉት ቃላትና አባባሎች ካላቸው የዲስኩር ጠቀሜታ (discourse value) ጠቋሚነት አንፃር ለትርጊሜ በጣም ጠቃሚ ናቸው (1985:5)።

በእጠቃላይ እነዚህ ቃላትና አባባሎች በውሁድ-አሀድ ውስጥ ያለውን ዝምድና በይፋ በማመልከት ረገድ ጠቃሚ ጠቋሚ (useful signals) ናቸው። በርግጥ ቃላቱና አባባሎቹ-ናታል (1982) እንደገለጹት-በራሳቸው፣ ለፀረፍተነገሮቹ ትክክለኛ ፍቺ (signification) ጊዜ-ጠቀስ (temporal) ከሆኑት በቀር ምንም አያበረክቱም። ሆኖም አንባቢው ትክክለኛውን ፍቺ እንዲመሠርት ሊረዱት ይችላሉ።

የእነዚህም ቃላትና አባባሎች በጥቅሉ የዲስኩር አመልካቾች ዝርዝር ገለፃ ከሰዋስዋውያንና ከተግባራውያን አመለካከቶች አንፃር በሚቀጥለው ክፍል (2.2.) ቀርቧል።

2.2. የዲስኩር አመልካቾች

በክፍል አንድ እንደተጠቀሰው በዚህ ጥናት የሚተኮርባቸው የዲስኩር አመልካቾች መስተፃምራዊ ዝምድናን (Conjunctive relationship) የሚያመለክቱት ቃላዊና ሐረጋዊ መስተፃምራን ብቻ ናቸው። መስተፃምራን በሰዋሰው ሊቃውንትም ሆነ በዲስኩር ውሁድ-አሀድ ተንታኞች (ስለመስተፃምር ያላቸው አመለካከት በእርግጥ ከሰዋሰዋውያን ይለያል) ዘንድ በተለያየ መልክ ተደጋግመው ይነሰሉ። በዚሁ መሠረት ለጥናቱ እከሄድ ይረዳ ዘንድ ስለመስተፃምራን የተሰጡትና ያሉት ሰዋሰዋዊና ተግባራዊ አመለካከቶች ቀጥሎ ይቀርባሉ።

2.2.1. ሰዋሰዋዊ አመለካከት /Grammatical View/

በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ሰዋሰው የጽሁፍ ቋንቋ ሰዋሰው፣ ቋንቋውም የሰዋሰው ውጤት ተደርጉ ይወሰድ ነበር (ሃሊዴይ፣ 1985a: Xviii)። በነበረውም ሰዋሰው መሠረት በቋንቋ ውስጥ የሚገኙት አከላት በስምንት የንግግር ክፍሎች (Parts of Speech) ተመድበው ይዘረዘሩ ነበር። ከነዚህም ስምንት የንግግር ክፍሎች ደግሞ አንዱ መስተፃምር ነው (ዲይክ፣ 1977:53)። በተጨማሪ ዲይክ

መስተፃምር የተፈጥሯዊ ቋንቋ አያያዦች (Natural Language Connectives) ከሚባሉት የቋንቋ ክፍሎች ሥር የሚመደብ ሆኖ አማራጭ፣ አነፃፃሪ፣ አኪኋኝ፣ ምክንያታዊ ወዘተ. በሚባሉ ንኡሰን ክፍሎች እንደሚከፈል ይገልፃሉ።

በአማርኛ ቋንቋም ጥንታዊና መዋቅራዊ ሰዋሰው (Traditional and Structural Grammer) የተንፀባረቀው ዕውነታ ይኸው ነው። በቀደምት ሊቃውንት የሰዋስው መፃሕፍት ውስጥ እንደተገለጸው መስተፃምር ከሰምንቱ የንግግር ክፍሎች አንዱ ነው። ተግባሩም "ቃላትንና ዐረፍተነገሮችን ሊያያዙ ከሚገባቸው ነገሮች ጋር ማያያዝ ነው" (መርስኤ ሀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ 1948 ዓ.ም: 145፤ ተክለማሪያም ፋንታዬ፣ 1957 ዓ.ም.: 74፤ ይትባረክ ወልደ ሚካኤል፣ 1966 ዓ.ም.: 106)። ኃይሉ ፋሲልም (1966) በበኩላቸው ከመዋቅራዊ ሰዋስው እመለከከት አኳያ የመስተፃምር ተግባር "ሰዋሰዋዊ እኩልነት ያላቸውን አበሮች (constituents) ማያያዝና ግሰን ከማሠር በማገድ ከሌላ ዐረፍተነገር ተጠግቶ እንዲነገር ማድረግ" እንደሆነ ይገልፃሉ (ገጽ 176)።

ከላይ የጠቀስናቸው የሰዋስው ሊቃውንት በየመጽሐፎቻቸው እንደገለጹት፣ መስተፃምር በሁለት ትላልቅ ክፍሎችና በልዩ ልዩ ንኡሰን ክፍሎች ይከፈላል። ዋና ክፍሎቹም ወደረኛ መስተፃምርና ጥገኛ መስተፃምር ናቸው። ወደረኛ መስተፃምር ሰዋሰዋዊ እኩልነት ያላቸውን ቃላትና ዐረፍተነገሮች (እንደ ኃይሉ ፋሲል አገላለጽ አበሮችን) የሚያያይዝ ሲሆን ጥገኛ መስተፃምር ደግሞ በግስ ላይ እየተጫነ (እየገባ) እንደያሰር በማድረግ ከሌላ ዐረፍተ ነገር ላይ ተጠግቶ እንዲነገር የሚያደርግ ነው (ጥገኛ መስተፃምራን የዚህ ጥናት ትኩረት በለመሆናቸው በዝርዝር እንመለከታቸውም)።

ወደረኛ መስተፃምር በዐረፍተነገር ውስጥ ሰዋሰዋዊ እኩልነት ያላቸውን ነገሮች እንደሚያያይዝ ከላይ ተጠቅሷል። ይህ የመስተፃምር ክፍል ከላይ በተጠቀሱት የሰዋስው ሊቃውንት ሥራዎች ውስጥ በተመሣሣይ ሁኔታ በሚከተለው አኳኋን በአራት ንኡሰን ክፍሎች ተመድቦ ይገኛል።

ሀ. እጫፋሪና/ወይም አደጋሚ (ና፣ ም፣ ስ፣ በዚያውም ላይ...)

ለ. አማራጭ (ወይ፣ ወይም፣ ወይስ ...)

መ. አሰብ ሰጪ (ስለዚህ፣ ታዲያ፣ እንዲህ ከሆነ...)

ሠ. አፍራሽ (ግን፣ ነገር ግን፣ ይሁን እንጂ...)

የሆነ ሆኖ ወደረኛ መስተፃምር በነዚህ ንኡሰን ክፍሎች ሊከፋፈል መቻሉ የተገለጸና ለእያንዳንዱም ንኡስ ክፍል የተለያዩ ምሣሌዎች የተሰጡት ቢሆንም ለምን በዚህ አኳኋን ሊከፋፈል እንደቻለ በእንዳቸውም ሥራ ውስጥ የተገለጸ ነገር የለም። የምሣሌዎቹም አቀራረብ ለዚህ መሠረታዊ ጉዳይ የሚሰጠው እንዳችም ዋቢ አልታየም። ስለግለሜዎቹና ስለምሣሌዎቹ አቀራረብ አብነት ይሆነን ዘንድ ከይትባረክ ወልደሚካኤል መጽሐፍ (1966 ዓ.ም. ገጽ 107) በአጫጭሩ መጥቀስ ይቻላል።

(የሌሎቹም ሊቃውንት-ኃይሉን ሰይጠምር-ምሣሌዎች ተመሣሣይ በመሆናቸው እቀራረበቸውን በዚሁ መልክ ይረዷል)።

ሀ) እጫፋሪና እደጋሚ:-በሀሰብ የሚመሣሰሉ ነገሮችን ያያይዛል።

ምሳሌ:- 1)እበበና አለሙ በሩጫ ተወዳደሩ።

2)እበበች እንቅርት አለባት፤ በዚያም ላይ ጆሮ ደግፍ ይዟታል።

ለ) አማራጭ:- አንድ ነገር ከሌላው መመረጡን ያመለክታል።

ምሳሌ:- 1)ነገ ወይም ተነገወዲያ እመለሰለሁ።

2) ወይ ነግድ ወይ እረስ።

መ) አፍራሽ:- በፊት የተነገረውን ሀሰብ የሚቃወም መስተፃምር ነው።

ምሳሌ:- 1) ትምህርት ይገበኛል፤ ነገር ግን ጥናት አልወድም።

2) አባቴ ይወደኛል፤ ይሁን እንጂ ሰጠፉ ይቀጣኛል።

ሠ) አሰብ ሰጪ:- አስቀድሞ ለተነገረው ማስረጃ ለመስጠት ወይም ተርጉሞ ለማስረዳት የሚጨመር መስተፃምር ነው።

ምሳሌ:- 1) በፈተና እንደኛ የሆነ ሁሉ ሽልማት ያገኛል፤ እንዲህ ከሆነማ ሁላችንም ጠንክረን እናጥና።

2) ገበያው ሁሉ ተነስቷል፤ እንግዲያማ እንመለስ።

በነዚህ ሊቃውንት ግለጌዎችና ከፍፍሎች ለይ በመመሥረት ግለጌዎቹ ምን ያህል የመስተፃምራኑን (በእኛ አጠራር የዲስኩር እመልከቾቹን) ተግባር በትክክል ገልጸዋል? ለከፍፍሎቹስ መሠረት የሆኑት ነገሮች ምንድናቸው? ግለጌዎቹና ምሣሌዎቹ ምን ያህል ይጣጣማሉ? ወዘተ. የሚሉ በርካታ ጥያቄዎች መነሰታቸው አይቀሬ ነው። አግባብም ነው። የጥያቄዎቹ መነሰት እንደለ ሆኖ የቀደምት ሊቃውንቱ ግለጌዎች በጥቅሉ ሲታዩ የየምድቦቹን መስተፃምራን ለመተርጉምና ለመወሰን ሲበል ብቻ የቀረቡ ናቸው እንጂ፤ የዲስኩር እመልከቾቹን ውሁድ-አሀዳዊ ወይም ዲስኩራዊ ጠቀሜታና ተግባር ከጭብጥ አገነባብ፤ ከመረጃ መዋቅር፤ ከተሰተጋባሪዎች (participants) ሚናና ዳራዊ ዕውቀት ወዘተ. አኳያ አይገልጹም፤ አያመለክቱም።

እንዲያውም እንደንደቹ ግለጌዎች ግልጽነት የሌላቸውና የሀሰብም መፋለስ (መዘበት) ያለባቸው ይመስላሉ። ለምሳሌ "ለእፍራሽ" ወደረኛ መስተፃምር የተሰጠው ግለጌ (በይትበረክ ወልደ ሚካኤል መጽሐፍ መሠረት) "በፊት የተነገረውን ሀሰብ የሚቃወም መስተፃምር ነው" (ገጽ 107) ይላል። በዚህ ግለጌ መሠረት የሚቃወመው መስተፃምሩ ነው ወይስ ሌላ? የሚቃወመው መስተፃምሩ ከሆነ ቀደም ሲል ለመስተፃምር በጥቅሉ ከተሰጠው ተግባር (እያያዥነት) ጋር የሚጋጭ ይመስላል። መስተፃምርስ እንዴት በራሱ ሊቃወም ይችላል? ግለጌው እነዚህንና እነዚህን የመሰሰሉ ጥያቄዎች ማስነሰቱ አይቀሬ ነው። ይህም ከላይ እንደጠቀስነው ከግልጽነት መጓደል ወይም ከሀሰቡ ዝብነት

የመነጨ ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ ግን ሲታይ ቀደምት ሊቃውንት ስለመስተፃምራን የሰጧቸው ግለጌዎችና ማብራሪያዎች በወቅቱ ስለቋንቋ የነበረው አመለካከት ነፀብራቅ ናቸው ማለት ይቻላል።

እስከአሁን ከቃኘናቸው የሰዋስው ሊቃውንት ሌላ፣ በአማርኛ ሰዋስው ረገድ ሊጠቀሱ የሚችሉት በየ ይማም ናቸው። በየ ይማም (1987 ዓ.ም.) ከጻፉት <u>የአማርኛ ሰዋስው</u> መጽሐፋቸው መረዳት እንደሚቻለው ከተመሠረቱበት የቋንቋ ትውረት አኳያ ከቀደምቱ ሊቃውንት ጋር በብዙ የቋንቋ ጉዳዮች ረገድ ይለያሉ። በዚህ እንፃር በመስተፃምርም ላይ ባላቸው እቋምና በሚሰጡትም ግለጌ ይሄው ልዩነት በግልጽ ተንፀባርቆ ይታያል። እንደ በየ አመለካከት ከሆነ መስተፃምርና መስተዋድድ በቅርጽም በአገባብም እንድ ናቸው።

> ...ከመስተዋድድ ሌላ በቀደምት የሰዋስው ሊቃውንት ዘንድ መስተፃምር ተብሎ የሚታወቅ እንድ የቃል ክፍል ነበር። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ቃላት ግን በቅርፃቸው መስተዋድድ ውስጥ ከመደብናቸው ጋር እንድ ናቸው። በገባባቸውም ቢሆን ይህን ያህል ከመስተዋድድ የተለዩ አይደሉም። መስተፃምር የሚለውም ስያሜ የሚያጣምር የሚያያይዝ እንደማለት ስለሆነ የሚያዋድድ ከሚለው ከመስተዋድድ ግለጌ ጋር ተመሰሳይ ነው (ገጽ 61)።

ይህንንም በምሣሌ ለማሳየት፣ "ስለ" የሚል ቃል ያለባቸው ሁለት ምሣሌዎች ሰጥተው ያብራራሉ።

ሀ) አስቴር ስለ ገንዘብ ደንታ የለትም።

ለ) ካሣ አስቴር ስለታመመች በጣም አዘነ (ገጽ 61)።

በመጀመሪያው ዐረፍተነገር (ምሳሌ ሀ) ውስጥ "ስለ" የገባው "ገንዘብ" ከሚለው ስም ጋር ነው። ከሁለተኛው ዐረፍተ ነገር (ምሳሌ ለ) ውስጥ ደግሞ "ታመመች" ከሚለው ግስ ጋር ነው። ከስም ጋር በመጀመሪያው ዐረፍተነገር ዓይነት በመግባቱ መስተዋድድ ተብሎ ይጠራል። እንደገና በሁለተኛው ምሳሌ ዓይነት ከግስ ጋር በመግባቱ ይኼው ቃል መስተፃምር ተብሎ ይጠራል። መስተፃምር ያሰኘውም እንደተጠቀሰው ከግስ ጋር መግባቱ ብቻ ነው። ስለዚህ ከመስተዋድድ ጋር በቅርጽም ሆነ በአገባብ የተለየ ነው ለማለት እንደማያስደፍር ተብራርቷል። እንዲያውም መስተፃምር የሚል የተለየ ራሱን የቻለ የቃል ክፍል ሊኖር እንደማይችልና በመስተዋድድ ሥር በንኡስ ክፍልነት መጠቃለል እንደለበት አጠንክረው ያሳስባሉ።

> ...አሁንም ቢሆን መስተፃምር የሚባሉት በቅርጽ ሆነ በአገባብ መስተዋድድ ከሚባሉት የሚለዩበት በርካታ ባህርያት ስለሌሏቸው በዚያው በመስተዋድድ ውስጥ በንኡስ ክፍል ሊካተቱ ይችላሉ። ይህን ካደረግን መስተፃምር የሚባል ራሱን የቻለ ክፍል አይኖርም ማለት

ነው። ...ሊጠቃለሉ የሚችሉ ነገሮችን ማጠቃለል ዋና የጥናት ስልት ነውና (ባየ፣ 1987 ዓ.ም. ገጽ 63)።

በጽሁፋቸው ከቀረበው ሀሳብ እንደምንገነዘበው ከመስተዋድድ ሥር በንኡስ ክፍልነት መጠቃለል አለበቸው በማለት ያቀረቢቸው በሙሉ ቅጣይ መስተፃምራንን እንጂ፣ ቃላዊ ወይም ሐረጋዊ የሆኑትን መስተፃምራን አይደለም። እንዲያውም ስለቃላዊ ወይም ሐረጋዊ መስተጻምራን የጠቀሱት ዝርዝር ነገር በጽሁፋቸው ውስጥ አላጋጠመም። የተጠቀሰ ነገር ቢኖር በሌላ የጥናት መስክ መታየት የሚችሉ የቋንቋ አካላት መኖራቸውን የሚጠቁም የመሸጋገሪያ ሀሳብ ብቻ ነው።

በዚህ መሠረት በቃላት ክፍል (word class or category) ሊጠቃለሉ ያልቻሉ በርከታ ቃላት መኖራቸውን ያስገነዝበሉ። ይህ ማለት ግን እነዚህ ቃላት የአማርኛ ቋንቋ አካላት አይደሉም ማለት እንደልሆነም ይጠቅሳሉ። ከእነዚህም ቃላት ውስጥ "እንደ እስ፣ እንጂ፣ እስቲ፣ እማ፣ እህማ፣ ለካ ወዘተ." ያሉት ጥቂቶቹ መሆናቸውንም አመልክተዋል። ስለነዚህም ቃላት በተጨማሪ ሲገልጹ፣

> ...እንደነዚህ ያሉ ቃላት እስካሁን ባየናቸው ክፍሎች ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ አይደሉም። ምክንያቱም በቅርጽም ሆነ በአገባብ እነዚህ ከማንኛውም ክፍል ጋር አይመሰሰሉም። ስለዚህ እንደ እስ፣ እንጂ፣ ያሉትን ቃላት ለንግግር (ለዲስኩር) ክፍል በመተው ማንኛቸውንም በቅርፃቸው ወይም በሥርጭታቸው ወይም በሁለቱም ከላይ በተዘረዘሩት አምስት ክፍሎች ውስጥ ሊከተቱ በሚችሉት ቃላት ላይ ብቻ እናተኩራለን (ገጽ 67)።

በእጠቃላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው እነዚህንና የመሰሰሉትን ቃላት /ሐረጋት፣ ሰዋስው ሊተነትናቸው ወይም ሊያጠናቸው ብሎም በሕግጋቱ መሠረት በየክፍሉ ሊመድባቸው አለመቻሉን ነው። ከዚህ ባለፈ ግን የምንገነዘበው እነዚህ ቃላት /ሐረጋት ሊጠኑ የሚችሉት በዲስኩር ክፍል (ትንተና) መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ የእሁኑን ጥናታችንን ተገቢነትና ወቅታዊነት የጐላ ያደርገዋል።

2.2.2. ተግባራዊ አመለካከት /Functional View/

ቀደም ሲል በክፍል (2.1.1.) እንደተመለከትነው በጽሁፍ (በንግግርም ቢሆን) የሚተላለፍ መረጃ–በየትኛውም መንገድ ቢሆን–ግጥምጥምነት ይጠበቅበታል። ለዚህም ፀሐፊው፣ በጽሁፋዊ ውሁድ–አሀድ ውስጥ ያሉትን ዐረፍተ ንግግሮች (ወይም ዐረተ ነገሮች) ተስማሚ ዐውድ በመፍጠርና ሌሎችም የማዘመጃ መንገዶች በመጠቀም የተዘመዱ እንዲሆኑ ማድረግ ቀዳሚ ተግባሩ ነው። ምክንያቱም፣ በክፍል (2.1.1.) እንደተገለጸው፣ ፀሐፊው የሚጽፈው አንባቢውን እያሰበ (ያንባቢውን ዳራዊ ዕውቀት፣ የመረጃ ፍላጐት፣ አጠቃላይ ዕውቀትና ችሎታ ወዘተ.) ነው። (የዊደውሰንን፣ (1979 1984)፤ የናታል (1982) ንና የካሬል (1982)ን ሥራዎች ያገናዝቢል)።

አንባቢውም ባለው ዕውቀትና የመረጃ ፍላጐት ላይ በመመርኮዝ ውሁድ-አሀዱን ከፀሐፈው መሠረታዊ ዓላማ አኳያ መተርጐም መቻል ይጠበቅበታል። አለበለዚያ ተግባቦቱ የተዋጣለት አይሆንም፤ ችግርም ይገጥመዋል (የዚህን ጥናት ከፍል (2.1.1.)ንና (2.1.3.)ን ለዝርዝሩ ይመለከቷል)። ከዚህ በመነሳት ነው ጽሁፍ መስተጋብራዊ ነው የሚባለው። ስለሆነም ለጽሁፍ ግጥምጥምነትና ስሜት መስጠት ሁለቱም ተስተጋባሪዎች (ፀሐፊና አንባቢ) ተገቢ ሚና አላቸው (ዊደውሰን፤ 1979)።

እዚህ ላይ ሁለቱም ተስተጋባሪዎች ጽሁፉን ግጥምጥም የማድረግ ግዴታቸውን እንዴት ሊወጡት ይችላሉ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አግባብ ነው።ለጥያቄው መልስ ይሆን ዘንድ ታይለር (1992) ስለዲስኩር ማዋቀሪያ-ማገጣጠሚያ-አካላት ከገለጹት ውስጥ የሚከተለው ይገኝበታል።

> እስካሁን ተለይተው የታወቁት የዲስኩር ማዋቀሪያ አካላት ቃላዊ የዲስኩር እመልካቾች፤ ደጊመ-ውቅሮች (Patterns of repitition)፤ ዳኅራይ ጥቆማ፤ ሰዋሰዋዊ ተደጋግፎዎች (syntactic incorporations) ወዘተ. ናቸው። እነዚህም የዲስኩር ማዋቀሪያ አካላት በተገለጸው ሀሳብ ውስጥ የሚያመለክቱት ተጠየቃዊውንና ዋናውን ዝምድና ነው (ገጽ 714)።

ከተጠቀሰው ሀሳብ ውስጥ የምንረዳው የዲስኩርን ግጥምጥምነት ከሚጠቁሙት አካላት ስብስቦች (sets) ውስጥ የዲስኩር እመልካቾች ተጠቃሽ መሆናቸውን ነው። ስለእንግሊዝኛ ቋንቋ የዲስኩር እመልካቾች ስትፍሪን (1985:662) እንደገለጹት "በት (but)፤ ናው (now)፤ ላይክ (like)፤ እህ (oh)፤ ኤንድ (and)፤ ዱዩ ኖው? (Do you know?) ወዘተ." የመሰሉት የዲስኩር እመልካቾች የውሁድ-አሀዱን አካላት የሚያጣፍሩና (coordinate) ጥገኛ የሚያደርጉ (subordinate) ብቻ አይደሉም። በዲስኩሩ የሚተላለፈው መልዕክት እንዴት እንደሚተረጐምና ሀሳቡም እንዴት እንደሚዘመድ ያመለክታሉ። በፀሐፊውና በአንባቢው መካከል ያለውንም መስተጋብራዊ ስምምነትና ተሳትፎ ይጠቁማሉ። በተጨማሪም እያንዳንዱ ዐረፍተነገር በገባበት ቦታ ያለውን ተግባር ያመለክታሉ (ናታል፤ 1982: 92፤ ማክርቲ፤ 1991:46፤ ኑናን፤ 1993:26)።

ከዚህ አኳያ የዲስኩር እመልካቾች (መስተፃምራን) ማክርቲ (1991:46) እንደጠቀሱት "ደኃራይ ዝምድናን (anaphora) ወይም የወደፊት ዝምድናን (cataphora) አያመለክቱም"። በመሆኑም መስተፃምራን ከጥቆማ (reference)፤ ከመተካት (substitution)፤ ከመግደፍ (ellipsis) ወዘተ. ይለያሉ። ምክንያቱም ለአንባቢው በዲስኩሩ ውስጥ ቀድሞ የተጠቀሱትን ሀሳቦች የሚያስታውሱ አካላት ባለመሆናቸው ነው። ነገር ግን ከላይ እንደተጠቆመው የዲስኩሩን ሀሳብ ተለጣጣቂነት (textual sequence) ይጠብቃሉ። ያለውንም ዝምድና ይፋ ያደርጋሉ። ይህም ተዘምደ ፀሐፈው በውሀድ-አሀዱ ሁለት አካላት መካከል እንዲኖር የፈለገውን ዝምድና በይፋ ማመልከታቸውን ይገልፃል።

እዚህ ላይ መታወስ ያለበት የዲስኩር፣ መገጣጠሚያ አካላት ወይም የዲስኩር እመልካቾች "በራሳቸው በውሁድ-እሀዱ ውስጥ ዝምድናዎችን አይፈጥሩም፤ ያለውን ዝምድና ይፉ ያደርጋሉ እንጂ" (ኑናን 1993: 27)። ከዚህ ሌላ ግን ሀሊዴይ (1985a) እንደጠቀሱት እነዚህ አካላት በተፈጥሯቸው ጭብጣዊነት አላቸው (ገጽ 51)።

ሆልምስ (1986:17) የ"ዩ ኖው (you know)"ን አገባብ በተናጠል ለማወቅ ባደረጉት ጥናት እንደገለጹት የእንደዚህ ዓይነቱ የዲስኩር እመልካች ትንተና የቋንቋውን ልዩ ባህርያት (features) ለምሳሌ:- የድምፅ ቅላጼ ሰዋሰዋዊ ቦታ (syntatic position) በማጥናት ብቻ ምሉዕ አይሆንም። ከነዚህ በተጨማሪ በዲስኩር ውስጥ ያሉት ዐረፍተ-ንግግሮች የንግግር ተግባራት (speach acts)፣ የተነገሩበቸው ሁኔታዎች (illocutionary points)፣ የመስተጋብሩ መደበኛ መሆንና አለመሆን፣ የመስተጋብሩ ዓለማ፣ የተስተጋባሪዎች እንፃራዊ ደረጃና (relative status) ሚና ሁለቱ ተስተጋባሪዎች በጋራ የሚጋሩበት ዳራዊ ዕውቀት፣ እንዲሁም በቅድሚያ የሚገመተው ገጠመኝ (assumed experience) ወዘተ. አብረው በጥንቃቄ መጠናት አለባቸው።

እነዚህ የዲስኩር እመልካቾች በዚህ ዓይነት ተጠንተው ከታወቁ በኋላ ጠቅለል ባሉና ተጠየቃዊ ተዘምደዎችን በሚወክሉ ስብስቦች መከፋፈልና መመደብ እንደሚቻል በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ይገልፃሉ። በዚህ መሠረት ሀሊዴይና ሀሰን (1976) ስለ ግጥምጣሜ በጻፉት ጽሁፍ ውስጥ የመስተፃምራዊ ተዘምደዎችን ዓይነቶች በሚከተለው አኳኋን በእራት ዋና ዋና ምድቦች ከፍለዋቸዋል።

ሀ) አካይ (additive):- ፈርዘርሞር-furthermore፤ አልሶ-also፤ ኤንድ-and፤ ኢን አዘር ወርድስ-in other words...

ለ) ልየታ (adversative):- "ዬት-yet፤ ዘ-though፤ በት-but፤ ሃው ኤቨር-however፤ እን ዘ ኮንትራሪ-on the contrary..."

መ) ሰበባዊ (causal):- "ሶ-so፤ ዜን-then፤ ሄንስ-hence፤ ዜርፎር-therefore፤ ቢከዝ አቭ ዚስ-because of this..."

ሠ) ጊዜ-ጠቀስ (temporal):-"ዜን-then፤ ኔክስት-next፤ አፍተር ዘት-after that፤ ኣት ዘ ሴም ታይም-at the same time..."

/ምንጭ፤ ሃሊዴይና ሀሰን፤ 1976: 242-243/

(ዝርዝሩን ኣከባሪ ሠ-1 ይመልከቱ)።

ናታል (1982) ደግሞ ከንባብ ትምህርት አኳያ እነዚህ የዲስኩር አመልካቾች ያላቸውን ተግባር መሠረት በማድረግ፣ የሀሊዴይ ና ሀሰንን (1976) ምድቦች እሻሽለውና ከራሳቸውም እደዲሰች አክለው አቅርበዋል። በዚህም መሠረት መስተፃምራዊ ዝምድናን እንደገና በሦስት ዋና ዋና ምድቦችና በበርካታ ንኡሳን ክፍሎች ይከፍሏቸዋል። ከሃሊዴይና ሀሰን (1976) ጋር ያላቸውንም እንድነትና ልዩነት በሚከተለው አኳኋን ይገልጹታል።

> ...ብዙዎቹ ዲስኩር አመልካቾች መስተፃምር ከሚለው የሃሊዴይና ሀሰን (1976) ምድብ ሥር ይፈረጃሉ። ይሁንና እኛ በዐረፍተነገሮችም ውስጥ ያሉትን ዝምድናዎች የሚያመለክቱትንም ቃላት ጨምረናል። እነሱ ግን ያተኩሩበት በዐረፍተ ነገሮች መካከል ያሉትን ዝምድናዎች በሚያመለክቱት ላይ ብቻ ነበር (ናታል፣ 1982:85-96)።

የዲስኩር አመልካቾቹንም በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የከፈሏቸው በሚያመለክቱት ዝምድና መሠረት ነው። ሦስቱም ዋና ዋና አመልካቾች:-

ሀ) የተዘገቡት ሁነቶች (reported events) የተከሰቱባቸውን ቅደም ተከተሎች የሚያመለክቱ፣

ለ) የፀሐፊውን የዲስኩር እደረጃጀት በሀርይ የሚያመለክቱ፣

መ) ፀሐፊው ስለፃፋቸው እውነታዎችና ስለመሰሰሉት ያለውን አመለካከት የሚያመለክቱ ናቸው (ገጽ 96-97)።

የነዚህንም አመልካቾች ዝርዝር በዚህ ጥናት አባሪ <u>ሠ-2</u> ይመልከቱ።

ትሪምብል (1985) በበኩላቸው ደግሞ የዲስኩር አመልካቾችን (እንደ እሳቸው አጠራር የትርጓሜ አመልካቾች (semantic markers)) በሰይንስና ቴክኖሎጂ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ካላቸው ተግባር አኳያ አጥንተው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም በተቀዳድሞ (ORDER) እና በውቅሮች (PATTERNS)፣ ከፍለዋቸዋል። እነዚህንም ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እንደገና የጊዜ ተቀዳድሞ (time order)፣ የቦታ ተቀዳድሞ (place order)፣ ሰበባዊና ውጤት (causal and result)፣ የአስፈላጊነት ተቀዳድሞ (order of importance)፣ ውድድርና ንፅፅር (comparison and contrast)፣ ምስስሎሽ (analogy)፣ ምሰላ (exemplification) እና ማሳየት (illustration) በማለት በንኡሳን ክፍሎች ከፋፍለው አቅርበዋቸዋል (ገጽ 53-54)። የእነዚህን ዝርዝር በአባሪ <u>ሠ-3</u> ይመልከቱ።

ከላይ ከተገለጹት ተመራማሪዎች በተጨማሪ ሃች (1992: 225-226) እንደጠቀሱት የዲስኩር አመልካቾችን በማጥናት በሰይንስ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ በላቸው ተግባርና ድግግሞሽ መጠን ከፋፍለው

ለማሰየት ጥረት ከደረጉት ተመራማሪዎች ዊንተር (1971) አንዱ ናቸው። በእሰቸው ጥናት መሠረት፣ ጥናቱ በተከሄደበቸው ውሁድ-አህደች ውስጥ የሚከተሉት ምድቦች ተደጋግመው ተገኝተዋል። ተጠየቃዊ ተለጣጥቶ (logical sequence)፣ ንፅፅር (contrast) ጥርጣሬ/ ርግጠኝነት (doubt/certainity)፣ ኢንፅፅር (non-contrast) እና ተስፋፍቶ (expansion)።

ቻውድሮንና ሪቻርድስ (1986:127) የዲስኩር እመልካቾች፣ (የክፍል ውስጥ) ገለፃዎችን (lectures) በመረዳት ረገድ ያላቸውን ተፅዕኖ (effect) ለይቶ ለማወቅ በደረጉት ጥናት ውስጥ የዲስኩር እመልካቾቹን ከመዋቅራዊ ቅርፃቸው አኳያ ንኡሰን (ቃላዊና ሐረጋዊ) እመልካቾች (micro-markers) እና ዐብይ (ዐረፍተነገራዊ) እመልካቾች (macro-markers) በማለት ከፋፍለው አቅርበዋቸዋል። ንኡሰን እመልካቾቹንም እንደገና መከፋፈያ (segmentation)፣ ጊዜ-ጠቀስ፣ ሰበበዊ፣ ንጽጽር እና አጽንኦት በማለት ከፋፍለው ተመልክተዋቸዋል።

እስከሁን ድረስ ለማሰየት እንደተሞከረው የሁሉም ተመራማሪዎች የጥናት ትኩረት፣ ይዘውት እንደተነሱት ዓላማና ግብ የተለያየ ነው። በዚህም የተነሳ የዲስኩር እመልካቾቹም አተናተንና የምድቦች አከፋፈል አንዳንድ መመሰሰሎች ቢንፀባረቁበትም የተለያየ ሊሆን ችሏል። የሆነ ሆኖ ከነዚህ ጥናቶችና እመደደቦች እንድ የምንረዳው ነገር አለ። ይሄውም በየትኛውም ደረጃና በየትኛው ቋንቋ የዲስኩር እመልካቾችን በሚመለከት የሚደረጉ ጥናቶችና የሚደረስባቸው ውጤቶች እንደተመራማሪዎቹ ዓላማና የትኩረት አቅጣጫ ሊለያዩ የሚችሉ መሆናቸው ነው።

ስለዚህ እንደማክርቲ አገለለጽ (1991:46-47) በየትኛውም ደረጃ የዲስኩር እመልካቾችን ተግባርና ሥርጭት ለማጥናት የሚነሱ የዲስኩር ተንታኞች (discourse analysts) "ለሌሎቹ ሰዋሰዋዊ አካላት የሚጠይቋቸውን ጥያቄዎች ለመስተፃምራንም ይጠይቃሉ።"

> ...ዲስኩርን በመፍጠር ረገድ ምን ሚና ይጫወታሉ? ምድቦቹና ተዛምደዎቹ ከቋንቋ ቋንቋ ይለያያሉ? በንግግርና በጽሁፍ ውስጥ የተሠራጩት እንዴት ነው?...የትኛው የእጠቃቀም ባህርያቸው ነው በሰዋሰው ሊገለጽ የማይችለው? ወዘተ.።

በመሆኑም የተንታኞቹ ዋና ተግባር ለእነዚህ ጥያቄዎች በበቂ መረጃ የተደገፉ መልሶችን ማስገኘት ነው። በርግጥ ሁሉንም እመልካቾች በአንድ ጊዜ ማጥናት አይቻልም (ማክርቲ 1991)። ይሁንና ከተለያዩ አቅጣጫዎች በሚደረጉ ጥናቶች የሚደረስባቸው ውጤቶች ተደምረው የቋንቋውን ዲስኩር እመልካቾች ተግባርና አጠቃቀም በተገቢና በተሻለ ሁኔታ ሊያመለክቱ ይችላል የሚል እምነት አለ።

ይህም የእሁኑ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙትን ዲስኩር አመልካቾች– መስተፃምሮች– በሙሉ ለመተንተን እቅሙም ሆነ ጊዜው አይፈቅድለትም። ስለዚህ የሚያተኩረው በተማሪዎቹ ውሁድ–አሀዶች ውስጥ ከተከሰቱት ውስጥ በተወሰኑ ዲስኩር አመልካቾች (በክፍል 3.2.4.1. ዝርዝራቸው የተጠቀሰው) ላይ ብቻ ይሆናል።

በእጠቃለይ በዚህ ክፍል (2.1. - 2.2.) የጠቀስናቸው ትውረታዊና ተዘማጅ ሥራዎች ከጋሰር (1984) ና ከኢትዮጵያውያኑ ሥራዎች በቀር በእንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ የተሠሩ ናቸው። የጥናቶቹም ዓለማና ትኩረት የተለያየ እንደሆነም ቀደም ብሎ ተገልጿል። ይሁንና ከነዚህ ጥናቶች ውስጥ ለዚህ ጥናት ትኩረት በተለይም ለዲስኩር አመልካቾቹ ትንተናና ከፍፍል የተሻለ ቀረቤታ ያለው የሃሊዴይና ሀሰን (1976) ጥናታዊ ሥራ ነው። ስለሆነም ጥናቱ ይህንኑ የጥናት አካሄድና አመዳደብ መነሻ ያደርጋል።

ይሁን እንጂ የጥናቱን አካሄድና የዲስኩር አመልካቾቹንም አመዳደብ የበለጠ የሚወስኑት የሰበሰብናቸው መረጃዎች ዓይነትና መጠን መሆኑ አያጠራጥርም። ምክንያቱም "በእነዚህ የመረጃ ማዋቀሪያ አካላት–የዲስኩር አመልካቾች፣ አጠቃቀምና አሠረጫጨት አኳያ ቋንቋዎች ሊለያዩ ስለሚችሉ ነው" (ታይለር 1992:714)።

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴ

3.1. የመረጃ ምንጭ

በምዕራፍ አንድ እንደተጠቀሰው ይህ ጥናት የተመሠረተው በከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተማሪዎች ተራኪ ጽሁፎች ላይ ነው። የከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተመረጠውም በሙከራ ጥናቱ ወቅት ቀና ትብብር በማድረጉ፣ ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ፈቃድ በመስጠቱ፣ በቅርብም ያለ በመሆኑ ሲሆን፣ በተጨማሪ የትምህርት ክፍሉም መምህራን በመረጃ እሰበሰቡ የበኩላቸውን ትብብርና ዕገዛ በማድረጋቸው ነው።

በዚህ መሠረት ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ጽሁፋዊ መረጃ የሰጡት ተጠኚዎች በዚሁ ኮሌጅ የሚማሩት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ-ትምህርት፣ የዲፕሎማ መርሐግብር የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በሙሉ (ሃያ ሦስቱም) ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች ለዚህ ጥናት በመረጃ ሠጭነት የተወሰዱበትም ምክንያት:-

- በሦስቱም የትምህርት ደረጃዎች (ከአንደኛ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረስ) በቋንቋው በእፍ መፍቻ ቋንቋነት ሲገለገሉበትና ሲማሩት የቆዩ በመሆናቸው፣
- በኮሌጁ ቆይታቸውም የአማርኛን ሥነ መዋቅር የተማሩ በመሆናቸው፣
- የሚሰለጥኑበትም ቢያንስ በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ- በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃም የሚያስተምሩ መኖራቸው ሰይዘነጋ- ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ስለሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እነዚህን ዲስኩር አመልካቾች ሊያስተምሯቸው ተዘጋጅተዋል የሚል እምነት በመኖሩ፣
- በሙከራ ጥናቱ ወቅት በታየው ሁኔታ ለዋናውም ጥናት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆናቸው ነው።

3.2. የጥናቱ መረጃ

3.2.1. የጽሁፍ መረጃ

የዚህ ጥናት ዓለማ በከተቤ መምህራን ትምህርት ክሌጅ የሚማሩ የዲፕሎማ መርሐግብር፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ከፍለ-ትምህርት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በፃፏቸው ተራኪ ውሁድ-እሀደች ውስጥ በከፍተኛ ድግግሞሽ የገቡትን የዲስኩር እመልክቾች እጠቃቀምና ተግባር መተንተን ነው። በዚህ መሠረት ዋናው መረጃ የተማሪዎቹ ጽሁፍ ስለሆነ ተራኪ ጽሁፎች እንዲጽፉ ተደርጊል። ተራኪ ጽሁፎም የተመረጠበት ምክንያት ዲስኩር እመልክቾችን ደጋግሞ ለመጠቀም ዕድል ይሰጣል ተብሎ ስለታመነበት ነው።

በመሆኑም እያንዳንዱ ተማሪ ሁለት ሁለት ተራኪ ጽሁፎች ጽፏል። ሁለቱም ጽሁፎች የተፃፉት በክፍል ውስጥ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ከክፍል ውጪ ጽፈው ቢመጡ ጽሁፉ የራሳቸው ለመሆኑ ማረጋገጫ ማግኘት እስቸጋሪ ስለሚሆን በዚህ ረገድ ሊኖር የሚችለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ታስቦ ነው። ምንም እንኳ ጽሁፎቹን በክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ቢደረግም ጥናቱ የተማሪዎቹን የድርሰት ችሎታ ወይም የመፃፍ ፍጥነት ለመለክት የታለመ በለመሆኑ የጊዜ ገደብ አልተደረገበትም። ሁለቱም ጽሁፎች የተፃፉት በተማሪዎቹ ነፃ ምርጫ ላይ ተመሥርተው ቢሆንም ሁለተኛው ጽሁፍ ግን ለሁሉም በተሰጣቸው ርዕሰ-ነገር (topic) መሠረት የተፃፈ ነው። የአፃፃፋቸው ሂደትና እቀነጃጀታቸው ግን ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ምርጫ የተከሄደ ነበር።

3.2.2. የጽሁፍ መመሪያ አዘገጃጀት

ተራኪ ጽሁፎቻቸውን እንዲጽፉ የተደረገበት መንገድ በራሳቸው ነፃ ምርጫ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ከላይ ተጠቅሷል። ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ ሁለቱንም ጽሁፎች ለመፃፍ ይችሉ ዘንድ ግልጽ የሆነ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነበር። ይህን መሠረት በማድረግ ለሁለቱም ተራኪ ጽሁፎች መመሪያዎች በእጥኚው ተዘጋጅተው ለተማሪዎቹ ከመሰጠታቸው በፊት፣ በሁለት የዩኒቨርስቲ መምህራንና በሁለት የድህረ ምረቃ /ቲም/ ተማሪዎች

ተገምግመዋል። ከዚያም ከገምጋሚዎቹ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት ከተስተካከሉ በኋላ ተበዝተው ለሁሉም ተማሪዎች እንዲደርሱ ተደርገዋል።

የተዘጋጁትም ሁለት መመሪያዎች–በአባሪ መ–1 ና መ–2 እንደተመለከቱት– እያንዳንዳቸው በሁለት ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው። በክፍል አንድ የቀረበው ጠቅላላ መመሪያ ሆኖ ተማሪዎቹ ጽሁፎቹን ለምን እንደሚጽፉና የጥናቱንም ዓላማ በግልፅ የሚያስገነዝብ ነው። ይህ ክፍል ለሁለቱም መመሪያዎች አንድ በመሆኑ በሁለቱም መመሪያዎች በግንባር ገጽ ላይ ተሰጥቷል። ክፍል ሁለት ደግሞ ስለሚጽፏቸው ተራኪ ጽሁፎች የሚገልጽ ዝርዝር መመሪያ ሆኖ የሚጽፉባቸውን የቃላት መጠን፣ ስለሚጽፏቸው ተራኪ ጽሁፎች፣ በሚሰጧቸው ወረቀቶች ላይ እንዴት ማስፈር እንደለባቸው የሚያሳስብ ክፍል ነው። ይህ ክፍል ለሁለቱም መመሪያዎች አንድ በለመሆኑ በተለያየ መልክ የተዘጋጀ ነው። ስለሆነም በመጀመሪያው መመሪያ መሠረት የሚጽፉት ጽሁፍ ስለአንድ ስለሚያውቁት ታሪክ የሚተርክ፣ በሁለተኛ መመሪያ መሠረት ደግሞ ስለራሳቸው የሕይወት ታሪክ የሚተርክ ጽሁፍ ነው። በነዚህም መመሪያዎች መሠረት ሁለቱንም ጽሁፎች ጽፈዋል።

3.2.3. ጽሁፎቹ የተፃፉበት ሂደት

ተማሪዎቹ ጽሁፎቹን የፃፏቸው በተለያዩ ጊዜያት ነው። የመጀመሪያው በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ማብቂያ አካባቢ፣ ሁለተኛው ደግሞ በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት መጀመሪያ ላይ ነው። ይህም የሆነበት በተለየ ምክንያት ሳይሆን በተደረሰበት የመርሐግብር ስምምነት ነው። ጽሁፎቹንም እንዲጽፉ የተደረገው አጥኚውና በክሌጁ የሚያስተምሩ ሁለት መምህራን በተገኙበት ነው።

ተማሪዎቹ ጽሁፎቹን ከመፃፋቸው በፊት ለእያንዳንዳቸው ከተሰጧቸው የጽሁፍ መመሪያዎች በተጨማሪ ስለሚጽፏቸው ጽሁፎች ዓላማ፣ ከጽሁፎቻቸውም ስለሚሰበሰበው መረጃ ጠቃሚነት ስለሚጽፏቸውም ጽሁፎች ይዘትና የአፃፃፍ ምርጫ የየራሳቸው መሆኑን፣ የሚጽፉትም ለፈተና ስለአለመሆኑ በመምህሮቻቸውና በአጥኚው ተብራርቶላቸዋል።

ከዚህም ሌላ ሁለት የተለያዩ–እንደኛው ልሙጥ (መስመር የሌለው)፣ ሁለተኛው ደግሞ በለመስመር– ወረቀቶች ከተሰጧቸው በኋላ መስመር የሌለው ለረቂቅ ማውጫ (ለማርቀቂያ) በለመስመሩ ደግሞ የመጨረሻውንና የተጣራውን ጽሁፍ የሚጽፉበት እንደሆነ ተገልጸላቸዋል። ጽሁፎችንም የሚጽፉት ከድርሰት ወይም ከጽህፈት ትምህርት ጋር ከተያያዙ ዕውቀቶችና ከሂሎች አኳያ እነሱን ለመለካት በለመሆኑ ሁለቱም ጽሁፎች የጊዜ ገደብ ሳይደረግ ጽፈው በጨረሱበት ሰዓት– እንደጨረሱ– በአጥኚው ተሰብስበዋል።

በዚህ መልክ የተሰበሰቡት ጠቅላላ ጽሁፎች (በ1 ተማሪ x 2 ጽሁፍ ስሌት) 38 (ሰላሳ ስምንት) ናቸው። 38 የሆኑበትም ምክንያት የመጀመሪያው ጽሁፍ በተጻፈበት ቀን ሦስት (3) ሁለተኛው ጽሁፍ በተጻፈበት ቀን አምስት(5) ተማሪዎች ቀሪ በመሆናቸው ነው። ዝርዝሩ በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል።

የጽሁፍ ዓይነት	የጽሁፎች ብዛት በመቶኛ					
	የተፃፉ		የቀሩት		ድምር	
	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%
1ኛ ጽሁፍ	20	86.96	3	13.04	23	100
2ኛ ጽሁፍ	18	78.26	5	21.74	23	100
ድምር	38	82.61	8	17.39	46	100

3.2.4. <u>የጽሁፎች አሰተራረም ሂደት</u>

ጽሁፎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ ተከታይ የነበረው ተግባር ተማሪዎቹ በሁለቱም ጽሁፎቻቸው ውስጥ በከፍተኛ መጠን በተደጋጋሚ የተጠቀሙባቸውን የዲስኩር አመልካቾች አገባብ ትክክለኛ ነት በባለሙያዎች ማሰረም ነበር። ይህም የተደረገው ተማሪዎቹ የተጠቀሙባቸውን የዲስኩር አመልካቾች በደፈናው ከመተንተን በፊት በራሳቸው አጠቃቀም መሠረት ምን ያህል በትክክል እንደተጠቀሙባቸው በባለሙያዎች ለማረጋገጥ ታስቦ ነው።

3.2.4.1. <u>ቅድመ-እርማት ከንውን፤</u>

እርማቱ ከመካሄዱ በፊት የሚከተሉት ተግባራዊ ሆነዋል፤

- በሙከራ ጥናቱ ወቅት በተገኘው ውጤት መሠረት በተማሪዎቹ ጽሁፎች ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተደጋግመው የገቡት ዲስኩር አመልካቾች በዋናውም ጥናት ጽሁፋዊ መረጃዎች ውስጥ መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ዝርዝር ቆጠራ ተደረገ፤
- በዚህም በሁሉም ጽሁፎች ውስጥ እሉ የሚባሉት ዲስኩር አመልካቾች ምልከት እየተደረገባቸው በእጥኗው ተቆጠሩ፤
- የተዘለሉ ወይም የተረሱ እንደይኖሩና በእጥኗው የተቆጠሩትም ተገቢ ስለመሆናቸው በሁለት የድህረ ምረቃ /ቲም/ ተማሪዎች ግምገማ ተደረገባቸው፤
- ቀጥሎም በቆጠራው መሠረት በሁለቱም ጽሁፎች የተገኙት ዲስኩር አመልካቾች በተመሰሰይነታቸው- በመልክ በመልካቸው-ከተፈረጁ በኋላ በድግግሞሽቸው ቅደም ተከተል

ከትልቁ (ብዙ ድግግሞሽ ካለው) ወደ ትንሹ (ዝቅተኛ ድግግሞሽ ወደለው) ተራ ቁጥር በመስጠት፤ ለዚሁ በተዘጋጀው ሠንጠረዥ ለቀማና ምዝገባ ተደረገ፤

- ከዚያም በእያንዳንዱ ጽሁፍ ውስጥ የተገኙት ዲስኩር እመልካቾች በሠንጠረዡ ላይ በተመዘገቡበት ተራ ቁጥር መሠረት እኩሌታቸው (median) ከተለየ በኋላ፤ ከእኩሌታ በላይ የተዘረዘሩት ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸው ዲስኩር እመልካቾች ተለዩ፤
- ከእነዚህ ውስጥ እንደገና በሁለቱም ጽሁፎች ውስጥ የሚገኙት ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸው ዲስኩር እመልካቾች ተለይተው ታወቁ፤
- በዚህ መሠረት ተለይተው የታወቁት ዲስኩር እመልካቾች–(ነገር) ግን፤ (እ)ና፤ ከዚያ(ም)፤ ደግሞ(ም)፤ (–) የተነሳ፤ ወይ(ም/ስ)፤ (ይሁን) እንጂ፤ ስለዚህ(ም)...ሲሆኑ እነዚህም በጽሁፎቹ ውስጥ በገቡበት እኩኋን ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ በባለሙያዎች እንዲታረሙ ተደረጉ።

3.2.4.2. <u>የጽሁፍ እርማት መመሪያ አዘገጃጀት፤</u>

በጥናቱ ዓላማ መሠረት በተማሪዎቹ ተራኪ ጽሁፎች ውስጥ የገቡትን ዲስኩር እመልካቾች አገባብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከአጥኚው ውጪ የሆኑ ባለሙያዎች እንዲያርሙት ተደርጓል። እርማቱም የተመሠረተው ለዚሁ በተዘጋጀው መመሪያ ላይ ነው። ይህ በአባሪ <u>መ–3</u> ላይ የቀረበው መመሪያ በአጥኚው ከተዘጋጀ በኋላ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በሁለት መምህራንና በአንድ የድህረምረቃ ተማሪ እንዲታይ ተደርጓል። ከዚያም በገምጋሚዎቹ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ተስተካክሏል።

መመሪያው በቅድሚያ የአጥኚው ዓላማ ምን እንደሆነ በግልጽ ያስረዳል። ቀጥሎም የመመሪያው ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በቅደም ተከተል ቀርበውበታል። ከፍል አንድ "አጠቃላይ" በሚል ርዕስ ሥር፤ እርማቱ የተማሪዎቹን የድርሰት ችሎታ የሚለካ አለመሆኑንና ዝርዝር የድርሰት እርማት የማይደረግበት መሆኑን፤ የእርማቱ ዋና ትኩረት የዲስኩር እመልካቾች ብቻ መሆናቸውን፤ በእርማቱም ሂደት እንደ አገባባቸው ትክክልና ስህተት ለሆኑት ዲስኩር እመልካቾች እንዴት የ(✓) እና የ(X) ምልክት ማድረግ እንደሚገባ፤ ስህተት ናቸው ለሚሏቸውም ተውላጥ ከለ፤ የትና እንዴት ማመልከት እንደለበቸው ያብራራል። በተጨማሪም እርማቱ የማይመለከታቸውን የቋንቋ አካላት ይጠቁማል።

የዚህ መመሪያ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ እርማቱ የሚመለከታቸውን የዲስኩር እመልካቾች ዝርዝር በከፊል የያዘነው። ይህ ክፍል በሥሩ የተዘረዘሩትን ዲስኩር እመልካቾች ብቻ እንዲይዝ ከመደረጉ በፊት ለሙከራ ጥናቱ እርማት መነሻ ሊሆኑ የሚችሉትን ዲስኩር እመልካቾች በዝርዝር የያዘ ክፍል ነበር።

3.2.4.3. <u>የእርማት ሂደት</u>

- በድግግሞሽቸው መሠረት ተለይተው የታወቁት ዲስኩር አመልካቾች በእርማቱ ወቅት እንዳይዘለሉ ለማድረግ በእርሳስ ምልክት ከተደረገባቸውና መለያ ቁጥር ከተሰጣቸው በኋላ ለበለሙያዎቹ እንዲደረሱ ሆነው፤ ጽሁፎቹ በሙሉ በፎቶ ኮፒ ተራቡ።
- ከዚያም ዲስኩር አመልካቾቹን የሚያርሙ አራት (4) የድህረምረቃ /ቲም/ ተማሪዎችና ሦስት (3) የትምህርት ደረጃቸው ቢ.ኤ. የሆኑ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፤ በድምሩ ሰባት አራሚዎች ተመረጡ። የጽሁፎቹም ፎቶ ኮፒ ለእያንዳንዳቸው ተሰጣቸው። ከዚያ በመመሪያው መሠረት ጽሁፎቹ ታረሙ።

- ከታረሙም በኋላ በእያንዳንዱ ዲስኩር አመልካች አገባብና አጠቃቀም ላይ አራሚዎቹ በሰቀመጧቸው የትክክል (✓)ና የስህተት (X) ምልክቶች መሠረት በሠንጠረዥ ላይ ዲስኩር አመልካቾቹ ተለቅመው ተመዘገቡ፤ በሌላም መተካት አለባቸው ተብለው ለተመለከቱትም ዲስኩር አመልካቾች የተሰጡት ተውላጦች (ትክኾ) ተለይተው በየአንዳንዱ ተመዘገቡ።

3.3. <u>የመረጃ አተናተን ስልት፤</u>

የጥናቱ ቀዳሚ ተግባር ቀደም ሲል በ(3.2.4.1.) የተጠቀሱትን ዲስኩር አመልካቾች አገባብ፤ ሥርጭትና ዲስኩር ተግባር መተንተን በመሆኑ፤ ጥናቱ በገለጭ ዓይነታዊ (qualitative) ዘዴና፤ በመጠናዊ (quantitative) ዘዴ ይጠቀማል።

3.3.1. <u>ዓይነታዊ ዘዴ፤</u>

ጥናቱ በመሠረቱ የዲስኩር አመልካቾችን ዲስኩራዊ ተግባር የሚተነትን ነው። ስለዚህ ዲስኩር አመልካቾቹ በጽሁፎቹ ውስጥ በገቡበት ሁኔታ ያላቸው ተግባር ምን እንደሆነ ከጽሁፎቹ ማስረጃ እየወሰደ ይተነትናል። ትንተናውም የተከሄደው ከጠቅላላ ሥነ ልሳን (General Linguistics) መሠረተ ሀሳቦች አንፃር ነው፤ ምክንያቱም ጥናቱ ከአንድ የዕውቀት ዘርፍ (ለምሳሌ፦ ከአእምሮት ትውረት (Cognitive Theory) ከአእምሯዊ ምስል ትውረት (Shema Theory) ወዘተ.) አኳያ ብቻ የሚደረግ ባለመሆኑ ነው። ለዚህም ጥናቱ በአመዛኙ ሃሊዴይና ሀሰን (1976) በፃፉት ጽሁፍ ውስጥ የመስተፃምራንን ተግባር ለመተንተን የተጠቀሙበትን አከሄድ ይከተላል።

ዲስኩር እመልከቾች በእብዛኛው በዐቢይ ሐረጎች መካከል ወይም በዐረፍተነገሮች መካከል በሁለተኛው ዐረፍተነገር መነሻ አካባቢ ይገኛሉ። በዚህ የተነሳ ዲስኩር እመልከቾቹ ከዐረፍተነገሮች-ብሎም ከውሁድ-አሀደች-ጭብጦች (themes) ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነትና ለጭብጥ አወቃቀሩም ያላቸውን አስተዋጽኦ ለመተንተን የዲ ኔሽ (1974) "የጭብጥ አስተዳደግ ውቅሮች (thematic patterns)" በተግባር ላይ ውለዋል (ዝርዝሩ በከፍል ሁለት ትውረታዊ ቅኝት ውስጥ ቀርቧል)።

3.3.2. <u>መጠናዊ ዘዴ</u>

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚከተሉት ስታትስቲካዊ ዘዴዎችና ቀመሮች በተግባር ላይ ውለዋል።

- በእያንዳንዱ ዲስኩር እመልከች እኪያ በሁሉም እራሚዎች መካከል ያለውን ስምምነትና ልዩነት እንዲሁም የጠቅላላ እርማቱን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ "Chronbac alpha" ስታትስቲካዊ ዘዴ በጥቅም ላይ ውሏል። ይህም ዘዴ የተመረጠው መረጃው በሁለት የተከፈለ (dicotomized) በመሆኑ ተስማሚ የሆነው ስታትስቲካዊ ቀመር ይሽው በመሆኑ ነው፣

- በእያንዳንዱ ጽሁፍና በሁሉም ጽሁፎች ውስጥ የተመረጡትን ዲስኩር እመልከቾች ሥርጭት ለመለየት፣ እንዲሁም አንድ ዲስኩር እመልከች በራሱ ውስጥ ለተለያዩ ዲስኩራዊ ተግባራት በምን ያህል ሥርጭት እንደገባ ለማስላትና ለመለየት የ"ካይ-ስኪር-(chi-square)" ቀመር አልፎ አልፎ በሥራ ውሏል።

- ከላይ ከተጠቀሱት ስታትስቲካዊ ቀመሮች ውጪ ጥናቱ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ በመቶኛ- በፐርሰንታይል- ስሌት ይጠቀማል።

ምዕራፍ አራት

የጥናቱ ውጤትና ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በክተቤ መምህራን ትምህርት ከሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ-ትምህርት የዲፕሎማ መርሀግብር የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በጻፏቸው ሁለት ተራኪ ውህድ-እሀደች ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ዲስኩር አመልከቾች ዲስኩራዊ ተግባርና ሥርጭት መተንተን ነው። ጥናቱም በሂደት የሚመልሰቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች:-

- በተማሪዎቹ ተራኪ ውሁድ-እሀደች ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተደጋግመው የገቡት ቃላዊና ሐረጋዊ ዲስኩር አመልካቾች የትኞቹ ናቸው? ሥርጭታቸውና አጠቃቀማቸውስ እንዴት ነው?
- በልማዳዊ የሰዋሰው መፃሕፍት ውስጥ ከተጠቀሰው "ቃላትና ሐረጋትን እንዲሁም ፀረፍተነገሮችንና ፀረፍተነገሮችን ከማያያዝ" የተለየ ተግባር አላቸው? ካላቸውስ ምን ምን ናቸው?
- በተማሪዎቹ ጽሑፎች ውስጥ ተደጋግመው በገቡት ዲስኩር አመልካቾች የተመለከቱት ተግባራት በተወሰኑ ምድቦች ሊከተቱ ይችላሉ? የሚሉ መሆናቸው በጥናቱ ዓላማ በ1.3. ተገልጿል።

ከዚህ በመነሳት በዚህ ምዕራፍ በተማሪዎቹ ጽሑፎች መረጃነት ለሚደረገው የዲስኩር አመልካቾች ትንተና ያመች ዘንድ ምዕራፉ በሁለት ዐበይት ክፍሎች ተከፍሏል።

የመጀመሪያው ዐብይ ክፍል ሁለት ንዑሳን ክፍሎች አሉት፣ እንደኛው ይህ ትንተና የሚመለከታቸው ዲስኩር አመልካቾች በሁለቱም ተራኪ ውሁድ-እሀደች (ውሁድ-እሀድ እንድና ሁለት) ውስጥ ያላቸውን አጎዛዊ ሥርጭት ይገልጻል። በቅድሚያ ዲስኩር አመልካቾቹ በእያንዳንዱ ውሁድ-እሀድ ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንደገቡ በድግግሞሻቸው መጠን ቅደም ተከተል መሠረት ይቀርባሉ። ሁለተኛው ደግሞ የነዚሁኑ ዲስኩር አመልካቾች አገባባዊ (አጠቃቀማዊ) ሥርጭት ይዘረዝራል። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ተተንታኝ ዲስኩር አመልካች በውሁድ-እሀደች ውስጥ የተለያዩ ተጠየቃዊ ተዛምዶዎችን ለማመልከት የገባባቸው የቋንቋ አውዶች (linguistic context) በዝርዝር ይቀርባሉ።

ሁለተኛው ዐብይ ክፍል በፈንታው የዲስኩር አመልካቾቹን ዝርዝር ተግባራትና የሚያመለክቱትን ተጠየቃዊ ተዛምዶ፣ እንዲሁም በጭብጥ መዋቅር-ጭው-ውስጥ ያላቸውን

አገልግሎት የተለያዩ መረጃዎችን በመጥቀስ ይተነትናል። በመሆኑም ይህ ክፍል እያንዳንዱ ተተኪ ዲስኩር አመልካች ያለው ተግባርና በ"ጭው" ውስጥ ያለው ሚና በነፍስ-ወከፍ የሚገለጽበትና የሚተነተንበት ክፍል ነው።

4.1. ሥርጭተ-ዲስኩር አመልቾች፣

4.1.1. አጠቃላይ የዲስኩር አመልካቾች ብዛትና ስርጭት፣

4.1.1.1. ውሁድ-አሀድ አንድ

በክፍል 3.2.3. በተገለጸው መሠረት ለዚህ ጥናት መረጃነት ከተሰበሰቡት 38 ተራኪ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ሃያዎቹ በመጀመሪያ የተገፉ በመሆናቸው ውሁድ-አሀድ አንድ ተብለው ይጠራሉ። በነዚህ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት ዲስኩር አመልካቾች በድምሩ 211 ጊዜ ገብተው ተገኝተዋል። (ዝርዝሩን ከአባሪ U-2 ይመለከቷል።) በዚህም መሠረት የእያንዳንዳቸውን የድግግሞሽ መጠን መሠረት በማድረግ በዲስኩር አመልካቾቹ መካከል ያለው የሥርጭት ተመሰሳይነትና ልዩነት በንጽጽር እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1፣ በውሁድ-አሀድ አንድ ውስጥ መካከለኛ ሥርጭት ያላቸው ዲስኩር አመልካቾች ንፅፅር።

ተራ ቁ.	ዲስኩር አመልካች	O	E	$(O-E)^2$	$\frac{(O-E)^2}{E}$
3	(-)እንጂ	28.38	25	11.42	0.46
4	ደግሞ	25.68	25	0.46	0.02
5	ስለዚህ(ም)	24.32	25	0.46	0.02
6	ወይ(ም/ስ)	21.62	25	11.42	0.46

$\chi^2 = 0.96$፣ $P>.05$

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ 1 መረዳት እንደሚቻለው "የካይስኳሩ" ውጤት በ$p>.05$ የጉልህነት ደረጃ በዲስኩር አመልካቾቹ አጠቃቀም ረገድ የጉላ የሥርጭት ልዩነት እንደሌለ ያሰያል። ይህም እነዚህ ዲስኩር አመልካቾች በሃያዎቹም ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ከሞላ ጉደል በተመሣሣይ ሁኔታ ተሠራጭተው እንደሚገኙ የሚጠቁም ነው።

በዚህ ዓይነት በጣም ተቀራራቢ ድግግሞሽ ያላቸው "ስለዚህ" "ደግሞ" እና "ወይም (ም/ስ)" ተወስደው ሲነፃፀሩ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል።

ሠንጠረዥ -2፣ በውሁድ-አሀድ እንድ ውስጥ የ"ደግሞ(-)"፣ የ"ስለዚህ(ም)" እና የ"ወይ(ም/ስ)" ሥርጭት ንፅፅር

ተራ ቁ.	ዲስኩር አመልካች	O	E	$(O-E)^2$	$\frac{(O-E)^2}{E}$
4	ደግሞ(-)	35.85	33.33	6.35	0.012
5	ስለዚህ(ም)	33.96	33.33	0.3969	0.19
6	ወይ(ም/ስ)	30.19	33.33	9.86	0.30

$\chi^2 = 0.50$፣ $p>.05$

ከላይ በሠንጠረዥ-2 እንደተመለከተው እነዚህም ሦስት ዲስኩር አመልካቾች በሃያዎቹም ውሁድ-አሀዶች ውስጥ በተመሰሰይ ሁኔታ ተደጋግመው በጥቅም ላይ ውለዋል። ስለሆነም ውጤቱ ዲስኩር አመልካቾቹ በተማሪዎቹ ጽሑፎች ውስጥ ያላቸው ስርጭት እጅግ በጣም የተቀራረበ መሆኑን ያሰያል። ከእነዚህ ሌላ ብዙ ጊዜ ተደጋግመው የገቡት "(-)ግን" ና "(እ)ና" ናቸው። በእነዚህ ሁለት ዲስኩር አመልካቾች መከከል ያለው የሥርጭት ተመሰሰይነትና ልዩነት ቀጥሎ በሠንጠረዥ -3 ይቀርባል።

ሠንጠረዥ -3፣ በውሁድ-አሀድ አንድ የ"ግን" ና የ"(እ)ና" ሥርጭትን ንጽጽር

ተራ ቁ.	ዲስኩር አመልካች	O	E	$O-E^2$	$\frac{(O-E)^2}{E}$
1	(-)ግን	52.99	50	8.94	0.18
2	(እ)ና	47.01	50	8.94	0.18

$\chi^2 = 0.36$፣ $p>.05$

ሠንጠረዥ -3 እንደሚያመለክተው በውሁድ-አሀድ አንድ ሃያ ጽሑፎች ውስጥ በ"ግን" እና በ"(እ)ና" ሥርጭት መከከል ጉልህ ልዩነት (significant difference) የለም። ስለዚህ በውሁድ-አሀዶቹ ውስጥ "ግን" እና "እና" ከሞላ ጉደል በእኩል ደረጃ በጥቅም ላይ ውለዋል ማለት ነው። በሌላም በኩል እነዚህ ሁለት ዲስኩር አመልካቾች ከሌሎቹ ስድስት አመልካቾች በበለጠ መጠን በውሁድ-አሀድ አንድ ሃያ ጽሑፎች ውስጥ መሠራጨታቸውንም ይጠቁማል።

በእጠቃላይ በውሁድ-አሀድ እንድ ውስጥ ስምንቱ ዲስኩር እመልከቾች በየሥርጭታቸው ተቀራራቢነት እንፃር በምድብ ተለይተው እርስ በርስ ሲነፃፀሩ የጐላ የሥርጭት ልዩነት አያሳዩ እንጂ በጥቅል ስምንቱም ሲነፃፀሩ ልዩነት እንደለ፣ ከነዚህም ውስጥ "ግን" እና "እና" ከፍተኛ የሥርጭት ድርሻ እንዳላቸውና ተማሪዎቹም አዘውትረው እንደተጠቀሙባቸው መረዳት ተችሏል።

4.1.1.2. ውሁድ-አሀድ ሁለት

ስምንቱ የዲስኩር እመልከቾች በውሁድ-አሀድ ሁለት ውስጥ ያላቸው ሥርጭት ምን እንደሚመስል ቀጥሎ ለማሳየት ይሞከራል። በውሁድ-አሀድ ሁለት ሥር የተከተቱ 18 ውሁድ-አሀዶች ናቸው። (ለዝርዝሩ 3.2.3. ን ይመለከቷል) በእነዚህ አሥራ ስምንት ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ስምንቱ ዲስኩር እመልከቾች 180 ጊዜ ተደጋግመው ገብተዋል። (ዝርዝሩን አባሪ ሀ-2 ይመለከቷል) በዚህ መሠረት ደረጃ በደረጃ ሥርጭታቸውን መሠረት በማድረግ ዲስኩር እመልከቾችን ከፋፍለን ብናነፃፅር የሚከተሉትን ውጤቶች እናገኛለን።

ሠንጠረዥ -4፣በውሁድ-አሀድ ሁለት ውስጥ ዝቅተኛ ሥርጭት (ከስምንቱ ዲ.አ.እንፃር) ያላቸው ዲስኩር እመልከቾች ንጽጽር፣

ተራ ቁ.	ዲስኩር እመልከች	O	E	$(O-E)^2$	$\frac{(O-E)^2}{E}$
5	(-)እንጂ	25.71	25	0.50	0.02
6	-የተነሳ	25.71	25	0.50	0.02
7	ወይ(ም/ስ)	25.71	25	0.50	0.02
8	ስለዚህ(ም)	22.86	25	4.58	0.18

$\chi^2 = 0.24$፣ $P>.05$

እነዚህ አራት ዲስኩር እመልከቾች በውሁድ-አሀድ ሁለት ጽሑፎች ውስጥ በተመሣሣይ ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ ተሰራጭተው የሚገኙ ናቸው። ከላይ በሠንጠረዥ -4 የተመለከተው ውጤት የሚያመለክተው እነዚህ ዲስኩር እመልከቶች በሁሉም 18 ጽሑፎች ውስጥ በተማሣሣይ ሁኔታ መሠራጨታቸውን ነው። በውሁድ-አሀድ አንድ ውስጥም እነዚሁ ዲስኩር እመልከቾች በተመሰሰይ ሁኔታ የጐላ ልዩነት ሳያሳዩ መሠራጨታቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል። በመሆኑም "(-)እንጂ"፣ "-የተነሳ"፣ "ወይ(ም/ስ)" እና "ስለዚህ(ም)" በሁለቱም ውሁድ-አሀድ ጽሑፎች ውስጥ በተመሰሰይ ደረጃ ተሠራጭተዋል ማለት ይቻላል።

በሌላ መልኩ ደግሞ ከነዚህ ሌላ ከፍ ያለ ስርጭት ያላቸው ዲስኩር አመልካቾች ሲነፃፀሩ የሚታየው ውጤት ቀጥሎ በሠንጠረዥ -5 ቀርቧል።

ሠንጠረዥ-5፣በውሁድ-አሀድ ሁለት ውስጥ ከፍ ያለ ሥርጭት ያላቸው ሦስት ዲስኩር አመልካቾች ንፅፅር

ተራ ቁ.	ዲስኩር አመልካች	O	E	$(O-E)^2$	$\frac{(O-E)^2}{E}$
1	(-)ግን	50.00	33.33	277.89	8.34
2	(እ)ና(ም)	27.69	33.33	31.81	0.95
3	ከዚያ(-)	22.31	33.33	121.44	3.64

χ^2= 12.93፣ P<.05

በሠንጠረዥ -5 እንደተመለከተው በእነዚህ ሦስት ዲስኩር አመልካቾች መካከል በP<.05 ደረጃ የጐላ የሥርጭት ልዩነት ታይቷል። ስለሆነም እነዚህ ሦስት ዲስኩር አመልካቾች በውሁድ-አሀድ ሁለት አሥራ ስምንት ጽሑፎች ውስጥ ተመሣሣይ ሥርጭት የላቸውም። ስለሆነም እንዳቸው ከእንዳቸው በአሠረጫጨት የሚለዩበት ሁኔታ ይታያል። በመጨረሻም በውሁድ-አሀድ ሁለት ውስጥ በጣም ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ዲስኩር አመልካቾች ብናነፃፅር የሚከተለውን ውጤት እገኛለን።

ሠንጠረዥ -6 በውሁድ-አሀድ ሁለት ውስጥ ከፍተኛ ስርጭት ያላቸው ሁለት ዲስኩር አመልካቾች ንፅፅር

ተራ ቁ.	ዲስኩር አመልካች	O	E	$(O-E)^2$	$\frac{(O-E)^2}{E}$
1	(-)ግን	64.36	50	206.21	4.12
2	(እ)ና(ም)	35.64	50	206.21	4.12

χ^2= 8.24፣ P<.05

በውሁድ-እሀድ አንድ ውስጥ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው እነዚህ ሁለት ዲስኩር አመልካቾች በሥርጭታቸው የጉላ ልዩነት ሰያሳዩ (χ^2 = .36፣ P>.05) በጥቅም ላይ ውለው ነበር። በውሁድ-እሀድ ሁለት ግን ሁለቱ ዲስኩር አመልካቾች በጉላ ልዩነት በP<.05 ደረጃ መለያየታቸውን የተገኘው ውጤት (χ^2=8.24) ያረጋግጣል። ስለሆነም እነዚህ ዲስኩር አመልካቾች በመካከላቸው የሥርጭት ልዩነት ጉልቶ ታይቷል ማለት ነው። በእርግጥ እንደውሁድ-እሀድ አንድ ሁሉ በውሁድ-እሀድ ሁለትም ውስጥ እነዚህ ዲስኩር አመልካቾች ከሌሎቹ በበለጠ ተደጋግመው ገብተዋል። ሆኖም ተማሪዎቹ በሁለተኛው ጽሑፋቸው ውስጥ እንደመጀመሪያው ውሁድ-እሀድ በተቀራረበና በተመሰሰለ መጠን የተጠቀሙባቸው አለመሆናቸውን ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል።

4.1.1.3. <u>የውሁድ-እሀድ አንድና ሁለት ንጽጽር፣</u>

በ4.1.1.1.ና በ4.1.1.2. እንደተዘረዘረው በዲስኩር አመልካቾች አሃዛዊ ሥርጭት መካከል ያለው ልዩነት እምብዛም አይደለም። ከፍተኛ፣ መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ ሥርጭት ያላቸው የዲስኩር አመልካቾች በየምድባቸው ሲነፃፀሩ በተገኘው ውጤት መሠረት፣

ሀ. በውሁድ-እሀድ አንድ በየምድቡ የጉላ የሥርጭት ልዩነት እንዳልታየና፣

ለ. በውሁድ-እሀድ ሁለት ግን ከፍተኛ ሥርጭት ባላቸው ዲስኩር አመልካቾች መካከል ብቻ በP<.05 የጉልህነት ደረጃ ልዩነት (χ^2 = 8.24፣ P<.05) እንደታየ በቦታው ተመልክቷል። መካከለኛ ደረጃ ሥርጭት ያላቸው ዲስኩር አመልካቾች በሁሉም ውሁድ-እሀደች ውስጥ በP>.05 የጉልህነት ደረጃ ልዩነት እንደሌላቸው ታይቷል። በአጠቃላይ በሁለቱም ውሁድ-እሀደች ውስጥ የሁሉም ዲስኩር አመልካቾች ሥርጭት ልዩነት የካይ ስኳር" ውጤት ሲነፃፀር የሚከተለውን ይመስላል።

ሠንጠረዥ -7፣ በሁለቱም ውሁድ-እሀደች ውስጥ የሁሉም ዲስኩር አመልካቾች ሥርጭት ልዩነት፣

ውሁድ-እሀድ	"ካይ ስኳር" (χ^2)	P-Value*
ውሁድ-እሀድ አንድ	51.00	.05
ውሁድ-እሀድ ሁለት	70.20	.05
ጠቅላላ	55.52	.05

* P<.05

ከሠንጠረዥ -7 ማየት እንደሚቻለው በP<.05 የጉልህነት ደረጃ ከ"ከይ ስኴር" ጠቅላላ ውጤቶች ልዩነት አሳይተዋል። ይህም ማለት በሁሉም ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ዲስኩር አመልካቾቹ በተመጣጣኝ መጠን አለመሠራጨታቸውን ነው። በሌላ አገባብ የአጠቃቀም ልዩነት በመካከላቸው አለ ማለት ነው።

ዲስኩር አመልካቾቹ እንደገና በላቸው የሥርጭት ደረጃ መሠረት በሁለቱ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ያላቸውን ተዛምዶ (Correlation) "በደረጃ ተቀዳድሞ የተዛምዶ (ρ)ማትሪክስ" (Rank Order Correlation) የተገኘው ውጤት የሚከተለው ነው።

ሠንጠረዥ -8፣ በዲስኩር አመልካቾች ሥርጭት ውስጥ በተዛምዶዎች መካከል ያለውን "የደረጃ ተቀዳድሞ ተዛምዶ (ρ)" ማትሪክስ" የሚያሳይ ሠንጠረዥ፣

	ውሁድ-አሀድ አንድ	ውሁድ-አሀድ ሁለት	ጠቅላላ
ውሁድ-አሀድ አንድ	—	.55**	.73*
ውሁድ-አሀድ ሁለት		—	.88*
ጠቅላላ			—

* P<.05

** P>.05

ይህ በውሁድ-አሀድ አንድና ሁለት መካከል ያለው ተዛምዶ በጥቅሉ ሲታይ አዎንታዊ (ρ=.55፣ P>.05) ነው። ከዚህ እንዳር በውሁድ-አሀዶች ውስጥ ዲስኩር አመልካቾቹ በላቸው ሥርጭት መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ አለ ማለት ይቻላል። ሆኖም በP>.05 የጉልህነት ደረጃ ሲታይ ያለው ተዛምዶ ጉልህ ተዛምዶ ነው ማለት አይቻልም። ይህም የሚያሳየው እነዚህ ዲስኩር አመልካቾች በሁለቱም ውሁድ-አሀዶች ውስጥ በእኩል መጠን አለመሠራጨታቸውን ነው። ቢሆንም የተዛምዶው ውጤት አዎንታዊ በመሆኑ በሥርጭታቸው ረገድ ተቀራራቢነት ይታያል ማለት ይቻላል።

እስከአሁን ድረስ (4.1.1.1. - 4.1.1.3.) የተመለከትነው፣ ዲስኩር አመልካቾቹ ያላቸው ሥርጭት ሲነፃፀር በመካከላቸው የታየውን የሥርጭት ልዩነትና ተዛምዶ ነበር። ቀጥለን የምንመለከተው ደግሞ የዲስኩር አመልካቾቹን ውሁድ-አሀዳዊ አገባብ ትክክለኛነት በረሙት በለሙያዎች መካከል ያለውን ውስጣዊ ስምምነት ይሆናል።

የጥናቱ ትኩረት የሆኑት ዲስኩር አመልካቾች በተማሪዎቹ ተራኪ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ያላቸው አገባብና አጠቃቀም፣ ትክክል መሆንና አለመሆን በባለሙያዎች እንደሚታረምና አጠቃላይ የእርማቱም ሂደት ምን እንደሚመስል በ3.2.4. ተገልጿል። በተጨማሪም ይህ የባለሙያዎች እርማት አስተማማኝነት በየትኛው ስታትስቲካዊ ዘዴ እንደሚረጋገጥ በ3.2.3. ተመልክቷል።

በዚህ መሠረት ዲስኩር አመልካቾቹ በእያንዳንዱ ውሁድ-አሀድና በሁለቱም ውሁድ-አሀዶች ውስጥ ባላቸው አገባብና አጠቃቀም ረገድ ሰባቱ እራሚ ባለሙያዎች ያላቸውን ውስጣዊ ስምምነት ለማሰየት የ"ክሮንባክ አልፋ (rα)የአስተማማኝነት ግምት" (Chronbac alpha reliability estimate) በጥቅም ላይ ውሏል። የ"ክሮንባክ አልፋ (rα) የአስተማማኝነት ግምት" በመሠረቱ የውስጣዊ አይለዋወጡነትን መጠን (magnitude of interanl consistency) ያመለክታል። የዚህም አስተማማኝነት ግምት ውጤት ዝርዝር ቀጥሎ በሠንጠረዥ 9 ቀርቧል። (የእያንዳንዱን ውሁድ-አሀድ (rα)ከአባሪ ለ-2.2 ፣ የእርማቱን ጥቅል ውጤት ደግሞ ከአባሪ ለ-4.1. ና ለ-4.2. ይመለከቷል)።

ሠንጠረዥ -9፣ በአራሚዎች ስምምነት ውስጥ ስላለው ውስጣዊ አይለዋወጡነት፣ የ"ክሮንባክ አልፋ (rα)የአስተማማኝነት ግምት" (Chronbac alpha reliability estimate for internal consistency in raters agreement)

ውሁድ - አሀዶች			
ውሁድ - አሀድ አንድ		ውሁድ - አሀድ ሁለት	
መለያ ቁጥር	rα	መለያ ቁጥር	rα
001/31	0.72	001/32	0.82
002/31	0.57	002/32	0.83
003/31	0.63	003/32	0.93
004/31	0.60	004/32	0.75
005/31	0.66	005/32	0.55
006/31	0.87	006/32	0.51
007/31	0.91	007/32	-
008/31	0.74	008/32	0.60
009/31	0.69	009/32	-
010/31	0.68	010/32	0.51
011/31	0.94	011/32	0.95
012/31	0.72	012/32	0.93
013/31	0.81	013/32	0.92
014/31	0.53	014/32	-
015/31	0.87	015/32	0.82
016/31	0.64	016/32	0.98
017/31	0.66	017/32	0.70
018/31	0.70	018/32	0.95
019/31	0.81	019/32	0.82
020/31	0.54	020/32	0.65
-		021/32	0.74

4.1.2. የዲስኩር እመልከቾቹ አገባባዊ ሥርጭት፤

4.1.2.1. (-)ግን (ግን፤ ነገር ግን፤ -ግን)

ለዚህ ጥናት ከተሰበሰቡት ተራኪ ውሁድ-እሀደች ውስጥ እንደታየው "ግን" ሁለት መልኮች አሉት፤ አንደኛው ብቻውን ገብቶ የሚገኝበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "ነገር" ከሚለው ምሥርት ስም ጋር እየተቀናጀ "ነገር ግን" በሚል ሐረግነት ራሱን ችሎ የሚገባበት መልኩ ነው። እነዚህ ሁለት ዓይነት መልኮች /ቅርጸች/ በዲስኩር ውስጥ በሚገቡበት የቋንቋ አውድ ተመሰሳይነትም ልዩነትም አለቸው። ተመሰሳይነታቸው ሁለቱም እንደአስፈላጊነቱ በዐረፍተንግግሮች መካከል ከሁለተኛው-ከተከታዩ-ዐረፍተንግግር መነሻ ላይ መግባታቸው ነው። "ነገር ግን" ከዚህ ውጭ ሲገባ አልታየም። ሌላው መመሰሰያቸው ደግሞ ሁለቱም በመከፈቻ ዐረፍተነገር መነሻ ላይና ተከታይ ዐረፍተነገር በሌለበት ሁናቴ በዐረፍተነገር መጨረሻ ላይ አለመገኘታቸው ነው።

እርግጥ በተዋስኦ መልክ (dialogue) በቀረበ ጽሑፍ ውስጥ ከእንደኛው ተራካቢ (conversationalist) ንግግር በእንጥልጥል በቀረ ዐረፍተነገር ውስጥ "ግን..." ተብሎ የሚተውበት ሁኔታ ሊያጋጥም (ለምሳሌ፤ 005/31 መ.10"... እታዘዛለሁ ግን... ብዬ" የሚለውን የመሠለ) ይችላል። በዚህ ጊዜ በ2.1.1. እንደተገለጸው ጥሩ እንባቢ አጠያቂ ጸሐፊ (interogating author) በመሆኑ (ዊደውሰን፤ 1984፤ ስዌልስ፤ 1990ን ያገናዝቢል) እንባቢው ከጠቀሳለ ወይም ከደራዊ እውቀቱ ወይም በአጠቃላይ "ስጥው" ከሆነው መረጃ (given information) ተነስቶ እሚልቶ እንዲያነበው ይጠበቅበታል። ይህ ሁኔታ ግን ከላይ ከጠቀስነው ምሳሌ በስተቀር በተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ በተደጋጋሚ ገብቶ አልታየም። ከዚህ ሌላ "ግን"፤ ብቻውን የሚገባባቸው በርከት ያሉ የቋንቋ አለባዎችና የቋንቋ ዐውደች አሉ። "ግን" ከዐረፍተነገሮች መካከል በተጨማሪ በሚከተሉት አካባቢዎች ይገኛል። በዐረፍተነገር ውስጥ ከጊዜ-ጠቀስ (temporal) ቃላትና ሐረጋት ቀጥሎ ለምሳሌ*፤ "በኋላ ግን"፤ "ለጊዜው ግን"፤ "ከዚያ በኋላ ግን"፤ "ከ...በኋላ ግን" ወዘተ.፤ ከስም ቀጥሎ ለምሳሌ፤ "ፍቅር ግን"፤ "እልግዝ ግን"፤ "እናቴ ግን" ና "ልጅቷ ግን" ወዘተ.፤ ከተውላጠ ስም ቀጥሎ ለምሳሌ፤ "እሷግን"፤ "እንቺ ግን"፤ "እኔ ግን"፤ ወዘተ. ከአዘማጅ ሐረጋት ቀጥሎ፤ ለምሳሌ፤ "የሚኖሩት ግን"፤ "ያሰብኩትን ግን"፤ ወዘተ፤ ከዲስኩር አመልካቾች-ከመስተፃምራን-ቀጥሎ ለምሳሌ፤ "ሆኖም ግን"፤ ከጥገኛ ዐረፍተነገሮች ቀጥሎ ለምሳሌ፤ ፍቅር ስንል ግን፤ "ከተሰካላት ግን"፤ "ስታነሰለት ግን"፤ "ከፈለግህ ግን"፤ ወዘተ፤ ከተውሰከግሶች ቀጥሎ ለምሳሌ፤ "ውስጥ ውስጡን ግን" "ላይ ላዩን ግን" ወዘተ.፤ እና ከልዩ ልዩ ቃላት ቀጥሎ ለምሳሌ፤ "ደሩ ግን"፤ ወዘተ. ይገባል። በነዚህ ዐውደች እየገባ የተለያዩ ተጠያቂዊ ዝምድናዎችን (በ4.2.1. የተገለጹትን) ያመለክታል።

---

*ምሳሌዎቹ በሙሉ ከተማሪዎቹ ጽሑፎች የተወሰዱ ናቸው።

4.1.2.2. (እ)ና* (ና፣ እና፣ እናም)

"(እ)ና" ከተሰበሰበው መረጃ እንፃር በሳዕላይ መልኩ ሁለት ቅርጸች አሉት፤ አንደኛውና ብዙ ጊዜ የሚታየው "ና" ብቻውን የሚገባበት ሁኔታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "እ"ን በመነሻው ላይ በማከል "እና" እየተባለ የሚፃፍበት ሁኔታ ነው። አልፎ አልፎ ግን ለተለያዩ ተግባራት "እና" በመድረሻው "ም" የተባለችውን መስተፃምራዊ ቅጣይ በማከል ይገባል (ዝርዝሩን በ4.2.2. ሥር ይመለከቷል)። "(እ)ና" በዐረፍተነገሮች መካከል፣ በሁለተኛው-በተከታዩ-ዐረፍተነገር መነሻ ላይና በዐረፍተነገር ውስጥ ከተለያዩ የቋንቋው አሳባዎች ጋር ሲገባ ታይቷል። በተሰበሰቡት ተራኪ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ በዐረፍተነገር ውስጥ ሲገባ የታየባቸው የቋንቋ ዐውዶች የሚከተሉት ናቸው።

በዐረፍተነገር ውስጥ ከአዛማጅ ሐረጋት** ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "...የፈራና..."፣ "...የምተኛበትና..."፣ "...የሚረዱትና..."፣ "...የሚገፋፉኝና..." ወዘተ.፣ ከመስተዋድዳዊ ሐረግ ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "...በምትገበበትና..."፣ "...በምትወጣበትና..."፣ "...ከሚያውቁትና..." ወዘተ.፣

ከጥገኛ ዐረፍተነገር ቀጥሎ፣ ለምሳሌ፣ "...መርጦና..."፣ "...ይልና..."፣ "...ሳይመከና ..."፣ "...ስለቆጨኝና..." ወዘተ. ይገባል። "(እ)ና" ከሌሎች ዲስኩር አመልካቾች መስተፃምራን ጋር ሲገባ በተሰበሰበው መረጃ ውስጥ አልተገኘም። ከ"ይሁን" ጋር ሲቀናጅ "ይሁንና" የሚል ዲስኩር አመልካች ያስገኛል። (ዝርዝሩን በ 4.2.2. ይመለከቷል)። ከዚህ ውጪ ግን በመከፈቻ ዐረፍተነገር መነሻ ላይ አይገባም። በዐረፍተነገር መጨረሻ ላይ ግን ሊገባ ይችላል። (ዝርዝሩን በ4.2.1. ይመልከቱ)። በዚህ ጊዜ ከድምፅ ቅላፄ ጋር የተያያዘ በሕሪይ ይኖረዋል ለብቻው መጠናት ስላለበት ይህ ጥናት አይመለከተውም።

---

* (እ)ና በርከታ አገባብና አገልግሎት ካላቸው መስተፃምራን አንዱ ነው። ስለዚህ ሁሉንም በዚህ ጥናት ማየት ባለመቻሉ በዐረፍተነገር ውስጥ በስሞች ወይም በ"ስሐ"ዎች መካከል በቅጽሎች ወይም በቅጽላዊ ሐረጉች መካከል፤ በመስተዋድዳዊ ሐረጉች መካከል ወዘተ. ያሉትን አገባቦችና አገልግሎቶች ይህ ጥናት አላካተታቸውም። የተመለከታቸውም በሙሉ በዐብይ ሐረግ (clauses) መካከል ማለትም በጥገኛ ዐረፍተነገሮችና በዐረፍተነገሮች መካከል ያሉትን አገባቦችና አገልግሎቶች ብቻ ነው።

** ስለ አዛማጅ ሐረግ ዝርዝር ገለፃ በ ዮ ይማም 1987 ዓ.ም ይመልከቱ።

4.1.2.3. (-)እንጂ (ይሁን እንጂ፣ እንጂ፣ -እንጂ)

ከላይ እንደየናቸው ዲስኩር አመልካቾች፣ "እንጂ"ም ሁለት ቅርጸች እንዳሉት መረዳት ተችሏል። እነሱም "እንጂ"ና "ይሁን እንጂ" ናቸው። "ይሁን እንጂ" ራሱን ችሎ በዲስኩር አመልካችነት የሚገኘው በዐረፍተነገሮች መካከል፣ በሁለተኛው-በተከታዩ ዐረፍተነገር መነሻ ላይ ነው። ከዚህ ውጪ በዐረፍነገር መድረሻ ላይ፣ በመከፈቻ ዐረፍተነገር መነሻ ላይ ወይም በዐረፍተነገር ውስጥ በሌሎች የቋንቋ አላባዎች ላይ ሲገባ አልታየም።

"እንጂ" ብቻውን ግን እንደ "ይሁን እንጂ" በዐረፍተነገር መካከል ከመገኘት-ከመግባት-በተጨማሪ በዐረፍተነገርም ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ሊገባ ታይቷል። "እንጂ" በዐረፍተነገር ውስጥ ከሰም ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "መጽናናት እንጂ" "ትዕዛዝ እንጂ"፣ "መቁረጥ እንጂ"፣ ከመስተዋድድ ሐረግ ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "ከልጁ ቤት እንጂ" ፣ "በአጋጣሚ እንጂ" ወዘተ.፣ ከጥገኛ ዐረፍተ ነገር ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "ብዬ እንጂ"፣ "አዲስ አበባ ውስጥ ይሁን እንጂ" "በፍላ ጉቴ ይሁን እንጂ" ወዘተ.፣ ከአዘማጅ ሐረግ ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "የዋለ እንጂ" ወዘተ. ይገባል። ከዚህ ሌላ ግን "እንጂ"ም ሆነ "ይሁን እንጂ" ከሌሎች መስተፃምራዊ ዝምድናን አመልካች ከሆኑ ቃላትና ሐረጋት ጋር ሲገቡ በመረጃችን ውስጥ አልታዩም። ከላይ በዘረዘርናቸው አካባቢዎች የሚያመለክቷቸው ተጠየቃዊ ዝምድናዎች በ4.2.3. ተዘርዝረዋል።

4.1.2.4. ስለዚህ (ስለዚህ፣ ስለዚህም)

ይህ ሐረግ መስተዋድዳዊ ሐረግ (ስለ + እዚህ) በመሆኑ በዐረፍተነገር ውስጥ መስተዋድዳዊ ሐረግ የሚፈጽመውን ሰዋሰዋዊ ሙያ ሊፈጽም ይችላል። ሊገኝ የሚችለውም ከግሰዊ ሐረግ (ግሐ) ጋር ሊሆን ይችላል (በዴ 1987 ይመለከቷል)። ይህን ሙያውን ጥናቱ አይመለከትም። ጥናቱ የሚመለከተው ከዚህ ሰዋሰዋዊ ሙያ ውጪ ያለውን ዲስኩራዊ ተግባር ይሆናል። በዲስኩር አመልካችነቱ በዐረፍነገር ውስጥ ከተለያዩ የቋንቋ አላባዎች ጋር እየገባ መነገር አይችልም። ስለሆነም የተዘወተረ ቦታው በዐረፍተነገሮች መካከል፣ በሁለተኛ-በተከታይ-ዐረፍነገር መነሻ ላይ ብቻ ነው። በዚህ ቦታ ሲገኝ ብቻ ነው ዲስኩር አመልካች ሊሆን የሚችለው።

"ስለዚህ" በዲስኩር ውስጥ አንድም ብቻውን ምንም ሌላ የቋንቋ አካል ሳይጨምር፣ አልያም "ም"ን መስተፃምራዊ ቅጣይ በማከል ሊነገር እንደሚችል ከተማሪዎቹ ውሁድ-አሀዶች መረዳት ተችሏል። ብቻውንም ሆነ ከ"ም" ጋር ሲገባ የሚያመለክተውም ተጠየቃዊ ተዘምዶ በ4.2.4. ተዘርዝሯል።

4.1.2.5 ከዚያ (-) (ከዚያም፣ ከዚያ በኋላ...)

"ከዚያ" የተሰኘው ዲስኩር እመልከች ከዲስኩር እመልከችነቱ በተጨማሪ በመስተዋድዳዊ ሐረግነቱ (ከ-እዚያ) የሚፈጽመው ሰዋስዋዊ ሙያ ይኖራል። የሚገኘውም በ"ግሑ" ውስጥ ይሆናል። (በዬ 1987 ይመልከቱ)። ከላይ ለ"ስለዚህ" እንደጠቀስነው ሁሉ ይህ ጥናት የሚተነትነው በዚህ ሰዋስዋዊ ሙያውና ሥፍራው እይደለም። "ከዚያ" በዚህ ጥናት የሚተነተነው ከዚህ ሰዋሰዋዊ አገልግሎቱ ውጪ በሚገኝበት ሁኔታና አጠቃቀም አንፃር ነው።

"ከዚያ" በሁለት መልክ በዲስኩር ውስጥ ሊገኝ ይችላል፤ አንደኛው በዐረፍተነገሮች መካከል፣ በሁለተኛው-ከተከታዩ-ዐረፍተነገር መነሻ ላይ፣ ሁለተኛው ደግሞ በዐረፍተነገር ውስጥ ከተለያዩ የቋንቋ አለባዎች ጋር በመግበት የሚያገለግልበት ሁኔታ ነው። በዐረፍተነገር መካከል ሲገኝ እንድም ብቻውን "ከዚያ" ምንም ሳይጨምር፣ አለበለዚያም ጊዜ-ጠቀስ ሁኔታዎችን ከሚያመለክቱ ቅጣሮች ወይም ቃሎች ጋር ለምሳሌ:- ከዚያም፣ ከዚያ በኋላ፣ ከዚያም በኋላ፣ ወዘተ. በመግበት ያገለግላል። በዐረፍተነገር ውስጥ ደግሞ "ከዚያ" ከስሞች ቀጥሎ ለምሳሌ፣ አትክልት መኸትከትና ማጠጣት ከዚያም... ወዘተ. ሊገባ እንደሚችል መረጃዎቹ ይጠቁማሉ።

4.1.2.6. ደግሞ (ደግሞ፣ ደግሞም)

"ደግሞ" በቅርጹ ሲታይ የ"ደገመ" ግስ በዝ አንቀጽ (ቅርጽ) ነው (ይትባረክ 1966 ዓ.ም፤ ኃይሉ 1966 ዓ.ም፤ በዬ 1987 ዓ.ም. ያገናዝቢል)። በዚህ ትንተና ውስጥ ከመዋቅራዊ ቅርጹ አኳያ እንመለከተውም። ተግበሩም ይህንን እንድናደርግ አይጋብዘንም። ስለዚህ በቅርጹ ከያዘው ሰዋስዋዊ አገልግሎት ውጪ ካለው ዲስኩራዊ ተግባር አኳያ ብቻ የሚታይ ይሆናል። "ደግሞ" እንደሌሎቹ ዲስኩር አመልካቾች በዐረፍተነገሮች መካከልና በዐረፍተነገሮች ውስጥ ይገበል። በዐረፍተነገር መካከል ሲገባም ከሁለተኛው-ከተከታዩ-ዐረፍተነገር መነሻ ላይ ነው የሚገባው። በዚህ ሁኔታ ግን እንደ "ስለዚህ" ወይም እንደ "ከዚያ" በመነሻ ቦታ እንድም ብቻውን ይገበል፤ አለዚያም ከሚከተሉት ጋር አብሮ ይገኛል።

በሁለተኛው-በተከታዩ-ዐረፍተነገር ብቻውን ከልተገኘ ከስሙ ወይም ከ"ስሑ"ው ቀጥሎ ለምሳሌ:- "ቋንቋ ደግሞ..."፣ "እናቴ ደግሞ..." ወዘተ.፣ ከመስተዋድዳዊ ሐረግ-መሐ-ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "በተለይ ደግሞ..."፣ "በሌላው ጊዜ ደግሞ..."፣ "ለህዝቡ ደግሞ..." ወዘተ.፣ ከተውላጠስም ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "እሷ ደግሞ"፣ "ይህ ደግሞ ... "እነሱ ደግሞ ..." ወዘተ. ይገበል። በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሲገኝም ከላይ በተዘረዘሩት የቋንቋ አለባዎች ላይ በተመሣሣይ ሁኔታ ይገበል። ሆኖም አቀማመጡ "... ደግሞ..." ነው የሚሆነው። ከላይ ከተዘረዘሩት ውጪ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ከአዘማጅ ሐረግ ቀጥሎ ለምሳሌ "...የሚችሉት ደግሞ...፣ "...የተወሰኑት ደግሞ ..."ወዘተ፣

ከልዩ ልዩ ተውሰክ ግሳዊ ቃላት / ሐረጋት/ ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "... ማታማታ ደግሞ ..."፣ "... እንደገና ደግሞ..."፣ ወዘተ.፣ ከቦዘዊ ሐረግ ቀጥሎ ለምሳሌ፣ "...ይበስ ብሎ ደግሞ ..." ወዘተ. ይገበል᎓ ከነዚህ የቋንቋ ዐውዶች ውጪ በሌሎች ቦታዎች ሲገበ የሚያሳይ መረጃ ከተሰበሰቡት ጽሑፎች ውስጥ አልተገኘም᎓

4.1.2.7. <u>–የተነሳ</u>

ይህ ዲስኩር አመልካች ቅርጹ እንደሚያመለክተው አዘማጅ ሐረግ ነው᎓ ከሌሎቹ የሚለየው ዐረፍተነገራዊ/አዘማጅ ሐረግ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ራሱን ችሎ በየትኛውም ቦታ ሊገበ አለመቻሉ ጭምር ነው᎓ በአዘማጅ ሐረግነቱም መሪ ሊኖረው ይችላል (በዱ 1987 ያመሳክሯል)᎓ ሆኖም በዲስኩር አገልግሎቱ እነዚህን ሰዋሰዋዊ ነገሮች እንዲያሟላ አይጠበቅበትም᎓ እንዲያሟላ ከተደረገም ዲስኩር አመልካችነቱ ይቀራል᎓ ለምሳሌ፣ "ታሞ የተነሳ ሰው..." እንዲሉ᎓ ስለሆነም በዲስኩር አመልካችነቱ ያለመሪ ከሰዋሰዋዊ አገባቡና አገልግሎቱ በተለየ ሌላ ዝምድናን እንዲያመለክት ሆኖ ሲገበ ብቻውን ስለማይነገር ከምን ከምን ቀጥሎ እንደሚገበ ቀጥለን እንመለከታለን᎓

"–የተነሳ" በዐረፍተነገሮች መካከል ሲገበ "በዚህ..."፣ "በዚህም..."፣ "ከዚህ..."፣ "ከዚህም..."፣ ከተሰኙት መስተዋድዳዊ ሐረጐች ቀጥሎ ይገበል᎓ እነዚህ መስተዋድዳዊ ሐረጐችም ከመስተዋድድና––"በ" ና "ከ"–– ጠቋሚ ከሆነው (referential) ከ"እዚህ" የተመሠረቱ ናቸው᎓ በዐረፍተነገር ውስጥ ሲገበ ደግሞ እንደዚሁ ከልዩ ልዩ ሰዋሰዋዊ ቃላትና ሐረጋት ከተመሠረቱ መስተዋድዳዊ ሐረጐች ቀጥሎ ይገበል᎓ ለምሳሌ፣ "...በጣም ከመዋደዳችን የተነሳ..."፣ "...ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ..."፣ "...በመቂረጡ የተነሳ..."፣ "...ከለው ፍቅር የተነሳ..." ወዘተ.᎓ እነዚህን "መሐ"ዎች ብንመረምራቸው ሁሉም መስተዋድዶቹን "በ–"ንና "ከ–"ን ይዘዋል᎓ የሚለዩበት ሁኔታ ቢኖር መስተዋድዶቹ የገቡበቸው–የሰቢቸው–ስሞች ወይም "ስሐ"ዎች ናቸው᎓ ማለትም በእርዕሰት ወይም በኢውሱን ቅርጽ– "መሆን፣ መቂረጥ–" ወይም በአዘማጅ ሐረግ– "የአለው ፍቅር" –ላይ ነው የገቡት᎓ ስለዚህ የ"–የተነሳ"ን አገባብ ከአሉት የጽሑፍ መረጃዎቻን አኳያ ብናጠቃልለው፣

[መስተዋድድ + ከ– በ– አርእስት– አዘማጅ ሐረግ– +(–ም)]+–የተነሳ]...
አመልካች ተውላጠ ስም

የሚለውን ይመስላል᎓

4.1.2.8. ወይ(ም/ስ) (ወይ...፣ ወይም፣ ወይስ)

በዚህ ጥናት የሚተኮርበት ሌላው ዲስኩር አመልካች "ወ ይ(ም/ስ)" ነው ። "ወይ(ም/ስ)" የቃሉ ሥር "ወይ" ነው? ወይም "ወይም" ወይም "ወይስ" ነው? የሚለው ጥያቄ መጠናት ያለበት ጉዳይ ይመስላል። ለዚህ ጥናት ግን "ወይም" የሚለውን ቃል እንደዋና በመውሰድ ሌሎቹን ደግሞ የዚህ ተውሳሮች በማድረግ ለማየት ተሞክሯል። "ወይም" በአብዛኛው በአረፍተነገር ውስጥ የመግበት ልማድ ቢታይበትም በዐረፍተነገሮች መካከልም ይገባል። ስለዚህ በሁለቱም ሁኔታዎች በዐረፍተነገር መካከልና ውስጥ "ወይም" የሚገባባቸውን የቋንቋ አሳቦች ቀጥለን እንመለከታለን።

በዐረፍተነገር መካከል ሲገባ በሁለተኛውና በተከታዩ ዐረፍተነገር መነሻ ላይ በ"ወይም" ወይም በ"ወይስ" ቅርጹ ይገባል። ለምሳሌ "...ምን ይለኝ? ወይስ ይገለኝ"፣ "...ይያዘል ወይም ይጠመዳል" ወዘተ.። ከዚህ ውጪ ባሉ ሌሎች አካባቢዎች ማለትም በዐረፍተነገር ውስጥ ሲገባ፣ ከስም ወይም ከ"ስሑ" መካከል፣ "...ወንበር ወይም መቀመጫ..."፣ "...ችግር ወይም መከራ..."፣ "...ፈቃድ ወይም ትዕዛዝ..."፣ ወዘተ.፣ ከእዚማኛ ሐረጉች መካከል ሲገባ፣ "...የሚያጋጥመው ወይም የሚደርስበት..."፣ "...የደረሰብንን ወይም የደረሰልንን..." ወዘተ.፣ ከመስተዋድዳዊ ሐረጉች መካከል፣ "...በንግግር ወይም በጽሑፍ..."፣ "...ከቦታ በታ ወይም ከከፍለ ሀገር ከፍለሀገር..."፣ "...ለእራት ወይም ለእምስት ዓመት..." ወዘተ.፣ ከቅጽሎች ወይም ከቅጽላዊ ሐረጉች መካከል "...የቄስ ወይም የቆሎ ትምህርት ቤት..."፣ "...የቃል ወይም በቃል የሚነገር ትምህርት..." ወዘተ. ይገባል። ከዚህ ሌላ በ"ወይ" ቅርጹ በዐረፍተነገር መነሻ ላይ ሊገባ ይችላል። ሆኖም ብዙ ጊዜ ከመረጃዎቻችን እኪያ የመደገም ባህርይ "-ወይ...፣ ወይ..."-ይታይበታል። ለምሳሌ "እንደንዲ ወይ እናቴ ሌላ ናት፣ ወይ አባቴ ሌላ ነው..." እናም ወይ አባቴ የተባለው ሰው ወይ እናቴ የተባለችው ሴት..." ወዘተ.፣ ከነዚህ ምሳሌዎች በተጨማሪ የምንገነዘበው ከ"ወይ" ቀደም ብሎ መስተፃምሩ "እናም"ና ሌሎች ሊገቡ እንደሚችሉ ነው። በውሁድ-አሀዶቹ ውስጥ ያላቸው አገልግሎት በ4.2.2. ና በ4.2.8. እንደ ቅድሞናቸው ይዘረዘራል።

4.2 የዲስኩር እመልከቾች ዝርዝር ዲስኩራዊ የተግባራት

4.2.1 "የ(ነገር) ግን" ተግባራት

"ግን" ብቻውንም ሆነ ከ"ነገር"ጋር በውሁድ-አሀድ ውስጥ በተለያየ ቦታ እንደሚገባ ከላይ በ4.1.2.1. ተገልጿል። በነዚህ የተለያዩ ቦታዎች በሚገባበት ጊዜ የሚፈጽመው ተግባር እንደማንኛውም ዲስኩር እመልከች በሁለቱ ውሁድ-አሀድ አረፍተነገሮች መከከል ያለውንና ፀሐፊው እንዲኖር የፈለገውን ዝምድና ለእንባቢው ግልጽ ማድረግ ነው (ናታል፣ 1982፤ ኑናን፣ 1993)።

"ግን/ነገርግን" በ2.2.1. እንደተረገጸው በልማዳዊ የአማርኛ ሰዋሰው መፃህፍት ውስጥ እፍራሽ መስተፃምራን ተበሎ ከሚታወቀው እንዱ ነው። ይህ በስዋስው ሊቃውንት የተሰጠው ግለፄ በተለያዩ ውሁድ-አሀዶች የተለያዩ የቋንቋ ዐውዶች ውስጥ በሚገባበት ጊዜ ከሚያሰገኛው ትርጊሜና ከሚያመለክተው ተጠየቃዊ ዝምድና አንፃር ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ሆኖ አልተገኘም። እንዲያውም ከተሰበሰበው መረጃ አንፃር የተለያዩ ዝሙድናዎችን በሚያመልክትበት አገባቡ የጭብጥ አደረጃጀቱንና ውቅሩን-ጭው-የመለዋወጥ እዝግሚያ ስለሚታይበት ከ"ጭው"ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ይመስላል።በዚህም መሰረት ከተግሪያች ውሁድ-አሀዶች ውስጥ በተወሰዱ አስረጂያች አማከይነት የ"ግን"ን የተለያዩ ተግባራት ቀጥለን እንመለከታለን።

4.2.1.1.ልየታ* (Adversative)

"ግን"በአጠቃላይ መልኩ ሊታይ ከእንግሊዝኛው"but"ጋር ተነፃፃሪ ይመስላል። የእንግሊዝኛው "but" ሀሊዲይና ሃሰን(1976)እንደገለጹት ከሚገመተው ወይም ከሚጠበቀው ሀሳብ ውጪ (beyond expectation) የሆነ ሀሳብ ከመጀመሪያው ዐረፍተነገር ቀጥሎ በመጣው ዐረፍተነገር መገለጹን የሚያመለክት ቃላዊ ዲስኩር እመልከች ነው። ይህ ከሚገመተው ወይም ከሚጠበቀው ሃሳብ ውጪ የሚቀርበው ሃሳብ የሚገባው ከመጀመሪያው ጋር ባለው አንድ ዓይነት ዝምድና በመሆኑ በመከከላቸውም የሚገባው "ግን" የሚያመለክተው (ይፋ የሚያደርገው) ይህንኑ ዝምድና ነው። በሌላ አበባል መጀመሪያ በቀረበው ዐረፍተ ነገር በተሰጠው መረጃ /ሐሳብ/

---

* ልየታ የሚለው ስያሜ ምናልባት በቀደምት ስዋስው ሊቃውንት ሥራዎች ውስጥ ከተጠቀሰው "እፍራሽ " ከሚለው ስያሜ ጋር እንድ[ጭ]ሊባል ይች ል ይሆናል። ሆኖም "እፍራ" የሚለው ስያሜ ሁልጊዜ አያንታ-አሉታ፣አሉታ-አያንታ ቅንጂት የሚጋብዝ ዓይነት ስለሚመስልና ለሁሉም የ"ግን" ተግባራት የተሰጠው ስለሆነ እንዲለወጥ ተደርጊል።

መነሻነት የሚጠበቅ ወይም የሚገመት ሀሣብ ይኖራል። ከዚያ ግምት ውጪ የሆነ ግን ደግሞ፣ ርዕሰ ነገር /topic/ ያልለመጠ ሀሳብ ከተከታዩ ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ተያይዘ ይገለፃል። በዚህም መልክ ከሚፈጠሩት ዝምድናዎች እንዱ የልየታ ዝምድና ነው ለማት ይቻላል።

(1) በሌሳ በኩል ለእናትህ ሐወልት ለማሠራት ሀሣብ አለህ የተባለውን ሰምቻለሁ። ነገር ግን ለእናትህ አያስፈልግም። የተኛችበት ሰጥን ይቆረቁራታል ብለህ እንደሆነ አታስብ....(007/31)*

እዚህ ላይ እንደምንመለከተው "ነገር ግን" የገባው በሁለቱ ውሁድ-አሀድ ዐረፍተ ንግግሮች መሀከል በሁለተኛው መጀመሪያ ላይ ነው። በዚህም አገባቡ በመጀመሪያው ዐረፍተ ንግግር ከሚገመተው ሃሳብ የሁለተኛው ዐረፍተ ንግግር ሀሣብ ማፈንገጡን ያመለክታል። በመጀመሪያው ዐረፍተነገር መሠረት የሚጠበቀው ሀሣብ "ሀሰቡ በጣም ተገቢ ነው በቶሎ ልታደርገው ይገባል" የሚል ዓይነት ሲሆን በሁለተኛው ዐረፍተንግግር የተገለጸው ግን ይህን ግምት የሚያጨልም ወይም የሚጠበቀውን ሀሳብ የሚክድ ነው። ስለዚህ በሁለቱ ዐረፍተ ንግግሮች መካከል ያለውን የ"ልየታ" ዝምድና "ነገር ግን" በይፋ ገልጿል። ተነጋሪው (The addressee) በሚያነብበት ጊዜ "ነገር ግን" የሚለውን ሐረግ ላይ ሲደርስ በሁለቱ ዐገፍተ ንግግሮች መከከል ሊኖር የተፈለገው ዝምድና "ከሚገመተው ወይም ከሚጠበቀው ውጪ" (ሀሊዲይና ሀሰን፣ 1976) እንደሆነ ይረዳል። በዚሁ መሰረትም ንባቡን ይቀጥላል፤ ምክንያቱም (በ2.1.1.እንደተገለጸው) ጥሩ አንባቢ "አጠያቂ ጸሐፊ" ስለሆነየፀሐፊውን ሐሳብ የመገመትና በዲስኩር አመልከቹም ምን ዓይነት ዝምድና ለማመልከት እንደተፈለገ ፈልፍሎ የመረዳት ሀላፊነት አለበት።

በሁለቱ ዐረፍተንግግሮች መካከል ያለው የ"ልየታ" ዝምድና በ"ነገርግን" አማከይነት ይፋ ሆነ ስንል ለሁለቱም የውሁድ-አሀድ አሳቦች ግጥምጥም መሆን አስፈላጊው እሱ ብቻ ነው ማለታችን አይደለም። ከላይ በ2.1.3. እንደተገለጸው ሁለቱ የውሁድ-አሀድ አከሎች በተገቢው ዐውድ ውስጥ በመነገራቸው ለተገቢው ተነጋሪ (አንባቢ) በመገለፃቸውና ተነጋሪውም ስለሁኔታው ደራዊ ዕውቀት ያለው በመሆኑ ግጥምጥም ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል (ዊይውሰን፣ 1979፤ ኑናን፣ 1993)። ይሁንና አዲሱ ሐሳብ (መረጃ)ና "ስጥው" (given) የሆነው ሀሰብ በየተነገረባቸው ዐረፍተንግግሮች መከከል ያለው ዝምድና ከላይ እንደተጠቀሰው በላዕላይ መልኩ ይፋ የሆነው በ"ነገርግን" አማከይነት ነው።

---

* በምሳሌዎች በስቀኝ ትይዩ በቅንፍ ውስጥ የሚቀመጠው ቁጥር የምንጩ ውሁድ ከድ (መለያ) ቁጥር ነው።

ከ"ጭው" አኳያ ሲታይ በምሳሌ (1) የቀረበው ውሁድ-አሀድ የሚከተለውን ይመስላል። በአብዛኛው የ"ልየታ" ዝምድና የታየባቸው የውሁድ-አሀድ አሳባዎች (ለምሳሌ.008/31: መ11-1200/31፤ መ4-5 003/32: መ12) የ"ጭው-1"ን አወቃቀር የሚከተሉ ይመስላሉ። በ2.1.2. እንደተመለከተው "ጭው-1" በጭብጥ አወቃቀር ረገድ በመጀመሪያው ውሁድ-አሀድ ዐረፍተንግግር (ዐረፍተነገር) ሀተታ-ጭብጥ/እንቀጽ (አ) ውስጥ ከተጠቀሱት የቋንቋ አሳባዎች አንዱ የተከታዩ ውሁድ-አሀድ ዐረፍተንግግር/ ዐረፍተነገር-ጭብጥ ሆኖ የሚወቀርበት "ጭው" ነው (ዴሄሽ፣ 1974፤ ጋሰር፣ 1984፤ ማክርቲ፣ 1991)። በዚህ መሠረት የ"መከድ" ዝምድና ይህን መዋቅር በአብዛኛው የሚከተል ይመስላል። እስኪ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

(2) ...ከተማዋ ከ ጉንደር ከተማ በ21 ኪሎሜትር እርቃ የምትገኝ በሠንሠለታማ ተራራ የታጠረች ውብ ከተማ ናት። ዳሩ ግን የከተማዋ መልክአ ምድር እቀማመጥ ለእድገቷ ከፍተኛ እንቅፋት በመሆኑ እስከሁን ድረስ ባለችበት የምትጂዝ ድንቅ ዮ ከተማ ናት።...(006/32)

ምሳሌ (2) የሚያመለክተው ከሳይ ምሳሌ (1) የተጠቀሰውን የ"ልየታ" ዝምድና ነው። በዚህም "ግን" የገባበት ሁለተኛው ዐረፍተንግግር ከመጀመሪያው መለየቱን በዚህም የሚጠበቀውን ሀሳብ መከዱን ወይም ማጠፉን መረዳት ይቻላል። እዚህ ላይ አዲሱ መረጃ "የከተማው መልክአምድር ለእድገቷ እንቅፋት መሆኑ" ሲሆን ስጥው የሆነው ደግሞ በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር ውስጥ "በሠንሰለታማ ተራራ መታጠሯ ውብ እንደደረጋት" የተገለጸው ሃሳብ ነው። "የከተማው መልክአምድር" የሚለው የሁለተኛው ዐረፍተንግግር ጭብጥ ደግሞ በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር እንቀጽ ውስጥ የተገለጸ ነው። ስለዚህ ከጭብጣዊነት እንፃር በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር የእንቀጽ አካል የነበረው በሁለተኛው ዐረፍተንግግር የጭብጥ ቦታ እንዲይዝ ተደርጓል።

የምሳሌ (1) እና (2) ጭው የሚከተለውን ምስል ይመስላል። ዝርዝሩ በ2.1.2. "ጭው-1" የተገለጸው ነው።



ሥዕል-2፤ የ(1) እና(2) ጭብጣዊ መዋቅር

4.2.1.2. ንፅፅር (Contrast)

ከ"ግን" ተግባራት ሁለተኛው በውሁድ-አሀድ አለባዎች መካከል ያለውን የ"ንፅፅር" ዝምድና መግለጽ ነው። እንደምሁራኑ ትንታኔ ንፅፅረ የሁለት ነገሮችን ወይም አካላትን በውድድር ወይም በንፅፅር መልክ መቅረብ የሚያመለክት የዝምድና ዓይነት ነው (ሀሊዴይና ሀሰን፣ 1976፤ ናታል፣ 1982፤ ሃች፣ 1992)። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

(3) ...እንድ ያልተማረ ሰው እምጥተን ስለእንድ ነገር ተናገር ወይም በጽሁፍ እቅርብ ብንለው እንደተማረ ሰዎች አድር ጉ እቀለጥፎ ቀለልና ግልጽ በሆነ መንገድ ሊያቀርብልን አይችልም። ነገር ግን በደንብ የተማረውን ሰው ላልተማረው ሰው የሰጠነውን እንዲሰራና በቃልም ሆነ በጽሑፍ እቅርብ ብንለው እጠር ባለና ቀላል በሆነ መንገድ ሊያቀርብልን ይችላል። (015/31)

"ምሳሌ (3) እንደሚያሳየው ከ"ነገርግን" በፊት የተገለጸው ሀሳብ "ያልተማረ ሰው" ስለእንድ ነገር በቃል ወይም በጽሑፍ እቅርብ ቢባል "እንደተማረ ሰዎች" ሊያቀርብ እለመቻሉ ነው። ከዲሰኩር እመልከቹ ቀጥሎ የመጣው ደግሞ "ላልተማረው ሰው እንዲሠራ የተሰጠውን ሥራ ለተማረው ሰው ቢሰጠው እቀለጥፎ በቃል ወይም በጽሑፍ ማቅረብ እንደሚችል" የሚገልጸው ሀሳብ ነው። ከዚህ የምንረዳውም በነዚህ በሁለቱም ዐረፍተንግግሮች ውስጥ ጭብጣዊነት ባለቸው "እንድ ያልተማረ ሰው "ና" በደንብ የተማረው ሰው" በተሰኙ ሀረጉችና ሐረጉቹም በሚወክሏቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለው "የመማርና ያለመማር ውጤት" በንፅፅር መልክ የቀረበበት ውሁድ-አሀድ መሆኑን ነው። በመሆኑም የ"ነገር ግን" አገባብና አገልግሎትም ይህንኑ የንፅፅር ዝምድና ማመልከት ነው።

ከጭው እንፃር ምሳሌ (3)ን ያየነው እንደሆነ በ"ነገር ግን" ዝምድናቸው የተመለከከቱት ሁለት የውሁድ-አሀድ አለባዎች ለየራሳቸው ጭብጦች አሏቸው። እነዚህም የተነፃፀሩት አካላት የተወከሉባቸው ሐረጉች ናቸው። ይሁንና፣ ሁለቱ ዐረፍተንግግሮች በንፅፅር መልክ ቢቀርቡም ከገቡበት አጠቃላይ አውድ አኳያ በተለያየ ሁኔታ የሚገልጹት ዐብይ ጭብጥ አለ ማለት ነው። ይህም ዕሰቤ በ2.1.2.የተለገጸው "ጭው-3" አንድን ዋና ጭብጥ ወይም የ"ጭብጥ ስብስብ" በተለያዩ ምሥርት ጭብጦችና አንቀጾቻቸው የመግለጽ ዕሰቤ ነው (ዴኔሽ፤ 1974፤ በተጨማሪ የጋሰር 1984ን "ጭው-1" ያገናዝቧል)። በዚህ ዓይነት በ"ግን" የሚገለጸው የንፅፅር ዝምድና ከመረጃዎቻችን አንፃር ይህንኑ "ጭው-3" የሚከተል ይመስላል። እንዳንድ ጊዜ በሥዕላዊ መግለጫ-1 ከተለገለጹት "ጭው"ዎች "ጭው-3"ንና "ጭው-1"ን በማጣመር ንጽጽሩ የሚገለጽበት ሁኔታ የሚኖር ይመስላል። ይህን ዓይነት አወቃቀርም ጋሰር (1984) በጥናታቸው እንዳጋጠማቸውና ይህም በአማርኛ ቋንቋ

ዐረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ በህሪያት ምክንያት እንደሆነ ገልጸዋል። እስቲ የሚከተለውን ምሳሌ ደግሞ እንይ፤

(4) ...ዘምቼም ለመጀመሪያ ጊዜ በጉጂም ብርሸለቆ ግሥልጠኛ ውስጥ ስሠለጥን ቆይቼ የተመደበልኝን የሥልጠና ጊዜ ከጪረስኩ በኋላ ጊደኞቼ ወደ ግንባር ሲላኩ እኔ ግን በዚያው ግሥልጠኛ ውስጥ ለቢሮ ፀሐፊ ለሃኪም ለከበድ መሣሪያ ትምህርት ተብ ዮ...ቀረሁኝ።(021/32)

በዚህ ምሳሌ መሠረት የ"ግን"አገባብ ንጽጽራዊ ዝምድናን ግመልከት ነው። "የጊደኞቹን ወደ ግንባር መላክ"እና የተራኪውን"በዚያው ግሥልጠኛ ውስጥ መቅረት"ያነፃፅራል። በዚህ ሁኔታ ከእንባቢው ገጠመኝና ከለው ደራዊ ዕውቀት አኳያ የሚጠበቀው ሃሳብ ለመዝመት የሰለጠነ ሰው ወደ ግዳጅ በታ መላኩንና ተራኪውም ከስልጠናው እንፃር ይህንኑ ግሟላት እንዳለበት ነው። ይሁንና ከ"ግን" በኋላ በተጠቀሰው ምክንያት ተራኪው ሊቀር ችሏል። ይህም ከተጠቀሰው ሃሳብ ወይም ግምት መለየትን የሚያሳይ ነው። ከላይ በምሳሌ (4) የቀረበው ውሁድ-እሀድ በእንድ ረጅም ዐረፍተነገር የቀረበና በርከት ያሉ ጉዳዮች የተገለጹበት ዓረፍተንግግር ነው። ስለዚህ እንደህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ከያዙት ሃሳብ አኳያ ራሳቸውን ችለው በ"ጭው" ሊገለጹ የሚችሉትን የውሁድ-እሃዱ አለበያች መለየት ይጠቅማል። ይህ ከሆነ ደግሞ ውሁድ-እሀዱ በእራት ወይም በሦስት ሊከፈል የሚችል ይመስላል። "ሥልጠና፤ የሥልጠና ጊዜ፤ ወደ ግንባር መላክና በግሥልጠኛ መቅረት" አለዚያም "ሥልጠናና የሥልጠና ጊዜ፤ ወደ ግንባር መላክና በግሥልጠኛ መቅረት" ሊሆን ይችላል። የእራቱን መሠረት በግድረግ በሥዕላዊ መግለጫ ብናቀርበው የሚከተለውን ይመስላል።



<u>ሥዕል-3፤</u> የምሳሌ 4 ጭብጣዊ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ

ሥዕላዊ መግለጫው እንደሚያመለክተው አራት ጭብጥ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት ወይም ሐረጋት አሉ። የመጀመሪያው "ዘምቼም" (እኔ) (ጭ1)፤ ሁለተኛው "የተመደበልኝን"(እኔ)ጭ2፤ ሦስተኛውም "ጊደኞቼ"(የእኔ) (ጭ3)፤ አራተኛ ደግሞ እኔ(ጭ4) ናቸው። ሁሉም ከተራኪው "ምልመላ፤ ሥልጠናና ግዳጅ" ጋር የተያያዙ ስለሆኑ የዲስኩሩን ርዕሰ-ነገር (Topic) ወይም [ጭ] የሚገልጹ ናቸው። ከላይ ከተገለጹት ምሳሌዎች (ምሳሌ 3ና4) በመነሳት "ግን" የንጽጽር ዝምድናን በሚገልጽበት አገባቡ የጭብጥ መዋቅሩ እንድም "ጭው-3" እልያም"ጭው-3 ከጭው-1" ጋር በጣምራ የመነገር ባህሪይ የሚታይበት ይመስላል ማለት ይቻላል።

4.2.1.3. <u>ልዩ ልዩ</u>

ሀ.<u>እርማት(correction)</u>

"ግን" በፀረፍተነገር ውስጥ በሚገኝበት ሁኔታ ተናጋሪው ወይም ተራኪው የራሱን ሃሳብ በራሱ ለመለወጥ የሚገደድበት ሁኔታ ሲያጋጥመው ወደ አልተጠበቀው ውጤት ራሱን የሚያርምበትን ሁኔታ ያሳያል። ይህም እንደለሎቹ የ"ግን" ተግባራት ከሚጠበቀው ወይም ከሚገመተው ሃሳብ መለየትን ቢያመለክትም የመለየቱ ሁኔታ በእርማት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ የእርማት ዝምድና ነው ማለት ይቻላል (ናታል 1982 ይመለከቷል)። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

(5) ...ሁለት ቀን ቢጠብቃት አላገኛትም። በሦስተኛው ቀን ዛሬ
ከገንዳት አገንዳት ከላገንዳት <u>ግን</u> መተው አለብኝ
በማለት...(010/31)

ከላይ በቀረበው ምሳሌ (5) "ግን" የገባበት ሁኔታ ሲጤን ከእጠቃላይ ዐውዱ በተለይም በምሳሌነት ከቀረበው ፃረፍተነገር አኳያ ከ"ግን" ቀጥሎ የመጣው (የተገለጸው) ሃሳብ ቀደም ብሎ ከተገለጸው ወይም ስጥው (given) ከሆነው ሃሳብ በመነሳት የሚጠበቅ ሃሳብ አይመስልም። የተገለጸውም ሃሳብ የሚጠቁመው ተራኪው ተከታይ የእቂም ለውጥ ለማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን ነው። ይህ የእቂም ለውጥ ደግሞ "ማግኘት አለብኝ "ብሎ ያደርግ ከነበረው ጥረት አኳያ በአልታሰበና በልተጠበቀ ሁኔታ የተከሰተ ነው። ስለዚህ ደራሹ ሃሳብ የራሱን እቂም በራሱ ማረሙን(መለወጡን) የሚገልጽ በመሆኑ በሁለቱ ሃሳቦች መከከል ያለው ዝምድና የማረም ዝምድና(correction)ነው።

ይሁን እንጂ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ ከምሳሌ (5) ውሁድ-አሃዳዊ ዐውድ ውጪ ሌላ ተመሰሳይ መረጃ አለጋጠመም። "ግን" በተጠቀሰው ሁኔታ መግባት እንደሚችል ግን ከሰበቱ

አራሚያች ስድስቱ ተሰማምተውበታል። ይህ ደግሞ፤ "ግን"እንዲህ ዓይነት ተግባር እንዳለው የሚያረጋግጥ ይመስላል። በመሆኑም ተግባሩን የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ ተጨማሪ መረጃ በመሰብሰብ መሰል ጥናት የሚጋብዝ ነው።

ለ.<u>ምክንያት</u>(reason)

"ግን" የሚያመለክተው ሌላው ዓይነት ዝምድና ምክንያታዊ ዝምድና ነው። ምክንያታዊ ዝምድና በመጀመሪያና በሁለተኛው ዓረፍተንግግር መካከል የተፈጠረው ዝምድና የሰበብና የውጤት ዝምድና የተገለጸበት መሆኑን የሚያመለክት ነው (ሀሊዴና ሀሰን፤1976፤ ናታል፤1982 ይመለክቷል)።

(6) ...አባቴ የሚሰጠኝ የትራንስፖርት ገንዘብ ገበያውም እምቢ ስላለው ገንዘብ መስጠት አቋረጠብኝ። <u>ነገር ግን</u> እኔ ያለኝ አማራጭ በእግር ተመሰልሰ መማር ጀመርኩኝ።....(003/32)

እንዲህ ዓይነቱ ዮ"ነገር ግን" አጠቃቀም ትክክለኛ ለመሆኑ ከሰባቱ አራሚያች አምስቱ ተሰማምተውበታል። ስለዚህ "ነገር ግን" በዚህ ሁኔታ በጽሑፍ ውስጥ ሊያገለግል እንደሚችል ስምምነት ያለ ይመስላል። በዚህ ዓይነት አጠቃቀም ግን ከጠቀሳነ መረጃዎቻችን የተገኙት ምሳሌዎች (አስረጂዎች) ሁለት ብቻ (ሁለተኛው 012/32:መ–12 ላይ የሚገኘው ነው) ናቸው። ስለዚህ በአራሚያች መሀከል ያለው ስምምነት ተጨማሪ መረጃ ሰብስቦ ማጥናትን የሚጋብዝ ነው። "ነገር ግን" በምሳሌ (6) አጠቃቀሙ ከላይ እንደጠቀስነው ምክንያታዊ ዝምድናን ማመልከት ስለመሆኑ በ"ነገር ግን"ቦታ "ስለዚህ"ን ብንተካ ወይም ሁለት ዐረፍተነገሮች መሆናቸው ቀርቶ "አቋረጠብኝ" የሚለውን ማሰር የሚችል ግስ፤ "ስለ" የሚል ቅድመ ግንድ ቅጣይ ምዕላድ ብናክልበትና "ስለቋረጠብኝ" እንዲሆን ብናደርገው ዐረፍተነገሩ የሃሳብ መፋለስ የማያጋጥመው መሆኑን በማሰየት ማረጋገጥ ይቻላል።

መ. <u>የጊዜ ዝምድና</u>

የጊዜ ዝምድና ደግሞ በሁለት የውሁድ-አሀድ ዐረፍተንግግሮች መካከል እንዲኖር የተፈለገው ወይም ያለው ዝምድና የጊዜንና የሁነትን ተለጣጥቶ (sequence) ሲያመለክት የሚታየው ዝምድና ዓይነት ነው (ሀሊዴይና ሀሰን 1976)። እንዲህ ዓይነቱ ዝምድና በ"ግን"/ነገር ግን/ መገለጹ የተዘወተረ ቢይመስልም ከመረጃችን የተገኘው ብቸኛ አስረጅ የሚከተለው ነው።

(7) ...የትምህርት ሰዓታችን እብቅቶ እንከንለቀቅ ድረስ መቁነጥነጥ እንጀምራለን። <u>ነገር ግን</u> የመለቀቂያ ሰዓት አልቆ ከት/ቤት ግቢ ስንወጣ እኔና ጊደኞቼ የምንገናኝበት ቦታ የታወቀ በመሆኑ ወደዚያ ወደምንገናኝበት ቦታ ተሰባስበን ወደየቤታችን የምናደርገው ጉዞ በጣም የሚያስደስት ነበር። (019/32)

እንዲህ ዓይነቱም አገባብ ትክክለኛ መሆኑን ከሰባቱ አራሚዎች አምስቱ ተስማምተውበታል። ይህ አገባብ ደግሞ ትክክል ከሆነ በሁለቱ ዐረፍተንግግሮች መካከል ያለው ዝምድና የድርጊት ተቀዳድሞ እንጂ ከመጀመሪያው ሀሰብ የመለየት ጉዳይ አይደለም። የሚገልጸውና እንበቢውም የሚገነዘበው ሁለተኛው ሀሰብ በመጀመሪያው ሀሰብ የተለገጸው ተግበር ተከታይ መሆኑን ነው። ስለዚህ "ነገር ግን" በዚህ አገባቡ ግልጽ ያደረገው ዝምድና የጊዜ ዝምድና ወይም ጊዜ-ጠቀስ (temporal) ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም "ነገር ግን"ን በ"ከዚያም" ብንተካው ዐረፍተነገሩ የተዛባ አይሆንም።

ሠ. <u>ማከል (መጪመር)</u>

"ማከል" ወይም "መጪመር" ሀሊዴይና ሀሰን (1976) እንደሚሉት "ቀድሞ በተገለጸ ሀሰብ (መረጃ) ላይ ሌላ አዲስ ተጨማሪ መረጃ ወይም በመጀመሪያው ያልተገለጸ መረጃ ተከትሎ ሲቀርብ የሚታይ ዝምድና ነው። "ነገር ግን" እንዲህ ዓይነቱን ዝምድና ሲያመለክት ከጠቀሳቸ መረጃዎቻችን እንድ አጋጣሚ ብቻ ተስተውሏል። ይህም እንደሚከተለው ይነበባል።

(8) ...እለት በእለት በሚያከናውናቸው እንደንድ ሥራዎች ቤተሰቡንና እራሱን መርዳት ችሏል። <u>ነገር ግን</u> ትምህርቱን አጥንቶ ለከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል ያለው ፍላጎት ከፍ ያለ በመሆኑ የተነሳ ቤተሰቡንና እራሱን ለመርዳት ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በተጨማሪ ያለፈውን ትምህርት እያጠና በዝግጅት ላይ ይገኛል። ...(006/31)

ከምሳሌ (8) እንደሚታየው ከ"ነገር ግን" በፊትና በኋላ ባሉት ሁለት ዐረፍተንግግሮች መካከል የመለያየት ሁኔታ አይታይባቸውም። እንዲያውም በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር ያልተገለጸው የባለታሪኩ ሌላ ገጽታና ሌላ ጥረት በሁለተኛው ሲገለጽ ይታያል። በመሆኑም "ነገር ግን" በዚህ አገባቡ የሚሰጠው ስሜት "በተጨማሪ የሚገለጽም አለ" የሚል ይመስላል። "ነገር ግን" "በተጨማሪ" ወይም "በሌላ በኩል" በተሰኙት ዲስኩር አመልካቾች ቢተካ የሚያስከትለው ችግር ያለ አይመስልም። ስለዚህ "ነገር ግን" በዚህ አገባቡ ያመለከተው ዝምድና የ"ማከል"/ የመጪመር/ ዝምድና ይመስላል።

ይሁንና ይህ አገባቡ ትክክል ለመሆኑ ከሰባቱ አራሚዎች አራቱ ስምምነታቸውን ሲገልጹ ሦስቱ ስህተት ነው ብለዋል። ከአብዛኛው ድጋፍ አኳያ ተግበሩ ቢተነተንም ከሰባት ሰው የሦስት ሰው በሀሰብ መለየት በቀላሉ የሚታይ አይመስልም። ስለዚህ ተጨማሪ ጥናት የሚጋብዝ ሆኖ ይታያል።

በ4.2.1.3. ሥር የተዘረዘሩት የ"ግን/ነገር ግን/" ተግባራት ከመረጃ ብዛት አኳያ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም ዲስኩር እመልከቹ እነዚህን ተግባራት ሊፈጽም እንደሚችል ደግሞ የአብዛኛዎቹ አራሚዎች ስምምነት እንደለ በቦታው ተጠቅሷል። ስለዚህ እነዚህንም እንደተግባራት መውሰዱ ተገቢም፣ አስፈላጊም ይመስላል። ሆኖም በዚህ ረገድ ተጨማሪ ጥናት የማድረጉ ተገቢነት አያጠያይቅም።

ከጭብጥ መዋቅር አንፃር በወጥነት ይህ ነው ለማለት መረጃው በቂ ባይሆንም ከቀረቡት መረጃዎች አኳያ በሥዕላዊ መግለጫ -1 ከቀረበው በ"ጭው"- የተገለጸውን የሚከተሉ ይመስላሉ። ማለትም በሥዕል ሦስት ስምሳሌ (4) የሰጠነውን የጭብጥ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ የመከተል አዝማሚያ ይታይባቸዋል።

ከላይ የ"ግን/ ነገር ግን/" ተግባራትና የሚያመለክቷቸውን ዝምድዎች ከ4.2.1.1.-4.2.1.3 ለመተንተን ተሞክሯል። በዚህም "ግን/ ነገር ግን/" የ"ልየታ" ዝምድናንና የ"ማነፃፀር" ዝምድናን እንደሚያመለክት፣ በተጨማሪም ምንም እንኳ ከተሰበሰቡት የተማሪዎች ተራኪ ውሁድ-አሀደች ውስጥ በርከታ መረጃ ማግኘት ባይቻልም የ"ማረም"፣ የ"ምክንያት"፣ የ"ጊዜ" ና የ"ማከል" ዝምድናዎችንም እንደሚያሰይ በስፋት ተብራርቷል። ስለዚህ ከመረጃዎቻችን በመነሳት "ግን/ ነገር ግን/"፣ የ"ልየታ"፣ የ"ማነፃፀር"፣ የ"ማረም"፣ የ"ምክንያት"፣ የ"ጊዜ" ና "የማከል/ የመጨመር/" ዝምድና ያመለክታል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

ይህ ደግሞ በ2.2.1. እንደተመለከተው ቀደምት የሰዋሰው ሊቃውንት ከሰጡት ግለጫ ጋር አይስማማም። የሊቃውንቱ ግለጫ "ግን/ ነገር ግን/" ና መሰሎቹ መስተጻምራን "እፍራሽ መሆናቸውን" የሚገልጽ ነው። በዚህ ንኡስ ክፍል ደግሞ የታየው ተግባር ማፍረስ ሆኖ አልተገኘም። በ4.1.2.1. ሥር የተገለጸውም ይኼው ነው። ስለዚህ የ"ግን/ ነገር ግን/" ተግባር በእብዛኛው የ"ልየታ" (adversative) (ሀሊዴይና ሀሰን 1976 ያገናዝቧል) ዝምድናን፣ ከዚያ በመለስ ደግሞ በ4.2.1.3. የዘረዘርናቸውን ዝምድናዎች ነው የሚያመለክተው። የልየታ ዝምድናም ልየታንና ንጽጽርም ይይዛል። (ሀሊዴይና ሀሰን፣ 1976፤ ሀሊዴይ፣ 1985a፤ ናታል፣ 1982)። ምክንያቱም ንጽጽርም ቢሆን ከመጀመሪያው ሀሳብ የሁለተኛው መለየቱን ነው የሚያመለክተው። ይህም ጋሰር (1984) ለ"-ስ" ቅጣይ መስተፃምር ከሰጡት የኢቀጣይነት (discontinuity) ባህርይ ጋር የሚዘመድ ይመስላል።

ከጭብጥና ከጭብጥ መዋቅርም አንፃር "ግን/ ነገር ግን/" ለተወሰኑ ተግባራት የተወሰኑ "ጭው"ዎችን የሚጠቅና የሚከተል- በ4.2.1.3 ሥር የተዘረዘሩትም ተግባራት ቢሆኑ የተወሰነ ውቅር (pattern) የሚከተሉ ስለሚመስሉ-ይመስላል። በዚህም መሠረት የልየታ ዝምድናን በሚያመለክቱበት ጊዜ በ2.1.2. ሥር ከተጠቀሱት "ጭው"ዎች የመጀመሪያውን "ጭው-1"፣ የንጽጽር ዝምድናን

ሲያመለክት ደግሞ በአብዛኛው "ጭ-3" እንዳንዴ ግን በ4.2.1.2. እንደተመለከተው "ጭ-3" ና "ጭ ው-1" በጣምራ እንደሚገለገል ታይቷል። በሌሎችም ተግባራቱ- በ4.2.1.3. የተዘረዘሩት- በተመሣሣይ ሁኔታ "ጭ-3"ን የሚገለገል ይመስላል። ይህ ግን ወደፊት በበለጠ መረዳ ለማረጋገጥ ለጥናት ይጋብዛል።

"ግን" በተለይ ደግሞ ለብቻው በሚገባቸው ሥፍራዎች ለምሳሌ፣ በምሳሌ (4) የተጠቀሰውን ዓይነት አገባብ ሲኖረው ከሌላው ውሁድ-አሀዳዊ ተግባሩ በተጨማሪ አጽንኦታዊ (emphatic) ሆኖ የዐረፍተንግግሩን ጭብጥ ያመለክታል። በዚህ ጊዜ አንባቢው፣ የጽሑፉን የመረጃ አወቃቀር ለመገመትና ትኩረቱም በምን ላይ እንደሆነ ለመረዳት ያስችለዋል። ከዚህ ሌላ በዐረፍተነገር ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በእንቀጽ /rheme/ ውስጥ ሲገኝም እንዲሁ ከሌላው ተግባሩ በተጨማሪ አጽንኦታዊነትን ያመለክታል። በመጨረሻም በውሁድ-አሀድ እንድና ሁለት ውስጥ የታዩትን የ"ግን/ነገር ግን/" አጎዛዊ ሥርጭቶች ከተግባራቱ አኳያ በሚከተለው አኳኋን ማጠቃለል ይቻላል።

ዲስኩር	ልየታ		ንፅፅር		ሌሎች		ጠቅላላ ድምር	
አመልክች	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%
ግን/ነገርግን/	85	67.46	31	24.60	10	7.94	126	100

4.2.2. የ"(እ)ና" ተግባራት

"(እ)ና" በ4.1.2.2. እንደተገለጸው በውሁድ-አሀድ ውስጥ በተለያዩ የቋንቋ አውዶችና አካባቢዎች እንደሚገባ የጥናቱ መረጃ ከሆኑት ውሁድ-አሀዶች ውስጥ የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ። ተግባሩም በነዚሁ ዐውዶች ውስጥ እየተገኘ የተለያዩ ተግባራትንና ዝምድናን ማሰየት ነው።

"(እ)ና"፣ ከላይ በ2.2.1. ሥር በተጠቀሱት ቀደምት የሰዋስው ሊቃውንት ዘንድ ወደረኛ መስተፃምር ሆኖ በአጫፋሪ መስተፃምር ሥር ተመድቦ የሚገኝ ዲስኩር አመልክች ነው። ሊቃውንቱም (ለምሳሌ ተክለማሪያም ፉንታዬ 1957 ዓ.ም.፤ ይትባረክ ወልደሚካኤል 1966 ዓ.ም.) "ወደረኛ መስተፃምር እኩል የሆኑ ቃላትንና ዐረፍተነገሮችን የሚያያይዝ" እንደሆነና "(እ)ና"ም ይህንኑ ተግባር "በዐረፍተነገር ውስጥ እኩልነት ያላቸውን ነገሮች በማጫፈር እንደሚፈጽም ይገልፃሉ። ከመዋቅራዊ የቋንቋ ጥናት አንፃር አማርኛን ለመተንተን ጥረት ያደረጉት ኃይሉ ፉለስም (1966 ዓ.ም.) "(እ)ና" በወደረኛ መስተፃምርነቱ "ሰዋስዋዊ እኩልነት ያላቸውን አበሮች (constituents) የሚያጫፍር /የሚያያይዝ/" መሆኑን ይጠቁማሉ።

ሆኖም በዚህ ጥናት ከተገኘው መረጃ አንፃር (ለዝርዝሩ ከ4.2.2.1. -4.2.2.4. ይመለከቷል) ከላይ የጠቀስናቸው ሊቃውንት ግለ ሄና ተግባር በእጅጉ የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም። ምክንያቱም እነሱ የተመለከቱት የማጫፈርን ተግባር (coordinate) ለመፈጸም በስምና በስም መሰሎች ቃላትና ሐረጋት መካከል የሚገባበትን ሁኔታ ብቻ ነው ማለት ይቻላል። ሆኖም በእንዳቸውም መጽሐፍ ውስጥ ከዚህ የተለየ ማብራሪያ ወይም አስረጅ ባለመሰጠቱ በእንድምታ "(እ)ና" በሚገኝበት ቦታ ሁሉ የሚፈጸመው ተግባር ማጫፈር እንደሆነ ተደርጉ የተወሰደ ይመስላል። ይህ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው ወጥነት ያለው ግለ ሄ እንዳልሆነ ለዚህ ጥናት ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለሆነም በስሞችና በስም መሰሎች ቃላትና ሐረጋት መካከል ከሚገኝበት ውጪ በጥገኛና በበቂ ዐረፍተነገሮች ላይ/መካከል/ በሚገኝበት ሁኔታ ያሉት ተግባራት ቀጥሎ ይቀርባሉ።

4.2.2.1. <u>ተለጣጥቆ</u>

የ"(እ)ና" ተግባራት ከሆኑት እንዱ ተለጣጥቆአዊ ዝምድናን ማመልከት ነው። ተለጣጥቆ፣ ተከታትሎ ከመከሰት/ከመፈጸም/ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሁነቶችንና ድርጊቶችን በሚገልጹ ዐረፍተነገሮች መካከል ያለውን ተጠየቃዊ ዝምድና የሚያመለክት ነው (ናታል 1982፤ ትሪምብል 1985፤ ሃኾ 1992ን ያገናዝቧል)። ተከታትሎ መከሰት /መፈጸም/ የሚያመለክተውም ቅደም ተከተልን ነው። ቅደም ተከተል ደግሞ በቀጥታ ከጊዜ ጋር የተያያዘ ነው። ስለሆነም "(እ)ና" ተለጣጥቆአዊ የሆነን ጊዜ-ጠቀስ ዝምድናን ይፋ ያደርጋል ማለት ይቻላል። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

(9) ...ከልኩኝ በኋላ ሁኔታውን አስብበት እንጂ እምጣት ብየአለሁ አልኩት። ወዲያውኑ ይሄድና ልጅቱን ይዘ መጣ (005/31)

ከምሳሌ (9) እንደምንመለከተው የ"ና" አገባብ በሁለተኛው ዐረፍተነገር ውስጥ ከሚገኘው ጥገኛ ዐረፍተነገር ግስ ላይ ነው። ከዚህ አገባቡም እንባቢው የሚረዳው ከሱ ቀጥሎ በሚመጣ ሌላ ሐረግ-ዐረፍተነገር-አማካይነት ቀጥሎ የሚገለጽ ድርጊት መኖሩን ነው። በሌላ አገላለጽ በአንባቢው አእምሮ "ቀጥሎ ምን አደረገ?" የሚል ጥያቄ ያጭራል። ለዚህ ጥያቄም የሚገኘው ምላሽ ደግሞ የሚገልጸው ከ"መሄድ" ተግባር ቀጥሎ የተከናወነውን ሌላ ተግባር ነው። ከዚህም የ"መሄድ" ተግባር ቀድሞ የ"መያዝና የመምጣት" ተግባር ለጥቆ መፈጸሙን መረዳት ይቻላል። የ"ና"ም ተግባር ይህን የተለጣጥቆ ዝምድና ለአንባቢው ግልጽ ማድረግ ነው የተባለውም ለዚህ ነው።

በሌላ በኩል ከጠቀሰላው መረጃ እንደታየው በ"ይሄድ" ዓይነት የግስ ቅርጽ የሚነገሩ/የሚፃፉ/ ግሶች ባሏቸው ጥገኛ ዐረፍተነገሮች ላይ "(እ)ና" ሲገባ ለምሳሌ፣ "...ይደበቅና...019/31 መ.5"፣ "...እንሰበሰብና...019/32 መ.22" የተለጣጥቶን ዝምድና ያመለክታል። ይህ ደግሞ እንበቢው የ "(እ)ና"ን ተግባርና የሚያመለክተውንም ዝምድና ፈጥኖ እንዲረዳ ያግዘዋል። ስለሆነም የ"(እ)ና"ን ተግባር የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የቋንቋ መዋቅርም አስተዋጽኦ አለው ማለት ይቻላል። ይህንንም በሚከተለው መልክ ማጠቃለል የሚቻል ይመስላል።

[[[. . . [መደብ እመልከች ምዕላድ + ግስ(ኢፍጽም አምድ)*]]+(እ)ና]...]

ው.አ. ጥ.ዐ.ነ.** ግስ

በተመሣሣይ ሁኔታ "(እ)ና" ከገባበት ዐውድ አኳያ ተለጣጥቶን እንደሚያመለክት የሚቀጥለው ምሳሌ ያሰያል።

(10) ...እቤት ገብቼ የያዝኩትን በቶዳ የተጠቀለለ ሥጋ እመሬት ሰፍ ሰደርገው አባቴ ይህን በማየት ጠላትህ ሰፍ ይበል አለኝና ወንድነቴን እደነቀው (002/31)

በምሳሌ (10) ውስጥ "(እ)ና" የገባው ማሠር በሚችል የ"አለ ግስ"*** (verb to say) ላይ ነው። ከዚህም የምንገነዘበው "የማድነቁ" ሂደት የቀጠለው "ጠላትህ ሰፍ ይበል" ከሚለው ሙገሳ ቀጥሎ መሆኑን ነው። ስለዚህ ከዚህና ከሌሎችም መሠል አገባቦች –ለምሳሌ፣ "...አለችና..." 010/31 መ.20፣ "...ይልና..." 012/31–"(እ)"ና የሚያመለክተውን የተለጣጥቶ ዝምድና እንበቢው ሊገነዘብ ይችላል። በዚህኛውም እንደተመለከትነው እንበቢው የ"(እ)ና"ን አገልግሎት በቶሎ እንዲረዳና የንበቡንም ከንውን እንዲያቀላጥፍ የሚያግዘው ከገጠመኙ ዐውድ በተጨማሪ የቋንቋው አውድ ነው ማለት ይቻላል። በዚህ መሠረት በምሳሌ (10) ያየነውን አገባብ ብናጠቃልለው የሚከተለውን ይመስላል።

---

* ኢፍጽም አምድ ያልተፈጸመን ድርጊት የሚገልጽ ግስ ዋና ቅርጽ ለምሳሌ [ህኝይድ]፣ [–ግኝድል]፣ [ብኝ ቅል] ወዘተ. ያመለክታል (በዬ 1987 ዓ.ም. ይመለከቷል)።

** "(እ)ና" የገባበትን ጥገኛ ዐረፍተነገር ያመለክታል። ወደፊት እንደሚያጋጥመውም አንዳንድ ጊዜ ጥ.ዐ.ነ. ሙሉ ዐረፍተነገር ሊሆን ይችላል። ው.አ.ደግሞ አገባቡ ጠቀሰላ የታየበትን ውሁድ–አሀድ ያመለክታል።

*** ይህ እንደ ሰቅ–፣ ፀጥ–ወዘተ. ባሉት ድጋፍ ፈላጊ ቃላት ላይ የሚገባውንም "አለ" ጨምሮ እንዲይዝ ተደርጓል።

[[...[የ"አለ" ግስ –]+(እ)ና]...]

በመረጃዎቻችን መሠረት ይኼው የ"(እ)ና" ተግባር በሌሎች የቋንቋ ዐውዶችም ሲከሰት ታይቷል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(11)...የእኔ ስም ሸዋቀና ይባላል። የአንቺ ስም ግን አበባ እንደሚባል አውቄዋለሁ በማለት ሥሙን አስተዋወቃትና የኔ አበባ ለምጠይቅሽ ጥያቄ መልስ እንድትመልሽልኝ ፈቃደኛ ነሽ? (0101/31)

(12)...በጎልም ውጤቱ ተነገረና ያላሰብኩትን ነገር ግን መጥፎ ያልነበረ ውጤት አመጣሁና* ከተቤ መምህራን ት/ኩሌጅ ለመግባት በቃሁ። (017/32)

በምሳሌ (11) በቀረበው ውሁድ–አሀድ ውስጥ "(እ)ና" የገባው በመጀመሪያው– ቀድሞ በመጣው–ዐረፍተንግግር መጨረሻ ላይ ነው። ከ"(እ)ና" ቀጥሎም ሁለተኛው–ተከታዩ–ዐረፍተንግግር ተገልጿል። በሁለቱ ዐረፍተንግግሮች መካከል የመጣው "(እ)ና" የሚያመለክተው ዝምድና ከጊዜ አንፃር የድርጊቶች ወይም የክንውኖች ቅደምተከተል የተገለጸበትን ዝምድና ነው። ማለትም "አበባ ለምትጠየቀው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኗን" የሚጠይቀው ዐረፍተንግግር "ሸዋቀና" የራሱን ስም ከማስተዋወቁ ሂደት ቀጥሎ የመጣ መሆኑን የሚያመለክት የተለጣጥቆ ዝምድና ነው።

በምሳሌ (12)ም እንዲሁ በሁለት ዐረፍተንግግሮች መካከል እንደሚገኝ የገባበት ዐውድ ያመለክታል። በዚህ አገባቡም በሁለተኛው ዐረፍተንግግር ውስጥ "ያላሰብኩትን ነገር ግን መጥፎ ያልነበረ ውጤት" በሚለው ሐረግ የተገለጸው ሐሳብ የ"መታወቁ ሂደት" በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር ውስጥ በለው "ውጤት ተነገረ" በሚለው ሐረግ ከተገለጸው የ"መነገር ሂደት" ቀጥሎ የተከሰተ መሆኑን ያመለክታል። በጭሩ "(እ)ና" የጊዜ ተቀዳድሞእቸውን ወይም ተለጣጥቆእቸውን ይፋ ያደረገ ዲስኩር አመልካች ነው።

---

* አገባቡና ተግባሩ ሌላ ስለሆነ ዝርዝሩ የሚቀርበው በ4.2.2.2. ነው።

በሁለቱ ምሳሌዎች (11 ና 12) ውስጥ "(እ)ና" የገባባቸው ቦታዎች የሚያስሩ ግሶች የመጀመሪያው በ"እስ-"፣ ሁለተኛው በ"ተ"- ምዕላድ የሚጀምሩ በመሆናቸው መዋቅራዊ ልዩነትም አላቸው። መዋቅራዊ ልዩነቱ ግን ያስከተለው የተግባር ወይም የዝምድና ለውጥ የለም።

ስለዚህ ከላይ እንደተብራራው በሁለቱም ቦታዎች ተግባሩ "ይኸኛው ከተደረገ/ከተፈጸመ/ ከሆነ በኋላ" የሚል ስሜት በመስጠት የጊዜንና የድርጊትን ተለጣጥቆ ማመልከት ነው። በዚህ መሠረት በሚቀጥለው አገባባዊ ቀመር የሚጠቃለል ይመስላል።

- ለምሳሌ (11)

[[[. . . [እስ-+-ግስ-+-እፀፋ-]]+-(እ)ና]...]

ለምሳሌ (12)

[[[. . . [ተ-+-ሀለፈ ግስ-+-እፀፋ-]]+-(እ)ና]...]

ከላይ በ4.2.2.1. ሥር በምሳሌነት በተጠቀሱትና (ምሳሌ9፣ 10፣፣ 11ና 12) በሌሎቹም እዚህ ባልተጠቀሱት ተመሳሳይ አገባቦች ባሉበቸው መረጃዎቻችን ውስጥ የገባው "(እ)ና"፣ ከየውሁድ-እሀደች ጭብጦች ይልቅ ከየእንቀጸቹ (Rhemes) ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ይመስላል። ከጊዜ-ጠቀስ-ተለጣጥቆ-ዝምድና አኳያ በደስኩር አመልካቹ የሚገለጸው ተግባር እንዱ ድርጊት ከሌላው ድርጊት ቀድሞ ወይ ቀጥሎ የተፈጸመ መሆኑን ማመልከት ነው። በዐረፍተነገር መዋቅር ውስጥ ደግሞ ድርጊት የሚገለጸው በግሱ ነው። "(እ)ና" ከላይ በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ የገባው በመጀመሪያው ዐረፍተነገር-ጥገኛም ሆነ ጥገኛ ባልሆነ ዐረፍተነገር-መድረሻ ላይ ከለው ግስ ጋር ነው። ግሶቹም የሚገኙት በእንቀጸቹ ውስጥ ነው።

በጭብጥ መዋቅር ውስጥ ቀደም ሲል በ2.1.2. እንደተገለጸው፣ ጭብጥ፣ እንደ ሀሊዴይ አገላለጽ "የጸሀፊውን የሀሳብ መነሻ /Point of departure/ የሚገልጸው ቃል /ሐረግ/ ነው።" በሌላ አገላለጽ ጭብጥ የፀሐፊው ትኩረት የሚከሰትበት በዐረፍተንግግሮች "ግንባር" ላይ የሚገኝና (ማክርቲ፣ 1991) በ"ጭው" ውስጥ ቀድሞ የሚነገር ቃል /ሐረግ/ ነው። "(እ)ና" ከላይ እንደየነው

ከዚህ አከል ጋር ሲገባ እልታየም። ሆኖም በመረጃችን መሠረት "(እ)ና" በአንቀጽ ውስጥ ይገኝ እንጂ የገባባቸው የውሁድ-አሀድ ዐረፍተንግግሮች የተከተሉት "ጭ ው" የ"ጭ ው-1"ን መሠረተ ሀሳብና አካሄድ ነው። (ዝርዝሩ በ2.1.2. ቀደም ብሎ ተጠቅሷል)። ይህን መሠረት በማድረግ የምሳሌ (9)፣ (10)፣ (11)ና (12)ን "ጭ ው"ዎችና የ"(እ)ና"ን አገባብ በሚቀጥሉት ሥዕላዊ መግለጫዎች ለመወከል ተሞክሯል።

ሀ. የምሳሌ(9)ጭ ው



ለ. የምሳሌ (10)ና(11)



መ. የምሳሌ (12)



ሥዕል 4፣የምሳሌ 9፣ 10፣ 11ና 12 ጭብጣዊ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ

4.2.2.2. ምክንያት (reason/cause)

የምክንያት ተዘምዶ አንዱ ለአንዱ መከሰት ወይም አንዱችነገር መሆን ምክንያት /ሰበብ/ መሆኑን ወይም አንዱ የአንዱ ነገር ውጤት መሆኑን ወዘተ. የሚያመለክት ዝምድና ነው። ዲስኩር አመልካቹም የሚያመለክተው ይህንኑ ነው (ናታል፣ 1982)። "(እ)ና"ም ይህን ዓይነት ዝምድና እንደሚያመለክት መረጃዎች አሰይተዋል። ከላይ ለ4.2.2.1. ከቀረቡት

ማስረጃዎች በምሳሌ (12) ሥር የተጠቀሰው ሁለተኛው የ"(እ)ና" አገባብ የሚያሳየው ይህንኑ የምክንያት ተዘምዶ ነው። "ከተቤ መምህራን ትምህርት ከሌጅ ለመግባት" ያስቻለው "መጥፎ ያልነበረ ውጤት ማምጣቱ" እንደሆነ ግልጽ ነው። ከሌጅ መግባት ያለውጤት የማይታሰብ ስለሆነ ዝምድናው "(እ)ና" ባይኖርም ከሁለቱ የውሁድ-አሀድ ዐረፍተንግግሮች ጀርባ (Underlyingly) ቀድሞውኑ አለ ሊባል ይችላል፤ ይህ ትክክል ነው። በዚህ ጥናት ክፍል 2.1.3. የተገለጸውም (የዊደውሰንን፤ 1979፤ 1984፤ የካሬልን 1982፤ የኑናን 1993 ሥራዎች ያገናዝቧል) ይኸው ነው። ግን በ2.1.4. እንደተጠቀሰው ሁሉ የዲስኩር እመልከቹ ተግባር-በእሁኑ ምሳሌ "(እ)ና"-ይህንን አለ የተባለውን ዝምድና ይፋ ማድረግ ነው። የጥናቱ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ግን "(እ)ና" ከገባበት የቋንቋ ዐውድ አኳያ "እመጣሁ"ን የመሰለ ቅርጽ በሳቸው ግሶች ላይ ሲገባ በወጥነት ይህን ተግባር በሁሉም ቦታ ላይፈጽም ወይም የተጠቀሰውን ዝምድና ላያመለክት ይችላል። ይህም የሆነበት ምክንያት ቅርጹ "(እ)ና"ን ሲጨምር [እ-ግስ+-እፀፋ+-(እ)ና]፤ በእመዘኛ ከምክንያት ይልቅ ጊዜ-ጠቀስ የሆነን ዝምድና የሚያመለክት መሆኑን መረጃዎቻችን ስለሚጠቁሙ ነው። የምክንያት ዝምድናም በተወሰነ ደረጃ የጊዜ ተለጣጥቆን በውስጡ የያዘ ስለሚመስል እንዲህ ዓይነቱ ግርታ መፈጠሩ አይቀሬ ይመስላል። ከላይ በሰጠነው ምሳሌ ውስጥ ያለው ዝምድና ከጊዜ ይልቅ ሁኔታን (Condition) የሚገልጽ ምክንያታዊ ዝምድና ለመሆኑ "እመጣሁና*" የሚለው ቅርጽ "ስለእመጣሁ" እንዲል ቢደረግ የዐረፍተነገሩ አለመዛባት ወይም ትርጊሜ አለመለወጥ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

"(እ)ና" የምክንያት ተዘምዶን የሚያመለክትባቸው የተለያዩ ቦታዎች መኖራቸውን ከጥናቱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል። የሚከተሉትን እንመልከት።

(13)...እንግዲህ እሺ በለኝ እባክህ ሲል እየህ ከተልባ ጋር ያለህ ሰሊጥ እብረህ ተወቀጥ ይባላልና ያሰብከው ነገር ጥሩ ስላልሆነ ያንተ መሰቀያየት ለእኔም ጭምር ነው...(005/31)

(14)...ስለሆነም እናትህ ከዚሬ ጀምሮ ተደፍታለችና እንተንም ሆነ ገንዘብህን አትፈልግም።...(007/31)

(15)...በፈገግታዋ በጣም ተደሰተ እና አንቺን ለማነጋገር ፈልጌ እስ ነው የእኔ እበባ እንዲህ የምጠነቀው አለት።...(010/31)

---

* "እመጣሁ" በዚህ ምሳሌ አጠቃቀሙ ከመሠረታዊ ፍቺው ይልቅ ዐውዳዊ ፍችው ነው የሚያገለግለው። አንድን ነገር ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ማንቀሳቀስን ሳይሆን የሚያመለክተው የሥራን፤ የልፋትን ውጤት ማወቅንና ማግኘትን ነው።

(16)...ቢሆንም ግን ከትምህርት ውጪ ለጥናት የምጠቀምበት
ጊዜ እልነበረኝም። እናም ወደ ስምንተኛ ክፍል በሚያረክ
ውጤት ሰላልፍ ቀረሁ...(018/31)

ከላይ በተዘረዘሩት አራት ምሳሌዎች እንደሚታየው የ"(እ)ና" አገልግሎት መጀመሪያ-ቀድመው-የተጠቀሱት ሐሳቦች ምክንያቶች፣ በሁለተኛ-በተከታዮቹ-ዐረፍተነገሮች የተጠቀሱት ሁኔታዎች ደግሞ ውጤቶች እንደሆኑ ማመልከት ነው። በመጀመሪያዎቹ ሦስት አስረጅዎች (13፣ 14ና 15) የ"እና" አገባብ ከመጀመሪያዎቹ የየውሁድ-አሀደቹ ዐረፍተንግግር ግስ ጋር ነው። በ16ኛው አስረጅ ግን "-ም"ን በመድረሻው ከግስ በተጨማሪ አገባቡ በሁለቱ ዐረፍተንግግሮች መካከል በሁለተኛው መነሸ ላይ ነው። ስለዚህ ይህኛው በቅርጹም በአገባቡም ከቀሪዎቹ ይለያል፣ አገልግሎቱ ግን ያው ምክንያትን መግለጽ ነው።

ይህ ቅርጽ-"እናም"- በ2.1.2. እንደተገለጸው ጋሰር (1984፣ 61-62) በእግርኛ "-ም"ና "-ስ" ላይ በካሄዱት ዲስኩራዊ ጥናት "-ም" በእውነተኛ መስተጣምር-ለምሳሌ "እና"፣ "ግን"... በመሰሰሉት-ላይ እንደማይገባ ከሰጡት ማጠቃለያ ጋር አይጣጣምም። መረጃችን ከ"-ም" ጋር አብሮ ሲገባ በተደጋጋሚ አሰይቷል። አጠቃቀሙም-ለምሳሌ ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ላይ መግባቱ-ትክክል ስለመሆኑ ሰበቱም አራሚዎች ስምምነታቸውን ገልጸዋል። በዚህ መሠረት "-ም" ከ"(እ)ና" ጋር ይገባል ማለት ይቻላል። በመረጃዎቻችን ውስጥ በተገኘባቸው ቦታዎች ሁሉ ግን ተግባሩ ምክንያት መግለጽ ላይሆን ይችላል። በምሳሌ (13፣ 14ና 15) ውስጥ "(እ)ና" ከገባበት መዋቅራዊ ቦታ አኳያ የተወሰነ ሕግ የሚከተል ይመስላል። ስለሆነም ከመረጃዎቻችን አኳያ የሚከተሉት ቅርጾች በነዚህ ምሳሌዎች የጠቀስናቸውን የ"(እ)ና"ን አገባቦች ሊወክሉ ይችላሉ።

ለ(13)

[[[...[መደብ አመልካች ምዕላድ+ኢፍጽም አምድ--አል]] +-(እ)ና]...]

ለ(14)

[[[...[ቶ-+ ኢፍጽም አምድ+-አል+-አፀፋ]] +-(እ)ና]...]

ለ(15)

[[[...[የሁኔታ ግስ (statives)-]] +-(እ)ና]...]

በ"ጭ ው" ውስጥ ምክንያታዊ ዝምድናን የሚያመለክተው "(እ)ና"—"እና"ን ሳይጨምር—በሁሉም ቦታ ከጭብጡ ጋር ሳይሆን ከእንቀጹ ጋር ግንኙነት ያለው ይመስላል። ምክንያቱም የሚገኘው በሁሉም ቦታዎች በውሁድ-አሀዶቹ የመጀመሪያ/ቀዳሚ ዐረፍተንግግሮች እንቀጽ ውስጥ ሆኖ በእንቀጾቹ መጨረሻ ላይ ከለው ግስ ቀጥሎ ነው። ስለዚህ ለጭብጥ አስተዳደግ ያለው ሚና በእንቀጹ ውስጥ ከሚገኘው ግስ ጋር በመግበት (ከአራት ነጥብ ወይም ከንባብ ተግታ (pause) በኋላ የሚመጣውን "እና" ሙሉ በሙሉ እይመለከትም) ምክንያታዊ ተዛምዶን መግለጽ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህ አገባቡ ዋቢ ነትም የተጠቀሱት ምሳሌዎች "ጭ ው" (ከምሳሌ (13) በቀር) በሙሉ ተመሣሣይ ይመስላል። ምሳሌ (13) ለየት ያለው "(እ)ና" በገባበት ቦታ ልዩነት ኖሮት ሳይሆን፣ "(እ)ና" የገባበት ዐረፍተንግግር ከመጀመሩ በፊት የተገለጸ የሌላ ተራኪ ሀሳብ የተገለጸበት ዐረፍተ ንግግር በመኖሩ ነው። በሥዕላዊ መግለጫ ብንወክላቸው የሚከተለውን ይመስላሉ።







ሥዕል 5፣የምሳሌ 12፣ 14፣ 15ና 16 ጭብጣዊ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ

4.2.2.3. "ልየታ"

"(እ)ና"፣ ከ"ይሁን-" ጋር ተቀናጅቶ በሁለተኛው ንግግር መጀመሪያ ላይ ሲገባ የ"ልየታ"ን ዝምድና-ማለትም ከሚጠበቀው ሀሳብ ውጪ የሆነ ተዛማጅ ሀሳብ መነገሩን የሚያመለክት ይመስላል። በዚህ አገባቡም "(እ)ና" ከ"እንጂ" ጋር ተመሳሳይ አገባብና አገልግሎት ያለው ይመስላል (ና= እንጂ)። ከመረጃዎቻችን የተገኘው ብቸኛ አስረጅ የሚከተለው ነው።

(17)...አብረውኝ ይማሩ ከነበሩና ትምህርታቸውን ከቀጠሉት ጓደኞች በአስተሳሰብ ያነስኩ እንዳልነበርኩ አስታውሳለሁ። ይሁንና ትምህርቴን በለመጨረሴና እንደጓደኞቼ ለሥራ በለመብቃቴ ይቆጨኝ ስለነበር...(017/32)

በሌላ በኩል "እናም"፣ እንደዚሁ በውሁድ-አሀድ ውስጥ በፀረፍተንግግሮች መካከል፣ በተከታዩ ፀረፍተንግግር መነሻ ላይ በመግባት ስጥው በሆነው ሀሳብ መነሻነት ከሚገመተው ሀሳብ ውጪ የቀረበውን ተዛማጅ ሀሳብ ሲያመለክት ተገኝቷል። ይህም እንደሌይኛው ያለው ብቸኛ ምሳሌ የሚከተለው ነው።

(18)...የእህቱ በእድሜ አለመብለል እንደሱ የጠንቃቃ በህሪይ በለቤት አለመሆን ሁሌ ያሳስበዋል። እናም መፍትሔው በቅጽበት ብልጭ ስለማይልለት በማያረካ ሀሳብ እራሱን ሸነጋግሎ ያለፈዋል።...017/31)

ይህ የ"እናም" አጠቃቀም ትክክለኛነት በሰባቱም አራሚዎች ስምምነት ተረጋግጧል። ስለዚህ አገባቡ ትክክለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ተግባሩ አጠራጣሪ የሚሆን አይመስልም። በዚህም መሠረት "እናም"፣ የ"ግን"ንና የመሰሎቹን ዲስኩር አመልካቾች ዓይነት ተግባር ይፈጽማል ማለት ይቻላል።

እነዚህ ሁለት አገባቦች በ"ጭው" ውስጥ ያላቸው ሚና በሁለተኛው ፀረፍተንግግር መነሻ ከጭብጡ ቀድሞ በመግባት ተከታዩ ሐሳብ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል መጠቆም ይመስላል። በመረጃዎቻችን ቁጥር ማነስ የተነሳ ከ"ጭው" አኳያ ይህን ይመስላሉ ብሎ ለማጠቃለል ስለማያስደፍር ሁኔታው ለሌላ ጥናት የሚጋብዝ መሆኑን እዚህ ላይ መግለጽ ብቻ በቂ ይመስላል።

4.2.2.4. ተጨማሪ ሀሳብ (additional idea)

"(እ)ና" ከላይ ከጠቀስናቸው አካባቢዎች ውጪ በሆኑ ሌሎች ፀውዶች ውስጥ በጥገኛና በሙሉ ፀረፍተነገር ግሶች ላይ ሲገባ በቀደመው ሀሳብ ላይ ተጨማሪ የሆነ ወይም በመጀመሪያው

ዐረፍተንግግር ያልተገለጸ ሌላ ሀሳብ መኖሩን ለማመልከት እንደሚገባ መረጃዎቻችን አሳይተዋል። ይህም ተግባሩ በዚህ ጥናት ከልታየው "ሰዋሰዋዊ እኩልነት ባላቸው" የዐረፍተነገር አካላት መካከል ከሚፈጽመው የማጣረር (coordinate conjunction) ተግባር ጋር ያመሳስለዋል።

(19)...በእጠቃላይ ይህ የሰንበት ትምህርት ቤት በውስጡ ብዙ ሰባክያንን ያፈራ ህብረተሰቡም ስለእግዚአብሔር ቃል እንዲያውቅ ያደረገ በመሆኑ በአካባቢው ካሉት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደኛ ደረጃን የያዘ ትምህርት ቤት ነው።...(004/31)

(20)...ከዚሁ ትምህርት ቤት እራት ቂጥሬ እንድሔድና ከዚያው ሰማር እንዳድር እቤቴ አዘዘኝ።...(005/32)

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች (19፣ 20) "(እ)ና" የገባው ሰዋሰዋዊ እኩልነት (በቅርጽም በመያም) ባላቸው ጥገኛ ሐረጋት መካከል ከቀዳሚው ሐረግ መድረሻ ላይ ነው። እነዚህም ጥገኛ ሐረጋት "...ያፈራና ...ያደረገ" (19)፣ "...እንድሄድና ... እንዳድር..." (20) ናቸው። የመጀመሪያዎቹ (19) እዘማጅ ሐረጉች ሲሆኑ ሁለቱም በጋራ እንድ ዓይነት መሪ (head) ያላቸውና መሪው የወከለው እክል የፈጸማቸውን ተግባራት፣ ሁለተኞቹ ደግሞ በጥገኛ ሐረግነታቸው የሰዋሰዋዊ ባለቤታቸው የፈጸማቸውን ተግባራት የሚገልጹ ናቸው። በሁሉም ቦታ "(እ)ና" የገባው ተጨማሪ ሀሳብ /መረጃ/ መኖሩን ወይም በመጀመሪያው ቃል ወይም ሐረግ ሳይገለጽ የቀረ ሌላ መረጃ መኖሩንና ያም ቀጥሎ የሚቀርብ መሆኑን ማመልከት ነው። በሌላ አገላለጽ ያለውን የመጨመር /የማከል/-የዕከላ ማለት ይቻላል-ዝምድና ማሳየት ነው።

እንባቢው በዚህ ዓይነት አገባብ "(እ)ና"ን ሲያገኝ የቀረና የሚገለጽ መረጃ መኖሩን ይገነዘባል። ከዲስኩር እመልከቹ ቀጥሎ በሚመጣው ቃል፣ ሐረግ ወይም ዐረፍተነገር አማካይነት ቀደም ብሎ ያልተገለጸ አዲስ መረጃ እንደሚገለጽም ይረዳል፤ ዝምድናውም የ"ዕከላ" ወይም የመጨመር ዝምድና እንደሆነ ይገነዘባል።

"(እ)ና" በዚህ መልኩ ሲገባ የተወሰነ ሥፍራ ስለሌለው በ"ጭው" ውስጥ ግንኙነቱንና ሚናውን ወጥነት ባለው ሁኔታ ማሳየት አዳጋች ይመስላል። በመረጃችን መሠረት "(እ)ና" በዚህ ሁኔታ የገባባቸው ቦታዎች የሚገኙት በአብዛኛው በእንቀጽ ውስጥ ነው። ቀሪዎቹም ለምሳሌ፣ 009/31 መ.7፤ 012/32፣ መ.18፤ የመሰሰሉት ከሚያስሩ ግሶች ቀጥሎ ቢገቡም የበለጠ ቅርበታቸው ለቀደመው ዐረፍተንግግር እንቀጽ ነው። ይህ ማለት ግን "(እ)ና" የ"ዕከላ" ዝምድናን በሚገልጽበት አገባቡ ሆኖ በጭብጥ ቦታ ሊመጣ አይችልም ለማለት የሚቻል አይመስልም። በ2.1.2. እንደተገለጸው ቃሉ /ሐረጉ/ ወደ ጭብጥ ቦታ የማይመጣበት ሁኔታ የለምና።

"እና" በመረጃችን ውስጥ ተሠራጭቶ የተገኘው በ"ና"፣ "እና"ና "እናም" ላዕላይ ቅርጾቹ ነው። እነዚህም በተለያዩ ቦታዎች ሲገቡ የተለያዩ ዝምድናዎችን እንደሚያመለክቱ ከላይ በ4.2.2.1 – 4.2.2.4. በዝርዝር ተገልጿል። በ2.1.1. ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከዲስኩር ተንታኙ ተግባራት አንዱ በውሁድ-አሀዱ ወይም በዲስኩሩ ውስጥ በሚታዩት "ተመሳስሎዎች (regularities)፣ ፍቺዎችና ተግባራት መካከል ያለውን ዝምድና መተርጉም (interprete) ነው " (ኑና 1993:7)። ከዚህ በመነሳት በጥናቱ "(እ)ና" በርከት ባሉ ቦታዎች ሲገባ የታዩትን መዋቅራዊ ተመሳስሎዎች በሕግ መሰል ቀመር ለማጠቃለል ተሞክሯል።

በዚህ መሠረት "(እ)ና" እንደ "ይሄድ፣ ይቆም፣ አለን፣ አለች፣ ተነገረ፣ ተበደረ ወዘተ." ባሉት የግስ ቅርጾች ላይ ሲገባ ከጊዜ አንፃር የድርጊቶችንና የሁነቶችን ተለጣጥቶ እንደሚያመለክት በ4.2.2.1 ተገልጿል። ከዚያም በ4.2.2.2. ደግሞ "(እ)ና" እንደ "ይበላል፣ ተደሰተ፣ ተደፍታለች ወዘተ." ባሉት ቅርጾችና "አመጣሁ" በሚለው ግስ ላይ-የ"አመጣሁ" ተመሳሳይ ቅርጾች በዚህ ሥር እይከተቱም-ሲገባ፣ ምክንያትን፣ ሁኔታን፣ ውጤትን በአጠቃላይ ሰበባዊነትን እንደሚያመለክት ተብራርቷል።

በ4.2.2.3.ም እንዲሁ "(እ)ና" ከ"ይሁን" ጋር ሲቀናጅ ("እናም" የሚለው በዐረፍተንግግር መካከል ሲገኝ ይህንን ተግባር ብቻ ስለማይፈጽም በወጥነት መጥቀስ አዳጋች ነው) ከተጠቀሰው ወይም ከተገመተው ሀሳብ የተለየ ተዘማጅ ሀሳብን ወይም ልየታን ለማመልከት እንደሚገባ ተጠቅሷል። በመጨረሻም ከላይ ከተገጹት መዋቅራዊ አካባቢዎች ውጪ በሆኑ ሌሎች መዋቅራዊ አካባቢዎች ሲገባ ተጨማሪ መረጃን እንደሚያመለክት በ4.2.2.4. ተመልክቷል። በአጠቃላይ በሁሉም አካባቢዎች እንደታየው በዐረፍተንግግር መካከል ከሚገኘው "እናም"ና ከአራት ነጥብ ወይም የንበብ ተግታ ቀጥሎ ከሚመጣው "እና" በቀር ከ"ጭው" አንፃር በአንቀጹ ውስጥ እንደሚገኝና በ4.2.2.4 ከተገለጸው ውጪ ባሉት አካባቢዎች ደግሞ ተግባራቱ ተመሣሣይ የሆነ "ጭው" የሚከተል እንደሚመስል በቦታው ተጠቅሷል። በመጨረሻም ለማጠቃለል ከተግባሩ አኳያ የ"እና"ን ሥርጭት በሚከተለው ሠንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል።

ደስኩር እመልከቹ	የደስኩር እመልከቹ ሥርጭት ከተግባር እንፃር										ድምር	
	ተለጣጥቶ		ምክንያት		ልየታ		ፅክለ		ያልተለያዩ			
	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%
(እ)ና/እናም	15	16.30	25	27.17	2	2.17	47	51.10	3	3.26	92	100

4.2.3. የ"(ይሁን)" እንጂ ተግባራት

ቀደም ሲል በ4.1.2.3. እንደተመለከትነው "(ይሁን) እንጂ"፣ ለጥናቱ በተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ በተለያዩ ፀውዶች ውስጥ መግባቱ ተገልጿል። ይህ ደስኩር እመልከቹ በቀደምት የሰዋስው መጻህፍት ውስጥ (ለምሳሌ፣ በመርስዔ ሀዘን ወልደ ቂርቆስና (1948 ዓ.ም.)፣ በተክለማሪያም ፋንታዬ (1957 ዓ.ም.)፣ የሰዋስው መጻህፍት ውስጥ) በጥቅል "በወደረኛ መስተፃምር"፣ በዝርዝር ደግሞ፣ "በእፍራሽ ወደረኛ መስተፃምር" ሥር ተፈርጀ ይገኛል።

በተግባሩም እንደሌሎቹ ወደረኛ መስተፃምራን እኩልነት ያላቸውን ቃለት፣ ሐረጋትና ዐረፍተነሮች ማያያዝና አፍራሽነትን መግለጽ እንደሆነ በነዚሁ መጻሕፍት ተጠቁማል። ሆኖም ለዚህ የመስተፃምር ዓይነት የተሰጠው "በፊት የተነገረውን ሀሳብ የሚቃወም መስተፃምር ነው" (ይትባረክ 1966 ዓ.ም. ገጽ 107) የሚለው ግለፄ መሠረታዊ ጥያቄ እንደሚያስነሰና ችግር ያለበት እንደሆነም በ2.2.1. መጠቀሱ ይታወሰል። ስለሆነም በዚህ ጥናት ከታዩት መረጃዎች እንፃር ግለፄውና ግብሩ የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም። (ዝርሩን ከታች በ4.2.3.1. ና በ4.2.3.2. ይመልከቱ)።

በዚህ መሠረት "(ይሁን)እንጂ" በተሰበሰቡት ውሁድ-አሀደች ውስጥ በተለያዩ አገባቦችና የቋንቋ ፀውድ ውስጥ የሚፈጽማቸውን ተግባራትና የሚያመለክታቸውንም የማነፃፀርና የ"መከድ" ዝምድናዎች ቀጥሎ ለማቅረብ ተሞክሯል።

4.2.3.1. ንፅፅር

በተለያዩ ውሁድ-እህደቶች ውስጥ "ይሁን"ን ሳይጨምር፣ "እንጂ" ብቻውን እየገባ ንጽጽርን ያመለክታል። ሁለቱ ተነፃፃሪዎች በመጀመሪያው - በቀዳሚው - ወይ በሁለተኛው-በተከታዩ-ዐረፍተንግግር ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። ወይም ንጽጽሩ ከውሁድ-እህዱ ውጪ ካለ(ሉ) አካል(ላት) ጋር ሊሆን ይችላል። የሚከተለውን ምሳሌ እንውሰድ።

(21)... ማንያህሉሽ ቢያልፈው በሚያስብለት ከፍተኛ ሀሳብ ደስታ ቢሰማትም ውስጥ ውስጡን ግን ትናደድ ነበር። ወይኔ እግዚአብሔር እረግሞን ነው እንጂ እኔ እንደዚህ የማንንም ምጣድ አገልጋይ ሆኜ እሷ ደግሞ ገና በወጣትነቷ እድሜዋ እንድ እንደወለደች ሞተች እያለች በጣም ትናደድ ነበር።...(008/31)

ከላይ በቀረበው የውሁድ-እህድ አካል የ"እንጂ" አገባብ በቀዳሚው ዐረፍተ ንግግር መጨረሻ ላይ በመሆኑ ሲነበብ የንባብ ተግታ ያለው ከ"እንጂ" ቀጥሎ ሁለተኛው አረፍተ ንግግር ሳይጀምር ነው። በዚህ ሁኔታ ሲገባ በጽሀፈት ጊዜ ከ"እንጂ" በፊት ካለው ግስ ቀጥሎ አራት ነጥብ አይገባም፤ የውሁድ-እህዱም ጠቅላላ ሀሳብ፣ ዐረፍተ ንግግሩን የምትናገረዋ "ማንያህሉሽ" በራሷ ኑሮና "እሷ" ብላ በምትጠራት ሌላ ሴት (ከእጠቃላይ ውሁድ-እህዱ እንደምንረዳው የ"ቢያልፈው" እናት የተናጋሪዋ እህት መሆኗ ነው) እንድ ወልዳ ያለጊዜዋ መሞት የተሰማትን ሀዘንና ምሬት የሚገልጽ ነው።

የምሬቱም መንስዔ ኑሮዋ ከሌላው ኑሮ ጋር ሲወዳደር በጣም ዝቅተኛና ችግር የበዛበት መሆንና፣ የእህቷ የ"ቢያልፈውም እናት እድሜ ከሚገመተው የመሞቻ ዕድሜ" ጋር ሲወዳደር ገና ሆኖ ሳለ በወጣትነቷ እንድ ወልዳ መሞቷ፣ በአጠቃላይም የእህትማማቾቹ ህይወት በተናጋሪዋ እምነት "እግዚአብሔር ከመረቃቸው ሰዎች" ጋር ሲነፃፀር "በእግዚአብሔር እርግማን" ምክንያት የችግር ሕይወት መሆን ነው።

በዚህ መሠረት የ"እንጂ" ተግባር ማነፃፀሪያ የሆነውን መሠረታዊ ሀሳብ በውስጡ ከያዘው ቀዳሚ ዐረፍተንግግር ቀጥሎ የመጣው ዐረፍተንግግር ሀሳብ መነፃፀሩን ከማመልከት ባሻገር "እግዚአብሔር የመረቃቸውማ..." በሚል የቁጭት ስሜት መነገሩንም ጭምር ለአንባቢው መጠቆም ነው።

"እንጂ" በዚሁ ዓይነት የማነፃፀር ተግባር ለመፈጸም በሌላ አካባቢ ሲገባ የመጀመሪያውን-የቀዳሚውን-ዐረፍተንግግር እንቀጽ ወይ ሙሉ በሙሉ ይገድፍና ጭብጡ ከሁለተኛው ዐረፍተንግግር ጭብጥ ጋር፣ ወይ ደግሞ የእንቀጹን ግስ ይገድፍና ከሁለተኛው ጋር

መነፃፀሩን ሊያመለክት ይችላል። በዚህ ጊዜ "እንጂ" በሁለቱ ዐረፍተ ንግግሮች መካከል ይገኛል። ቢሆንም የበለጠ ቀረቤታው ከቀደመው ዐረፍተ ንግግር ጋር በመሆኑ፣ በመጀመሪያው ላይ የተገለጸው ሀሳብ ከሁለተኛው ሀሳብ ጋር ሲነፃፀር የሚመረጥ ወይም የሚደገፍ መሆኑን ጭምር ያመለክታል። የሚከተሉትን መረጃዎች እንመልከት።

(22)... እኔ ልጅቷን እይቻትም አለውቅ ከልጁ ቤት እንጂ ከልጅቷ ቤት በራሱንም ረግጪው አለውቅ። እሷ ግን የሴት ልጅ ዓይን አውጣ ሆና... (005/31)

(23)... ስለሆነም እንድ ሰው ችግር ሲያጋጥመው ችግሩ ችግሩን እንዲመጣው ተቀብሎ መጽናናት እንጂ ሁልጊዜ የደረሰበትን ችግር እያሰበ አለምሮን ማስጪነቅ የለበትም።... (009/31)

በምሳሌ (22) የቀረበው ምንባብ ተናጋሪው ሁለቱን ቤቶች በማወዳደር መልክ እቅርቦ ከ"ልጅቷ ቤት" ይልቅ የ"ልጁን ቤት" እንደሚያውቅ ያስረዳል። ስለዚህ የ"እንጂ"ም ተግባር በሁለቱም ጭብጦች መካከል ያለው ዝምድና የንፅፅር መሆኑን ለእንባቢው ማሳየት ነው። ከላይ እንደተገለጸውም እንቀጹ የተገደፈበት ዐረፍተንግግር፣ "ከልጁ ቤት" የሚለው መስተዋድዳዊ ሐረግ ጭብጥ የሆነበት ቀዳሚ ዐረፍተንግግር ነው። እንዲህ ዓይነት የመገደፍ ሁኔታ የሚያጋጥመው የሁለቱ ዐረፍተንግግሮች እንቀጽ የትርጊሜ ተመሰሳይነት ሲኖራቸው ይመስላል። ምክንያቱም የሁለተኛውን ዐረፍተንግግር እንቀጽ በማየት የመጀመሪያው ዐረፍተንግግር እንቀጽ– የተገደፈው ማለት ነው–ምን ሊሆን እንደሚችል (በምሳሌ (22) ውስጥ የተገደፈው "በራሱን ረግጪ አውቃለሁ" የሚለው እንቀጽ ነው) ለመገመት እደጋች አይሆንም።

በምሳሌ (23) በቀረበው ምንባብ ውስጥ በ"እንጂ" መግባት ምክንያት ከ"መጽናናት" ቀጥሎ መግባት የነበረበት የእንቀጹ ግስ ተገድፏል። ይህም የተገደፈ ግስ ከ"ማስጪነቅ" ቀጥሎ የመጣው የ"የለበትም" ትይዩ ነው። አንባቢውም በቀላሉ ይረዳዋል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚገደፈው ግስ የተነገረበት መልክ እዎንታዊ ሲሆን ያልተገደፈው–በምሳሌው መሠረት "የለበትም" የሚለው–አሉታዊ ነው። በአጠቃላይ በምሳሌ (22)ም ሆነ በ(23) ዓይነት "እንጂ" ሲገባ ተግባሩ መነፃፀርን ማሳየትና የቀደመውም ሀሳብ ተደጋፊ/ተመራጭ ወዘተ. መሆኑን ጭምር ማመልከት ነው። በዚህ ሁኔታ ንፅፅርን ከማመልከት በተጨማሪ "እንጂ" በጭብጥ መዋቅር ውስጥ ስጥው የሆነውንም መረጃ ያመለክታል። ለምሳሌ ከላይ በቀረቡትም ምሳሌዎች በ(21) "የእግዚአብሔር እርግማን"፣ በ(22) "የልጁ ቤት መታወቅ"፣ በ(23) ደግሞ "የችግሩ ችግሩን ማምጣት"፣ ስጥው ናቸው። እንባቢውም እነዚህን ስጥው መረጃዎች በ"እንጂ" አማካይነት ከመጠቆሙም በላይ "ስለዓለም ከለው እውቀት" ወይም በ"ውሁድ–አሀድ ውስጥ ቀድሞ ከተጠቀሰው መረጃ" በመነሳት ፈልፍሎ በማውጣት ይረዳቸዋል (ስለስጥው መረጃ ሃሊዴይ፣ 1985aንና ኑናን፣ 1993ን ይመለከቷል)።

ከላይ በተጠቀሱት ምሳሌዎችም ሆነ በሌሎቹ መረጃዎቻችን ውስጥ በሉት ተመሳሳይ አገባቦች እንደታየው፣ የማነፃፀር ተግባር ሊያመለክት የገባው "እንጂ"፣ ነው እንጂ "ይሁን እንጂ"፣ አይደለም። ከመረጃዎቹም አንፃር ይህ የንፅፅር ተግባር የበለጠ ተዘውታሪ ይመስላል። (ለዝርዝሩ ምዕራፍ መጠረሻ የቀረበውን ሠንጠረዥ ይመልከቱ)።

የማነፃፀር ተግባር በሚገለጽበት ጊዜ "እንጂ" የገባባቸው ጭብጣዊ መዋቅሮች በ"ጭ-1"ና በ"ጭ-3" ጭምር ሊተነተኑ ይችላሉ። የ"እንጂም" አገባብ ከላይ እንደተገለጸው ንጽጽሩን ማመልከት፣ ስጥው የሆነውንና ከንጽጽሩ አንፃር ተደጋፊውን መረጃ መጠቆም በመሆኑ፣ በአብዛኛው በአንቀጹ ውስጥ ነው የሚገኘው። ይህም ቦታው ይመስላል እንዳንዴ የቀዳሚውን አንቀጽ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲገደፍ የሚያደርገው። ግድፈት በማይኖርበት ሁኔታ ግን (ምሳሌ (21)) ከቀዳሚው ዐረፍተንግግር ቀጥሎ ይገባል። በዚህ ጊዜ ግን የንባብ ተግታው ከግሱ ላይ ሳይሆን ከ"እንጂ" ላይ ነው።

4.2.3.2. <u>ልየታ</u>

"እንጂ" ሳይሆን "ይሁን እንጂ"፣ በውሁድ-አሀድ ውስጥ በተለያዩ ዐውዶች ውስጥ ከሚገመተው ሀሳብ ውጪ የሚመጣን ሀሳብ ለማመልከት ይገባል። ከሉት መረጃዎች አኳያ ሲታይ ይኸኛው አገልግሎት ከንጽጽሩ ተግባር በነሰ ሁኔታ የሚዘወተር ይመስላል። "እንጂ" በሚገባበት የንጽጽር ተግባር "ይሁን እንጂ" እንደልታዬ ሁሉ "ይሁን እንጂ" በሚገባበት የልየታ ተግባር ደግሞ "እንጂ" አልታየም።

"ይሁን እንጂ"፣ ከተገኘባቸው አውዶች ውስጥ የሚከተለው ለአብነት ያህል ይጠቀሰል።

> (24)... መኩንን የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወሰደ የፈለገውን ያህል ውጤት በለማግኘቱ በሥራ አጥነት የሚገኝ የ20 ዓመት (ሃያ አመት) ልጅ ነው። <u>ይሁን እንጂ</u> ሥራ አጥነቱን አሜን ብሎ አልተቀመጠም።...(006/31)

የ"ይሁንእንጂ" አገልግሎት ከላይ በመንደርደሪያው እንደተጠቀሰው በሁለቱ ዐረፍተንግግሮች መካከል ያለው ዝምድና የልየታ ዝምድና መሆኑን ማመልከት ነው። በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር ከተሰጠው መረጃ በመነሳት "የሚፈለገው ውጤት እስከልተገኘ" ድረስ በሥራ አጥነቱ እንደሚቀጥል እንበቢ ይጠብቃል። እንዲያውም ይህ መረጃ (24) በዋናው ውሁድ-አሀድ መነሸ ላይ የቀረበ በመሆኑ እንበቢው ከዚህ ከሥራ አጥነቱ ጋር በተያያዘ መልኩ ወይም በሥራ አጥነቱ ላይ ሌላ ችግር/ነገር/ ሳያጋጥመው እንደልቀረ እንበቢ ይገምታል። ሆኖም

ከዚህ ግምት ውጪ የሆነ የተለየ ሀሳብ በሁለተኛው-በተከታዩ-ዐረፍተንግግር በመቅረቡ፣ ሁለተኛው ከመጀመሪያው ግሙት ሀሳብ ይለያል። በመሆኑም በሁለቱ አረፍተንግግሮች መካከል ያለው ዝምድና የልየታ ነው ማለት ይቻላል። ይህን ዝምድናም በላዕላይ ደረጃ ይፉ ያደረገው "ይሁን እንጅ" እንደሆነ በግልጽ ይታያል።

በ"ይሁን እንጂ" ውስጥ ያለው "ይሁን" የሚለው ተቀናጅ በመጀመሪያው-በቀዳሚው-አረፍተንግግር የጭብጥ መዋቅር አንቀጽ ውስጥ የተገለጸውን ዋና ሀሳብ ያመለክታል ማለት ይቻላል። በምሳሌውም (24) መሠረት የመጀመሪያው አረፍተንግግር አንቀጽ ዋና ሀሳብ "ሥራአጥነት" ነው። "ይሁንእንጂ" ውስጥ ያለው "ይሁን"ም የሚያመለክተው ይህንኑ ይመስላል።

"እንጂ" ና "ይሁን እንጂ" በተለያዩ ዐውዶች ውስጥ እንደሚገቡ አለይ ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህም "እንጂ" የንጽጽርን፣ "ይሁን እንጂ" ደግሞ የልየታን ዝምድና ያመለክታሉ። ከተሰበሰቡትም መረጃዎች አንፃር "እንጂ" የሚያሳየውን የንጽጽር ዝምድና "ይሁን እንጂ" አያሳይም፤ "እንጂ" በገባበትም ቦታ፣ "ይሁን እንጅ" ሊገባ አልታየም። በተመሳሳይ ሁኔታም እንዲሁ "ይሁን እንጂ" የሚያሳየውን የልየታ ዝምድና "እንጂ" አያሳይም፤ "ይሁን እንጂ"ም በተገኘበት ዐውድ "እንጂ" ሊገባ አልተገኘም።

ከዚህ በተጨማሪ "እንጂ" በቀደመው ዐረፍተንግግር መጠረሻ ላይ ከሚገኘው የሚያስር ግስ ቀጥሎ መምጣት የነበረበትን አራትነጥብ እንዲቀር ያደርጋል። የንባብ ተግታውም ከግሱ ላይ ተነስቶ "እንጂ" ላይ ያርፋል። ጠቅላላ ሀሳቡም እዚያ ላይ ሊቆም ወይም ሊገታ እንደማይችል ይጠቁማል። "ይሁን እንጅ"፣ ግን የሚገባው የመጀመሪያው ዐረፍተንግግር ከተዘጋና የንባብ ተግታው እንዳበቃ መሆኑን ማስረጃዎቹ አመልክተዋል። ስለዚህ ከ"እንጂ" ይልቅ "ይሁን እንጂ" ሙሉ በሙሉ ግንኙነቱ ከሁለተኛው ዐረፍተንግግር ጭብጥ ጋር ነው ማለት ይቻላል።

"(ይሁን)እንጂ" ከተግባሩ አኳያ ያለውን ሥርጭት የሚከተለው ሠንጠረዥ ያጠቃልለዋል።

ዲስኩር አመልካቹ	የዲስኩር አመልካቹ ሥርጭት ከተግባር አኳያ ተግባራት					
	ንጽጽር		ልየታ		ጠቅላላ ድምር	
	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%
(ይሁን)እንጂ	24	80.00	6	20.00	30	100%

4.2.4. የ"ስለዚህ" ተግባራት

"ስለዚህ"፣ ብቻውን ወይም በመድረሻው ላይ ቅጣይ መስተፃምሩን "-ም" በማከል በተለያዩ አከባቢዎች እንደሚገባ በ4.1.2.4. ተገልጿል። በተጨማሪም "ስለዚህ" በዚህ ጥናት ውስጥ የሚተነተነው በዲስኩር አመልካችነቱ እንጂ በመስተዋድዳዊ ሐረግነቱ* በሚኖረው ሰዋሰዋዊ ሙያ አለመሆኑም ተጠቁሟል።

ጥንታዊ የሰዋስው መፃሕፍት፣ ሌሎቹን መስተፃምራን እንደገለጹት ሁሉ፣ "ስለዚህ"ንም በሚመለከት የሰጡት ግለፄ አለ። ይህ ዲስኩር አመልካች በነዚህ የሰዋስው መፃሕፍት (ለዝርዝሩ 2.2.1.ን ይመልከቷል) ውሰኔ መሠረት ወደረኛ መስተፃምር ሆኖ "በሀሳብ ሰጪ" መስተፃምር ምድብ ሥር ይፈረጃል። ተግባሩንም "አስቀድሞ ለተነገረው ማስረጃ ለመስጠት ወይም ተርጉሞ ለማስረዳት የሚጠመር መስተፃምር ነው" በማለት ይገልጹታል (ይትባረክ ወልደሚካኤል፣ 1966 ዓ.ም.: 107)። በተጨማሪም "የነገሩን አኳኋን በምክንያት ሊገልጽ ምክንያታዊ እንደሚሆን" ያብራራሉ (ጥላሁን በየነ፣ 1965 ዓ.ም.: 58)።

ለሌሎቹ መስተፃምራን ከሰጧቸው ግለፄዎች የ"ስለዚህ" ግለፄ በመጠኑ ተጠያቃዊ ይመስላል። ሊቃውንቱ የተነሱበት አመለካከት ሙሉ በሙሉ ሰዋስዋዊ በመሆኑ የተሟላና ውሁድ-አሀድን መሠረት ያደረገ አይደለም እንጂ አገባቡ በመሠረቱ ከ"ምክንያት" ወይም "ሀሳብ ከመስጠት" ጋር የተያያዘ እንደሆነ በመጠኑ የተረዱት ይመስላል። ሆኖም "ሀሳብ የሚሰጠውም" ወይም "የነገሩን አኳኋን" በምክንያት የሚገልጸው መስተፃምሩ እንደሆነ አድርገው ስለቀረቡት የግለፄ መዘበት ይታይበቸዋል። የዚህ ጥናት ውጤትም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው።

ስለዚህ ቀጥሎ ስለ "ስለዚህ" ተግባራዊ አገልግሎት ከተሰበሰቡት መረጃዎች እንፃር ለመተንተን ተሞክሯል።

4.2.4.1. ምክንያታዊ

ከ"ስለዚህ" ተግባራት ዋነኛውና ብዙ ስርጭት ያለው ምክንያታዊ ዝምድናን መግለጽ ነው። በውሁድ-አሀዶቹም ውስጥ ተደጋግሞ እንደታየው ቀዳሚው ዐረፍተንግግር ለሁለተኛው ዐረፍተንግግር ምክንያት ሆኖ ነው የገባው። ከ"ስለዚህ" አጠቃቀም አኳያ ይህ ሁኔታ በሁሉም ውሁድ-አሀዶች ውስጥ እምብዛም ሲፋለስ ወይም ሲዘበ አይታይም።

---

* ስለ መስተዋድዳዊ ሐረግ አገልግሎት በዬ ይማም 1987 ዓ.ም. ይመልከቱ።

(25)... ሆኖም እንደተለመደው ከባለቤትህ ጋር ወደሽርሽር መሔድህ ተነገረኝ። ስለዚህ ምንም ማድረግ ስላልቻልኩኝ መልዕክት በጉሪቤትህ እስጠምጡ እያዘንኩ ወደቤቴ መመለሴ ትዝ ይለኛል።... (007/31)

በምሳሌ(25) ከቀረበው የ"ስለዚህ" አገባብ እንደምንመለከተው የተናጋሪው "ምንም ለማድረግ አለመቻል" ና "መልዕክት ከጉሪቤት እስቀምጦ በሀዘን ወደቤት መመለስ" ምክንያቱ በመጀመሪያ ዐረፍተንግግር የተገለጸው ተነጋሪ (addressee) በቤቱ አለመገኘት ነው። ስለሆነም በሁለቱ ዐረፍተንግግሮች መካከል ያለው ዝምድና የምክንያት ዝምድና ነው። ይህንንም ዝምድና በይፋ የሚያውጀው "ስለዚህ" ነው።

በእጠቃላይ፣ "ስለዚህ" በምሳሌ (25) ዓይነት በገባባቸው አውዶች መሠረት የሚያመለክተው (ጥቂት የተለየ ተግባር ከሚያመለክቱት አገባቦች በቀር) በአብዛኛው ይህ ኑ የምክንያት ዝምድናን ነው። አገባቡም በሁሉም ቦታ(ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል)በሁለቱ ዐረፍተንግግሮች መካከል ሲሆን፣ የሚገኘውም ከሁለተኛው/ከተከታዩ ዐረፍተንግግር መነሻ ላይ ነው። ከታዩት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ከ"ስለዚህ" ቀድሞ የሚመጣ ምንም ዓይነት የቋንቋ አለባ የለም። ከዚህ ሌላ ግን በመድረሻው እንዳንድ ጊዜ "–ም" የተባለውን ቅጣይ መስተዓምር የማስቀጠል ልማድ እንዳለው ጥቂት መረጃዎች ጠቁመዋል።

በእረፍተንግግር መካከል ሲገባም የበለጠ ንግኙነት ያለው ምክንያቱን ከሚጠቁመው ዐረፍተንግግር ጋር ሳይሆን ውጤቱን ከሚገልጸው ዐረፍተንግግር ጋር ነው። በጭብጥ መዋቅርም ውስጥ ከ"ስለዚህ" ቀጥሎ የሚገባው አካል የቀጣዩ ዐረፍተንግግር ጭብጥ ነው። ስለዚህ "ስለዚህ"፣ ከጭብጡ ጋር ግንኙነት አለው ማለት ይቻላል። የምክንያትን ዝምድና ለማመልከት "ስለዚህ" ሲገባ የሚኖረውም "ጭ ው" በእንድ ወጥነት "ጭ ው–3" የሚከተል ይመስላል። የምሳሌ (25) "ጭው" እንደሚከተለው ሊተነተንና የሌሎችም ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

ምሳሌ (25)



ሥዕል 6፣ የምሳሌ 25 ጭብጣዊ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ

4.2.4.2. ልዩ ልዩ

በዚህ ንዑስ ክፍል የሚቀርቡት የ"ስለዚህ" ተግባራት ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ እንዳንድ መረጃ ያላቸው ብቻ ናቸው። እንደተግባርም ሊተነተኑ የቻሉበት ምክንያት የእራሚዎች ስምምነት ነው። (ዝርዝሩ በቦታው ይቀርባል)። በመሆኑም "ስለዚህ" ተጨማሪ ሀሳብ ለመስጠትና ጊዜ-ጠቀስ የሆነ ዝምድና ለማመልከት ሲገባ ቀጥሎ ለማመልከት ተሞክሯል።

ሀ. ተጨማሪ

በውሁድ-አሀድ ውስጥ ቀደም ብሎ ከተሰጠው መረጃ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል አዲስ መረጃ ለአንባቢው ለማቅረብ /ለመስጠት/ ተከታይ ዐረፍተንግግር ሲኖር ይህንኑ የመጨመር ዝምድና ለመግልከት "ስለዚህ" ይገባል። ይህ እጠቃቀምም ትክክል ለመሆኑ ከሰባቱ እራሚዎች እምስቱ ስምምነታቸውን ገልጸዋል። ለዚህ የ"ስለዚህ" ተግባር ብቸኛው ዋቢ በሚከተለው ምሳሌ (26) ቀርቧል።

> (26)... ይህ የመጨረሻ ልጃቸው ከጉናቸው ሆኖ እንዲጽናኑ የሚያደርገው ምክር በእጅጉ ያስደንቃቸዋል። ስለዚህም ቢሆንኝ ከዚያች በችግርና በሀዘን ከተሸበበች ጉጂ ከእናቱ ጋር አብሮ ሲኖር የሚተዳደሩበት ስላልነበራቸው የግድ ጫማ እየቀባ ለመኖር አሰበ።... (013/31)

ከላይ በ(26) እንደቀረበው የ"ስለዚህም" አገባብ ምክንያታዊ እንዳልሆነ የሁለቱ ዐረፍተንግግሮች ሀሳብ ያመለክታል። የምክንያት ዝምድና ቢሆን ኖሮ እንድም የመጀመሪያው ለሁለተኛው ምክንያት መሆን፤ እሊያም የመጀመሪያው ለሁለተኛው መከሰት የተመቻቸ ሁኔታ መኖር የጠቀሰው ነገር መኖር ነበረበት። የተገለጸው ነገር በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር ውስጥ "የመጨረሻው ልጅ የሚያደርግላቸው ምክር እንዳስደነቃቸው" ነው። በሁለተኛው ደግሞ "ቢሆንኝ" (በርግጥ የመጨረሻ ልጅ የተባለው እሱ ነው) "ችግራቸውን ለመቅረፍ ጫማ ለመጥረግ ማሰቡ" ተገልጿል። "ማድነቅ" ቢያንስ በዚህ አገባብ ደግሞ፤ ለጫማ መጥረግ ሐሳብ" ምክንያት /ሰበብ/ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ መረጃው የምክንያት ተዘምዶ በሁለቱ የውሁድ-አሀድ አላባዎች መካከል አለ ለማለት አያስችልም።

ሊሆን የሚችለው፤ መረጃውም እንደሚያመለክተው የመጀመሪያው ዐረፍተንግግር ጭብጥ "ይህ" የሚለው ነው። ይህ ደግሞ ወደፊትም ወደኋላም የሚጠቀመው "የመጨረሻውን ልጃቸውን" ነው። የ"መጨረሻ ልጅ" የተባለው ደግሞ "ቢሆንኝ" ነው። "ቢሆንኝ"ም በበኩሉ የሁተኛው ዐረፍተንግግር ጭብጥ ነው። ስለዚህ በእጠቃላይ የቀረቡት ሁለት መረጃዎች የሚያትቱት ስለ "ቢሆንኝ" የተለያዩ ገጽታዎች ነው። በመሆኑም የሁለቱ ዐረፍተንግግሮች ዝምድና

መረጃ የመጨመር፣ የማከል /የዕከላ/ ዝምድና ነው። የ"ስለዚህም" ተግባር ይህንኑ ይፋ ማድረግ ነው። "ስለዚህም" የሚለውን አውጥተን "ቢሆነኝ" ላይ "-ም" ን ብንጨምር ምናልባት ይህ ከላይ የተጠቀሰው ዝምድና ግልጽ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አለ።

ይህ ዝምድና ከ"ጭው" እንፃር በሁለት መንገድ ሊተነተን የሚችል ይመስላል። እሁን በሉት ሁለት ዐረፍተንግግሮች (ምሳሌ (26)) መሠረት ብቻ ከተመለከትነው "ጭው-2"ን የሚከተል ይመስላል። ምክንያቱም የመጀመሪያው ዐረፍተንግር ጭብጥ ሆነ የሁለተኛው ዐረፍተንግግር ጭበጥ ያው "ቢሆነኝ" ነው። ይህ ዓይነት "ጭው" በአማርኛ ውስጥ እንደልብ እንማይገኝ ጋሰር (1984) ይገልጻሉ። ሆኖም የ"ጭው-2" ፅንሰ ሀሳብ (ዝርዝሩ በ2.1.2. ተገልጿል) አንዱ ጭብጥ በተለያየ መንገድ በተደጋጋሚ በሚመጡ የጭብጥ መዋቅሮች ውስጥ ጭብጥነቱን ሳይለቅ በተለያዩ አንቀጾች የሚገለጽ መዋቅር ነው (ለዝርዝሩ ዴነሽ፣ 1974፤ ጋሰር፣ 1984 ይመለከቷል)። ይህም የሚያመለክተው ይህንኑ ይመስላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከአጠቃላይ የደስኩር ጭብጥ ስንነሳ ዋና ጭብጡ "ቢሆነኝ" ሳይሆን "እናቱና የቤተሰቡ እኗኗር" ነው። ከዚህ አንፃር ከየነው የምሳሌ (26)ም "ጭው"፣ "ጭው-3" ነው የሚሆነው። (ለዝርዝሩ 2.1.2.ን ይመለከቷል)። ያም ሆነ ይህ ከለው መረጃ አንፃር በተግባሩም ሆነ በሚከተለው "ጭው" አንፃር አስተማማኝ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ ተጨማሪ ጥናት የሚጋብዝ መሆኑን መጠቆም ተገቢ ነው።

ለ. <u>ተለጣጥቆ</u>

"ስለዚህ" ከተዘወተረው የምከንያት ዝምድና በተለየ የጊዜ ወይም የሁኔቶችን ተለጣጥቆ ለማመልከት ይገባል። ሆኖም ያለው መረጃ አንድ አጋጣሚ ብቻ በመሆኑ የአራሚዎችን ስምምነት ማየቱ ተገቢ ነው። ቁጥሮ በ(27) የቀረበውን የ"ስለዚህ"ን አጠቃቀም ከሰባቱ አራሚዎች አራቱ ሲስማሙበት ሦስቱ ተቃውመዋል። ከሰባት ሰው ደግሞ ሦስት ቀላል ቁጥር አይደለም። በመሆኑም ይህ አጠቃቀም በሰፊ መረጃ ተጨማሪ ጥናት የሚጋብዝ መሆኑን አበክሮ መግለጽ ይገባል።

እዚህ ላይ ግን አራቱ አራሚዎች-ብዙሃን በመሆናቸው-በተስማሙበት መሠረት የታየውን ሁኔታ ለመቃኘት ተሞክሯል። መረጃው ቁጥሮ ይቀርባል።

(27)... ከልፋቴ አንፃር ጥሩ ውጤት በማምጣቴ ተደስቻለሁ።
<u>ስለዚህ</u> አሁንም በአመጣሁት ነጥብ አማካኝነት በከተቤ
መምህራን ትምህርት ከሌጅ ተመድቤ ትምህርቴን
እየተከታተልኩ እገኛለሁ።... (015/32)

በምሳሌ (27) በቀረበው መረጃ መሠረት "መደሰቱ፣ ከሌጅ ለመግባቱ" ምክንያት ሊሆን አይችልም። ይህንንም "ለከሌጅ መግባት" ምክንያት ወይም የተመቻቸ ሁኔታ፣ "ያመጣው ነጥብ" እንደሆነ በሁለተኛው ዐረፍተንግግር ውስጥ ተጠቅሰ ይገኛል። ስለዚህ በነዚህ ሁለት ዐረፍተንግግሮች መከከል ሊኖር የሚችል ዝምድና የቅደም ተከተል ጉዳይ ብቻ ነው። "ደስታው መቼ ነው?" ጥሩ ውጤት ያመጣበት ወቅት ነው። ያም ወቅት የብሔራዊ ፈተና ውጤት የሚገለጽበትን እማከይ የጊዜ ክልል ያመለከታል። ይህ ደግሞ ከከሌጅ መግባት በፊት የሚሆን ነው።

ከዚህ በኋላ የሚመጣው ወደ ከሌጀች መመደብ በመሆኑ የከሌጅ መግባቱ ሂደት ከተናጋሪው-ከተራኪው-"ደስታ" ቀጥሎ የተከሰተና ተከታይ ክንውን ለመሆኑ ሁለተኛው ዐረፍተንግግር ዋቢ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በሁለቱ መከከል ያለው ዝምድና ከጊዜ ጋር የተዘመደ ስለሆነ የተለጣጥቆ ዝምድና ነው ማለት ይቻላል። የ"ስለዚህ"ም ተግባር የተለጣጥቆ ዝምድናውን ለእንባቢው መግለጽ ነው።

ይህ መረጃ ግን ስለሚከተለው የ"ጭው" ዓይነት እፍግልቆ ለመናገር፣ ከመረጃው እንድኑት የተነሰ አደጋች ነው። ምሳሌ (27)ን ብቻ በተመለከተ ግን ቀደም ሲል በ"ስለዚህ" የምክንያት አገልግሎት ላይ የገለጽነውን "ጭው-3" የሚከተለው ይመስላል።

"ስለዚህ"፣ ብቻውንም ሆነ "-ም" ቅጣይ መስተፃምርን-- በመረጃዎቹ ውስጥ ያለው ስርጭት ጥቂት ቢሆንም--በመድረሻው በማከል በአገልግሎት ላይ ይውላል። የ"ስለዚህ" አጠቃቀም በሁሉም ውሁድ-አሀደች ውስጥ አንድ ወጥ ነው፤ በሁሉም ቦታ በዐረፍተንግግሮች መከከል፣ ከሁለተኛው ዐረፍተንግግር መነሻ ላይ ነው የሚገኘው።

በዚህ አገባቡም ያለው አገልግሎት ከተገኘባቸው ዐውደች በእብዛኞቹ የምክንያት ዝምድናን ማመልከት ነው። በጥቂት ሥፍራዎች ግን በ4.2.4.2. እንደተገለጸው የመጨመርን ወይም የእከላንና የተለጣጥቆን ዝምድና ያመለክታል።

"ስለዚህ" በዐረፍተ ንግግር መከከል ላይ ሲገኝም የበለጠ ቀረቤታ ያለው ለሁለተኛው አረፍተንግግር ጭብጥ ነው። ይህም ጭብጥ በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር ውስጥ በተጠቀሰው ሀሳብ ምክንያትነት ተጠቃሚ ወይም ተጉጂ የሆነው ወይም በጥቅሉ የተከሰተው ውጤት ቀዳሚ ትኩረት የሆነ አካል ነው። በጭብጥ መዋቅር ውስጥ በምክንያት ዝምድና አመልካችነቱ የት ቦታ እንደሚገኝም በቦታው ተጠቁሟል። በእብዛኛውም፣ የሚከተለው "ጭው-3"ን እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክቷል።

በ4.2.4.2.የተጠቀሱት ሁለት ተግባራት በበርካታ መረጃ የተደገፈ ጥናት የሚጋብዙ መሆናቸውም በቦታው ተጠቁሚል። ምክንያቱም ለዚህ ጥናት ከተሰበሰቡት መረጃዎችና "ስለዚህ"ም ከተገኝበቸው እውደች ውስጥ እንዳንድ ጊዜ ብቻ የታዩ በመሆናቸው በሁሉም መልክ ለማጠቃለል አስቸጋሪ ስለሆኑ ነው። እሁን በተገኙበት ቦታና ተግባር ግን ከግማሽ በላይ የሆኑ አራሚዎች በመስማማታቸው ተግባራቸው በቦታው ተተንትኗል። ለማጠቃለል "የስለዚህ"ን ሥርጭት ከተግባር እንፃር ቀጥሎ በሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል።

የዲስኩር እመልክቹ ሥርጭት

ዲስኩር	ምክንያት		ልዩ ልዩ		ጠቅላላ	
እመልክች	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%
ስለዚህ(ም)	21	91.30	2	8.70	23	100

4.2.5. <u>የ"ከዚያ*(-)"ተግባራት፤</u>

"ከዚያ(-)" የሚለው ቃል/ሐረግ በ4.1.2.5. እንደተመለከተው በይበልጥ የሚታወቀው በመስተዋድድ ሐረግነቱ (ከ-እዚያ ወይም ከ-ያ-ቦታ ማለት ስለሆነ (ባዬ፤ 1987ን ይመለከቷል)) በዐረፍተነገር መዋቅር ውስጥ በሚፈጽመው ሰዋሰዋዊ ሙያው ነው። በሰዋሰዋዊ ሙያውም ከፍሉ ከተውሰከሰ ነው። ቀደምት የሰዋስው ሊቃውንትም በዚህ ይስማማሉ (ተከለማሪያም ፋንታዬ፤ 1957 ዓ.ም.፤ ጥላሁን በየነ፤ 1965 ዓ.ም.፤ ይትባረክ ወልደሚካኤል፤ 1966 ዓ.ም.)።

ከዚህ በስተቀር ግን በአንዳቸውም የሰዋስው መጽሐፍ ውስጥ "ከዚያ" በመስተፃምርነትም ሆነ በሌላ ሙያ ሊያገለግል እንደሚችል የሚጠቁም ምንም ፍንጭ የለም፤ እንዲያውም በመስተፃምራን ዝርዝር ውስጥ ጠርሰ የለም። ይህም በመሆኑ "ከዚያ" በጽሑፍም ሆነ በንግግር በሚተላለፉ መረጃዎች ውስጥ ስላለው አገልግሎት እስካሁን የሚታወቅ ነገር አልነበረም ማለት ይቻላል።

---

* ሀሊዴይና ሀሰን (1978) "ከዚያ"ንና የመሰሉትን ቃላት/ሐረጋት ከለቸው ሰዋሰዋዊ ሙያ ውጪ "መስተፃምርነትም" ተግባር ስለሚፈጽሙ መስተፃምራዊ ተውሰከ ግስ (conjunctive adverbs) ብለው ይጠሯቸዋል።

ስለሆነም ይህ ጥናት ከሰበሰባቸው ጽሑፋዊ መረጃዎች አኳያ የ"ከዚያን ውሁድ-አህዳዊ አገልግሎት ለመተንተን ይሞክራል። "ከዚያ"፣ ከሳይ እንደተጠቀሰው የቋንቋው መዋቅር አካል በመሆኑ ሰዋስዋዊ ተግባር ቢኖረውም በዚህ ጥናት መረጃዎች ውስጥ እንደታየው ከታወቀው መዋቅራዊ በታውና ሰዋስዋዊው ሙያው ፈቀቅ ብሎ ውሁድ-አህዳዊ ተግባር ሲፈጽም ይታያል። በመረጃ ውሁድ-አህዶቻችንም ውስጥ የታየው ተግባር ተለጣጥቆን ማመልከት ነው።

<u>ተለጣጥቆ</u>

"ከዚያ" ብቻውን በውሁድ-አህድ ዐረፍተንግግሮች መከከል ሲመጣ ከሳይ እንደተገለጸው የድርጊቶችን ወይም የሁነቶችን ተለጣጥቆ ያመለክታል። ሆኖም በተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ "ከዚያ" ብቻውን በገባቸው ዐውደች እንደታየው ተለጣጥቀው የሚፈጸሙት ድርጊቶች ወይም የሚታዩት ሁነቶች የግድ የሆነ ተጠየቃዊ የቅደም ተከተል ዝምድና አይታይባቸውም። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

(28)... ተስፋ በለመቁረጥ በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ተነስቶ
ከቤቷ እከባቢ በመሔድ ወደ ት/ቤት ለመሔድ ከቤቷ
ስትወጣ እያት። ተከትሏት ወደ ት/ቤት ሄደ። <u>ከዚያ</u> ምን
ልበለት ይሆን? እያለ ተጨነቀ።... (013/31)

በምሳሌ (28) በቀረበው መረጃ "ከዚያ" በሁለቱ ዐረፍተ ንግግሮች መከከል ገብቶ ከጊዜ አንፃር ያለውን ተለጣጥቆ ያሰያል። ሆኖም በሁለተኛው አረፍተንግግር የቀረበው መረጃ ከመጀመሪያው ለጥቆ መምጣቱ ተጠያቂው ዝምድና ኖሮት ሳይሆን ቀጥሎ የታየ ከስተት(ሁነት) በመሆኑ ነው። ምክንያቱም የመጀመሪያው አረፍተንግግር የሚገልጸው የተለያዩ ድርጊቶች በቅደም ተከተል ተከታትለው መፈጸማቸውን ነው። ሁለተኛው ዐረፍተንግግር የሚገልጸው ደግሞ "እሱ" ያለበት ሁኔታ በመጀመሪያው አረፍተንግግር ከተገለጸው የመጨረሻ ድርጊት ቀጥሎ የታየ ነው። ቢሆንም በመጀመሪያው አረፍተንግግር ውስጥ እንደተገለጹት ድርጊቶች ቅደም ተከተል ተከትሎ የመጣ በለመሆኑ ተጠያቂነት አለው ለማለት አይቻልም። በመሆኑም በመጀመሪያውና በሁለተኛው አረፍተንግግር መከከል ያለው ዝምድና የጊዜ ተለጣጥቆ ዝምድና ነው ማለት ይቻላል።

ከ"ከዚያ" በተጨማሪ "ከዚያ በኋላ"ም እንዲሁ የጊዜ ተለጣጥቆ ዝምድናን እንደሚያመለክት ማስረጃቹ ያረጋግጣሉ።

(29)... ይህም ሐሳቡ የምትማርበትን ትምህርት ቤት ጠይቆ
ትምህርት ቤት በምትገባበትና በምትወጣበት ሰዓት ጠብቆ

ልጅቷን ማነጋገር ነው ብሎ ወሰነ። ከዚያ በኋላ ልጅቷ
በምትማርበት ትምህርት ቤት በመቆም በምትወጣበትና
በምትገባበት ሰዓት ይጠብቅ ጀመር።... (010/31)

"ከዚያ በኋላ"፣ በዚህ አገባቡ የሚያመለክተው ካለይ እንደተጠቆመው ከመጀመሪያው ድርጊት ፍፃሜ ቀጥሎ ባለው ጊዜ፣ ሌላ የተፈጸመ ወይም የታየ ክስተት መኖሩን ማሰየት ነው። ስለዚህ ይህም እንደ "ከዚያ" የጊዜ ዝምድናን ያመለክታል። ከ"ከዚያ በኋላ" ሌላ በተሰበሰቡት ውሁድ-አሀደች ውስጥ በርከታ ሥርጭት ያለው "ከዚያም" የሚለው ቅርጽ ነው።

"ከዚያም"፣ ከሁለቱ ቅርጸች የሚለየው በለ፩ ላይ በያዘው ቅጣይ መስተፃምር-"ም" ነው። ቅጣይ መስተፃምሩ ከጊዜ ጋር ዝምድና የለውም። በ2.1.2. እንደተገለጸው "-ም" ያለበት አለባ በቀደመው አረፍተንግግር ውስጥ የሚዘመደው አለባ (related element) አለው። የመረጃ ሂደት ቀጣይነትንም (continuity) ያመለክታል (ለዝርዝሩ ጋሰር፣ 1984ን ይመለከቷል)። ይሁንና በ"ከዚያም" ላይ የገቢውን "-ም" ተግባር ከጋሰር (1984) ጥናት ውጤት ጋር ያለው ስምምነት ወይም ልዩነት መርመር የዚህ ጥናት ትኩረት ባለመሆኑ አይመለከተውም፤ ነገር ግን "ከዚያም" ከ"-ም" ጋር በመነገሩ ምክንያት ከሌሎቹ ("ከዚያ"፣ "ከዚያ በኋላ") በተለየ የሚያመለክተውን ተጨማሪ ስሜት መግለጽ ይቻላል። በመሆኑም "ከዚያም" በገባባቸው አውዶች የጊዜ ዝምድናን ከማመልከት በተጨማሪ በሁተኛው ዐረፍተንግግር የተገለጸው ጉዳይ ከየትኛው ጊዜ ቀጥሎ እንደተፈጸመ ለይቶ የሚያመለክት ይመስላል። እስቲ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

(30)... አልማዝም በደረቀው ሌሊት ብቻዋን ስታነባ ከቆየች
በኋላ ለመሞት ወሰነች። ከዚያም በምን ራሷን ማጥፋት
እንደለበት ስታስብ ከቆየች በኋላ ከትራሳቸው ባለው የማብሪያ
ማጥፊያ ገመድ ላይ ባለው የተሳጠውን ኤሌክትሪክ ጠብጣ
ለመሞት ወሰነች...(018/31)

ከላይ በምሳሌ (30) በቀረበው መረጃ ውስጥ በሁለቱ ዐረፍተንግግሮች የተገለጹት ድርጊቶች የጊዜ ብቻ ሳይሆን የድርጊትም ተለጣጥቶ አላቸው። የመጀመሪያው ሳይፈጸም ሁለተኛው ሊፈጸም አይችልም። ስለዚህ በመጀመሪያው አረፍተ ንግግር የተገለጸው ድርጊት ለሁለተኛው መፈጸም ቀዳሚ ሁኔታ ነው። ምክንያቱም መረጃው እንደሚያሰየው ለ"መሞት ከወሰነች" በኋላ ነው ራሷን "ስለምታጠፋበት ዘዴና መሣሪያ ማሰብ" የቀጠለችውና ከመጨረሻው ውሳኔ ላይ ለመድረስ የቻለችው። በመሆኑም በዚህ መልክ የሚገለጹ ድርጊቶች ወይም ሁነቶች ውስጣዊ የሆነ ተጠየቃዊ ዝምድና አላቸው ማለት ይቻላል።

በዚህ ሁኔታ በሁለቱ አረፍተ ንግግሮች መካከልም የገባው "ከዚያም" የሚያመለክተው ከጊዜ አንጻር የተዘማጅ ድርጊቶችን ተጠየቃዊ ተለጣጥቶ ነው። በተጨማሪ "ከዚያም" በቅጹ ከሌሎቹ በመለየቱ ይመስላል (በአገባብ ልዩነት አልታየም) የድርጊቶችን መቆለፍና የትኛው

ድርጊት ከየትኛው ድርጊት ቀጥሎ መፈጸሙን ለይቶ ያመለክታል። ከምሳሌው (30) አንፃር የ"መሞቻ ዘዴና መሣሪያ ፍልጋው፣ ለመሞት ከመወሰን" ድርጊት ቀጥሎ መምጣቱን "ከዚያም" ነጥሎ ያመለክታል።

ከጭብጥ መዋቅር አኳያ ሲታይ ግን በሦስቱም ቅርጸች መካከል ልዩነት አይታይም። በውሁድ-አሀደቹ ውስጥ እንደታየው የሁሉም አገባብ በዐረፍተ ንግግሮች መካከል፣ በሁለተኛው አረፍተንግግር መነሻ ላይ ነው። በመሆኑም የበለጠ ቀረቤታ ያላቸው ለሁለተኛው አረፍተንግግር ጭብጥ ነው። ይህ ደግሞ በቀዳሚው አረፍተንግግር የተገለጸው ድርጊት ተከታይ ድርጊት ነው። ከመረጃውም ይዘት አኳያ ሲታይ ከ"ስጥው" መረጃ ጋር ሳይሆን ከአዲሱ መረጃ ጋር ነው የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው። ከ"ጭው"ም ውስጥ የበለጠ የሚስማማው "ጭው-1" ነው ማለት ይቻላል። የ(29) ና የ(30) "ጭው" የሚከተለውን ይመስላል።



ከላይ እንደቀረበው "ከዚያ"፣ "ከዚያ በኋላ"ና "ከዚያም" በውሁድ-አሀድ ውስጥ ያላቸው ተግባር ተዘማጅና ተመሣሣይ ነው ማለት ይቻላል። ሁሉም የሚያመለክቱት ተለጣጥቆን ነው። ነገር ግን በለቸው የቅርጽ ልዩነት ይመስላል የተለጣጥቆው ዓይነት በመጠኑ ሲለያይ ይታያል። "ከዚያ"ና "ከዚያ በኋላ" የጊዜን ተለጣጥቆ ሲያሰፉ፣ "ከዚያም" ከጊዜ ተለጣጥቆ በተጨማሪ የድርጊቶችን ተጠየቃዊ ተለጣጥቆ ያመለክታል። ይህም መጠነኛ ልዩነት ሊታይ የቻለው ከቅርጻቸው መለያየት፣ በተለይም "ከዚያም" ላይ ያለው "-ም" ተጽዕኖ ይመስላል። ይህ ግን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ትኩረት ባለመሆኑ በዝርዝር አልታየምና ለጥናት የሚጋብዝ ሀሳብ ነው።

በጭብጥ መዋቅር አኳያ የሁሉም ቅርጸች ግንኙነት ከሁለተኛው ዐረፍተንግግር ጭብጥ ጋር ነው-ማለትም ከ"ከዚያ(-)" ቀጥሎ የሚመጣው የቋንቋ አላባ የተከታዩ የጭብጥ መዋቅር ጭብጥ ነው። በመረጃው መዋቅር ወይም እደረጃጀት አንፃር "ከዚያ(-)" የሚያመለክተው ጭብጣዊነት ያለውን አዲስ መረጃ ነው። ስለዚህ እንደጭብጥም ሁሉ "ከዚያ(-)" ግንኙነቱ

ከአዲስ መረጃ ጋር ነው ማለት ይቻላል። በጥቅሉ በ"ጭ ው" ረገድ ሀሉም በተመሰሰይ በ"ጭው-1" የተጠቀሰውን እሳቤ ይከተላሉ ማለት ይቻላል።

4.2.6. <u>የ"ደግሞ" ተግባራት፤</u>

"ደግሞ"፤ በቅርጹ ሲታይ የ"ደገመ" ግስ ቦዝ* ቅርጽ (በላ=በልቶ፤ ሄደ=ሄዶ ወዘተ. እንዲሉ) ነው ማለት ይቻላል። ይህም የዚህ ጥናት ትኩረት ባለመሆኑ እንደማይመለከተው በ4.1.2.6. ተገልጿል።

በአማርኛ ቋንቋ ልማዳዊ የሰዋሰው መፃሕፍት ውስጥ "ደግሞ" ምድቡ "አጫፋሪ" ወይም "አደጋሚ" ከሚባሉት የወደረኛ መስተፃምራን ዓይነት ውስጥ ነው (ተከለማሪያም ፈንታዬ፤ 1957 ዓ.ም.፤ ይትባረክ ወልደሚካኤል፤ 1966 ዓ.ም. ይመለከቷል)። በነዚሁ መጻህፍት ውስጥ ስለአጫፋሪ ወደረኛ መስተፃምር የተሰጠው ግለጌ "አጫፋሪ የተባለው እንዱንና ሌላውን ቃል የሚያጋጥም ነው፤ አስረኛ :-እርሱ ብልህ ነው፤ አንተ <u>ደግሞ</u>።" (መርስዔ ሀዘን ወልደቂርቆስ፤ 1948 ዓ.ም.: 146)። በተማሣሣይ ሁኔታ ተከለማሪያም ፈንታዬ (1957 ዓ.ም.) አጫፋሪን፤ "በሀሳብ የሚመሰሰሉ ነገሮችን ያያይዛል" (ገጽ 76) ብለው ይገልጹታል። በተጨማሪም ከዘረዘሯቸው መስተፃምሮች ውስጥ ደግሞ፤ "ደግሞ" አንዱ እንደሆነ ተመልክቷል።

ሆኖም፤ "ደግሞ" በውሁድ-አሀድ ውስጥ ከለው ተግባር አኳያ ሲታይ የልማዳዊ ሰዋሰው መፃህፍቱ ግለጌና ተግባሩ በእጅጉ አይጣጣሙም። ምክንያቱም ከላይ በጠቀስናቸው በሁለቱም መፃህፍት የተጠቀሰው ተግባር—"ቃላት ማጋጠም"ና በ"ሀሳብ የሚመሰሰሉ ነገሮች ማያያዝ"—ግልጽነት የሚጐድለው ከመሆኑም በላይ፤ በዚህ ጥናት እንደታየው ተግባሩ ከዚህ የሰፋ ነው።

ለጥናቱ በተሰበሰቡት ተራኪ ውሁድ-አሀዶች ውስጥ "ደግሞ" በገባባቸው አውዶች ያለው ተግባርና የሚያመለክታቸውም ዝምድናዎች ንጽጽር፤ ተጨማሪ ሀሳብና ምክንያታዊ ሆነው ተገኝተዋል። ዝርዝሩ ቀጥሎ በቅደም ተከተል ቀርቧል።

---

* "ደግሞ" የደገመ ቦዝ አንቀጽ ተደርጐ ብዙ ጊዜ ይወሰዳል። ጋሰርም (1984) ይህንኑ ይገልፃሉ። በሰዋሰው መፃህፍትም ተደጋግሞ የሚገለጸው የቦዝ ቅርጽ ይኸው ነው። (ለእብነት ያህል ይትባረክ ወ/ሚካኤል፤ 1966 ዓ.ም. ይመለከቷል)። ሆኖም ከቋንቋው የዐረፍተነገር ባለቤትና ግስ ስምሙነት ሕግ አንፃር ትክክል የማይሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለምሳሌ "እሱ ደግሞ"፤ "እኔ ደግሜ"፤ "እሷ ደግማ" ሲባል ቦዝነቱ እያጠያይቅም፤ ግን "እሷ ደግሞ ምን መሆኗ ነው?" ወይም "እኔ ደግሞ..." ሲባል ከባለቤቱ ጋር ያለመስማማት ይታያል። ስለዚህ ዲስኩር እመልከቹ (መስተፃምሩ) "ደግሞ" እውን የ"ደገመ" ቦዝ ቅርጽ ነው? የሚለው ጥያቄ ለጥናት የሚጋብዝ ነው።

4.2.6.1. ንጽጽር

"ደግሞ" በውሁድ-እሀድ ውስጥ በተለያሉ በታዎች በመግበት ከሚያሰያቸው ዝምድናዎች አንዱ የንጽጽር ዝምድና እንደሆነ መረጃዎች ያሰያሉ። ንጽጽር፣ ቀደም ብሎ በተለያዩ በታዎች እንደተገለጸው፣ የሁለት አከሳትን መወዳደር፣ መነፃፀር ወዘተ. የሚገልጽ የዝምድና ዓይነት ነው።

(31)... እኔ እንደዚህ የማንም ምጣድ አገልጋይ ሆኜ እሷ ደግሞ ገና በወጣትነቷ እድሜዋ አንድ እንደ መለደች ሞተች። (008/31)

ምሳሌ (31) እንደሚያሰየው የ"ደግሞ" አገባብ ከዐቢይ ሐረጉ (main clause) ጭብጥ ቀጥሎ ነው። በዚህም አገባቡ "እሷ" የሚለው ቃል ጭብጣዊነት እንደለው ከማመልከቱም በሳይ የንጽጽር ዝምድናን ይጠቁማል። ንጽጽሩም "በተናጋሪዋ (እኔ)"ና በ"እሷ" (ከ"ደግሞ" በፊት የተገለጸችው) መከከል ያለ ነው። በዚህም አንዳቸውም የተሸለ ሕይወት እንደልኖሩ ያመለከታል። እንድምታውም የ"ሁለታችንም ሕይወት ሲነጻጸር ያንዳችንም እንኳ የተሸለ አይደለም፣ እሷም ያለዕድሜዋ ሞተች፣ የእኔም ኑሮ የመከራ ኑሮ ነው" የሚል ነው። ስለዚህ የ"ደግሞ" አገባብ የንጽጽሩን ዝምድና ይፈ ያደርጋል። በተመሣሣይ ሁኔታ የንጽጽርን ተግባር ለመፈጸም "ደግሞ"፣ በሚከተለው ዓይነት ሊገባ ይችላል።

(32)... ግን ልቧ ፈቃደኛ ባይሆንም በደረገኩት የጭካኔ ተግባር በመፍራት ነበር የተከተለችኝ። ደግሞ እውነቷን ነው። እንዴት ከእቦቷ ገዳይ ጋር ትስማማለች ብለህ?... (002/31)

"ደግሞ"፣ በሁለቱ እረፍተ ንግግሮች መከከል በሁለተኛው በተከታዩ ዐረፍተንግግር መነሻ ላይ ነው የገባው። በዚህ አገባቡም የሚያመለከተው ንጽጽርን ነው። ንጽጽሩም በተራኪው "የጭካኔ ተግባር"ና "እሷ ባሰየችው ፈቃደኛ አለመሆን" መከከል ያለው ነው። ንጽጽሩንም የሚያደርገው ራሱ ተራኪው ነው። የራሱን ተግባር ከሷ ተግባር ጋር በማነፃፀር የእሷን "እውነትነት" ለመቀበል ሲሞክር ነው የሚታየው። ስለዚህ "ደግሞ" በእንዲህ ዓይነቱም አገባቡ የንጽጽሩን ዝምድና ያመለከታል። በተጨማሪም የንግግሩን እጽንእታዊነት ያሰያል።

"ደግሞ" ከላይ በ(31)ና በ(32) ምሳሌዎች ውስጥ በገባበት ዓይነት በውሁድ-እሀድ ውስጥ በመግበት የንጽጽርን ዝምድና ያመለከታል። ይህ ዝምድና ደግሞ ጋሰር (1984) ከደረሱበት ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል (ለዝርዝሩ ጋሰር 1984: 96-97 ይመለከቷል)።

4.2.6.2. ሰበባዊ ዝምድና፣

ሰበባዊ ዝምድና በተለያየ ቦታ ለምክንያት ዝምድና የተሰጠው ዓይነት ዝምድና ሆኖ ከምክንያት ሰፋ ያለ የዝምድና ዓይነት ነው። በጥቅሉ ሲታይ ግን የሰበብና የውጤት ዝምድና የሚገለጽበት ነው (ሀሊዴይና ሀሰን፣ 1976 ንና ናታል፣ 1982ን ያገናዝቢል)።

"ደግሞ" ይህን ሰበባዊ ዝምድና ይፋ እንደሚያደርግ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሰያሉ። ይህም ሲሆን የሚታየው የቀደመ እውነታን መሠረት በማድረግ ከተለመደው፣ ምክንያት + ውጤት ሂደት ለየት ብሎ በሚቀናጅ ውጤት + ምክንያት የመረጃ መዋቅር ውስጥ ነው። ቀጥለን ምሳሌውን እንመልከት።

(33)... ስለዚህ ይህን የምንገልጸውን ነገር ሰዎች ሊረዱልን የሚችሉት ደግሞ በግልጽና ቀለል በሆነ መንገድ ሲቀርብላቸው ነው።... (015/31)

ከላይ በምሳሌው (33) እንደተገለጸው ከ"ደግሞ" በፊት ያለው ሀሳብ ከ"ደግሞ" በኋላ የመጣው ሀሳብ ውጤት ነው። ይህ ዓይነቱ አቀነጃጀት አጽንኦትንም ጭምር ያሳያል። ከ"ደግሞ" በኋላ አጭር ተግታ አለ። የድምፅ ቅላጼም ለውጥ ይታያል። የመጀመሪያው የሁለተኛው ውጤት ለመሆኑ ማረጋገጫ ሊሆን የሚችለው የዐረፍተ ንግግሩን መዋቅር መለወጥ ነው። ለምሳሌ፣ "ስለዚህ ግልጽና ቀለል በሆነ መንገድ ሲቀርብ ሰዎች የሚገለጸውን ነገር ሊረዱ ይችላሉ" ማለት ይቻላል። ያቀራረቡ መንገድ ግልጽና ቀለል መሆን ለመረዳቱ አስፈላጊ ነው ማለት ነው። በተጨማሪ "ደግሞ" በተለመደው የምክንያት ውጤት አወቃቀርም እየገባ ሰበባዊ ዝምድናን ያመለክታል። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

(34)... አባቴ ከሥራው በጡረታ ተገልሏል። ከተወለድኩ ልጆች ማንም ሥራ የያዘ አልነበረም፤ የቤተሰባችንም ሁኔታ ከመከከለኛ ኑሮ ወደ ድህነት እመራ፤ ይህ ደግሞ እኔን የበለጠ በትምህርቴ እንድተጋና ትልቅ ደረጃ እንድደርስ ይገፋፋኝ ጀመር።... (017/32)

"ደግሞ"፣ በ(34) ውስጥ ያለው አገባብ ከሁለተኛው ዐረፍተ ንግግር ጭብጥ ቀጥሎ ነው። ስለዚህ በጭብጥ መዋቅር ውስጥ "ደግሞ" በእንዲህ ዓይነቱ አገባብ ሲመጣ ጭብጡን እንደሚያመለክት ያሳያል። ከዚሁ ጋር አብሮ ይኸው ዲስኩር አመልካች ጭብጣዊነትንና አጽንኦታዊነትንም ያመለክታል። በዚህ አገባቡም ያለው አገልግሎት ከላይ እንደተገለጸው ሰበባዊ ነው። በመጀመሪያው አረፍተንግግር የተጠቀሱት በሙሉ ከ"ደግሞ" በኋላ ለመጣው አዲስ ሀሳብ ምክንያት ናቸው። ይህንንም ዝምድና ግልጽ ያደረገው፣ በሁለተኛው-ከውጤቱ -ዐረፍተ ንግግር ጭብጥ ቀጥሎ የገባው "ደግሞ" ነው።

"ደግሞ" በ(33) ና በ(34) ምሳሌዎች ዓይነት እየገባ የሰበብና የውጤት ዝምድናን ያመለክታል ማለት ይቻላል።

4.2.6.3. ተጨማሪ ሀሳብ፣

የ"ደግሞ" ሦስተኛ ተግባር ሆኖ በመረጃዎቹ ውስጥ የታየው ተጨማሪ መረጃ መሰጠቱን ማመልከት ነው። ቀድሞ በቀረበው መረጃ ላይ አዲስ መረጃ ለማከል ሲፈለግና ዝምድናውም የመጨመር/የማከል/ መሆኑን ለማሳየት "ደግሞ" ይገባል። ምንም እንኳን ቀደምት የሰዋሰው ሊቃውንት ለ"ደግሞ" ና ለመሰሎቹ ተግባር የሰጡት ግለጌ ችግር ያለበት ቢሆንም ይህን የ"ደግሞ" የማከል/የመጨመር/ ዝምድና ሰይገነዘቡት የቀሩ አይመስሉም፤ ምክንያቱም የሰጧቸው ምሳሌዎች ፍጥር ዐረፍተነገሮች ቢሆኑም የሚታየው ዝምድና ይኸው የመጨመር ዝምድና ስለሆነ ነው።

ለዚህ ጥናትም በተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ "ደግሞ" በገባበት ዐውድ ይህንኑ የማከል ዝምድና ሲያሳይ ቀጥለን እንመልከት።

(35)... እናቱ ወ/ሮ ተመቸሽ ቦጋለ በእራት ዓመቱ፣ አባቱ ደግሞ ከስድስተኛ ወደ ሰባተኛው ክፍል በተዘዋወረበት ወቅት አባቱ ለጤፍ አጨዳ ቆለ ወርደው እዚያው ንዳድ መቷቸው መጡ። ዘመዶቻቸው በየሀኪም ቤቱ ይዘዋቸው ቢዘዋወሩ ሊተርፉ አልቻሉም። በታመሙ በወራቸው ከዚህ ዓለም ተሰናበቱ።... (008/31)

(36)... ለጥናት የምጠቀምበት ጊዜ አልነበረኝም እናም ወደስምንተኛ ክፍል በሚያረከ ውጤት ሰላልፍ ቀረሁ። ይባስ ብሎ ደግሞ የስምንተኛ ክፍል ትምህርቴን መከታተል ከጀመርኩ ከሁለት ወር በኋላ በከፍተኛ ሁኔታ ታመምኩ።... (018/32)

በምሳሌ (35) እንደታየው የ"ደግሞ" አገባብ የተጨማሪ መረጃን መቅረብ ለማመልከት ነው። በዚህም በመጀመሪያው "ስለእናቱ ሞት ከተናገረ" በኋላ እንደገና የ"አባቱን ታሞ መሞት" ይገልፃል። ስለዚህ አንባቢው "ደግሞ"ን በሚያይበት ጊዜ የቀረ ግን ተመሳሳይነት ወይም ቀጣይነት (ጋሰር 1984) ያለው መረጃ በተጨማሪ እንደሚቀርብ ይረዳል። በ(36)ም የሚታየው ተመሳሳይ ተግባር ነው። ተራኪው "በሚያረከ ውጤት አለማለፉን" ከገለጸ በኋላ ቀጥሎ የሚጠቅሰው በመጀመሪያው ላይ የሚታከል ሌላ አዲስ መረጃ ነው። ስለዚህ ፀሐፊው በዚህ ሁኔታ "ደግሞ"ን ሲጠቀም "ሌላው የቀረ የሚገለጽ ሀሳብ አለ" ማለቱ መሆኑን አንባቢው ይረዳል። በመሆኑም የ"ደግሞ" ተግባር ይህንኑ የማከል ዝምድና ገልጾ ማሳየት ነው።

ከዚህ ሌላ ግን በ(35) ላይ የምንመለከተው አንድ ባህርይ አለው። ይህም ተከታትለው የሚገለጹት መረጃዎች ተመሣሣይ እንቀጽ ከላቸውና ደስኩር እመልከቹ፣ "ደግሞ" በ(35) ዓይነት የሚገባ ከሆነ የመጀመሪያው እረፍተንግግር ግስ ሊገደፍ ይችላል። በምሳሌውም (35) ውስጥ የተገደፈው "ሞቱ" ወይም "ተሰናበቱ" የሚል ግስ መሆኑ አጠራጣሪ አይመስልም።

ከ4.2.6.1.-4.2.6.3. እንደተዘረዘረው "ደግሞ" ሦስት የተለያዩ ተግባራትንና ዝምድናን ሲያመለክት ታይቷል። እነዚህም የንጽጽር፣ የሰበብና የመጨመር ዝምድናዎች ናቸው። "ደግሞ" በመረጃዎች ውስጥ እንደታየው (ከላይ የተጠቀሱትን ምሳሌዎች ጨምሮ) በእንድ ቦታ ብቻ ሲገባ አልታየም። በዐረፍተ ንግግር ውስጥ፣ በዐረፍተ ንግግር መካከል፣ በዐረፍተ ንግግር መነሻ ወይም ከጭብጣዊው አካል ቀጥሎ ወዘተ. ይገባል። በነዚህ ሁሉ ቦታዎች ግን የሚያከናውናቸው ተግባራት ያው ከላይ የተጠቀሱት ናቸው። ይሁን እንጂ ከዐረፍተ ንግግሩ የመጀመሪያ አካል/የግንባር አካል ቀጥሎ ሲገባ ከሌላው ተግባሩ በተጨማሪ በአጽንኦት የገባበትን ዐረፍተንግግር ጭብጥ ያመለክታል።

ከጭብጥ መዋቅር አኳያ "ደግሞ" እንድ ወጥ መገኛ ሥፍራ ያለው አይመስልም። በተመሰሳሰይ አካባቢዎችም በመግባት የተለያዩ ተግባራት ሲፈጽም የሚታይ ይመስላል። ስለዚህ ከተግባራቱ አኳያ በወጥነት ይህንን "ጭው" ይከተላል ማለት እደጋች ነው። ሆኖም ሁሉም የተገኘባቸው ውሁድ-አሀደች የተከተሉት "ጭው" በ"ጭው-1" እና በ"ጭው-3" ሥር የተገለጹትን (ለዝርሩ 2.1.2. ይመልከቱ) መሠረተ ሐሳቦች ይመስላል።

ለማጠቃለል፣ "ደግሞ"፣ በውሁድ-አሀደቹ ውስጥ ያለው ሥርጭት ከተግባሩ አኳያ ቀጥሎ ቀርቧል።

የደስኩር እመልከቹ ሥርጭት ከተግባር አኳያ

ደስኩር	ንጽጽር		ተጨማሪ		ሰበባዊ		ጠቅላላ ድምር	
እመልከቹ	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%
ደግሞ	14	41.18	14	41.18	6	17.64	34	100

4.2.7. የ"የተነሳ"ተግባራት፤

"–የተነሳ" በ4.1.2.7. እንደተገለጸው ከሌሎቹ ተተኪሪ ዲስኩር አመልካቾች የሚለይበት በህርይ አለው። ይህም በዲስኩር አመልካችነት ራሱን ችሎ በውሁድ–አህድ ውስጥ ብቻውን ገብቶ አለመገኘቱ ነው። ከመነሻው የሚገባ ደጋፊ ሐረግ የግድ ይፈልጋል። በመሠረቱ "–የተነሳ" በውስጡ ባሉት መዋቅራዊ አካላት ቅንጅት የተመሠረተ ጥገኛ ዐረፍተነገር ነው። በጥገኛ ዐረፍተነገርነቱም ለይ አዘማጅ ሐረግ ነው (ለዝርዝሩ በዬ 1987 ዓ.ም ይመልቱ)።

በዚህ ጥናት የሚተኮርበት ግን በለው መዋቅራዊም ሆነ ሰዋስዋዊ በህርይና አገልግሎት ሳይሆን በውሁድ–አህድ ውስጥ በለው ተግባራዊ አገልግሎቱ ነው። "–የተነሳ" በእማርኛ ቋንቋ ልማዳዊ ሰዋስው መፃሕፍት ውስጥ በእንድ ዓይነት መልክ በቀጥታ ተጠቅሶ አይገኝም። በእንዳንዶቹ ከቅርጹ አኳያ ምድቡ ከጥገኛ ሐረግ ሆኖ በለው ሰዋስዋዊ ተግባር ደግሞ ስማዊና ቅጽላዊ ጥገኛ ሐረግ እንደሆነ ይጠቅሳል (ይትባረክ ወልደሚካኤል፣ 1966 ዓ.ም.: 114–115 ይመለከቷል)። በተክለማርያም ፋንታዬ ጽሁፍ ውስጥ ደግሞ ይሄው ግለጌና ምዳቤ እንደለ ሆኖ "ከዚህም የተነሳ" የሚለውን መከሰቻውን ብቻ ግን፣ ከወደረኛ መስተፃምራን ዝርዝራቸው ውስጥ አስገብተውት ይገኛል (1957:58)። በእጠቃላይ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በጽሑፍም ሆነ በንግግር ስለለው አገልግሎት የተሰጠ ግለጌ /አስረጂ የለም።

ስለሆነም በዚህ ጥናት ከተሰበሰቡት መረጃዎች አኳያ፣ "–የተነሳ" ያለውን ውሁድ–አህዳዊ ተግባር ለማመልከት ተሞክሯል። በመረጃዎቹም ውስጥ "–የተነሳ" ከየትኛውም የቋንቋ አላባ ጋር ይግባ ያለው ተግባር አንድ ዓይነት ብቻ ነው። ያም የምክንያት/የሰበብ/ ዝምድና ነው። ዝርዝሩ ከዚህ በታች ቀጥሎ ቀርቧል።

ምክንያት፤

"–የተነሳ" በዐረፍተ ንግግር ውስጥ ወይም በዐረፍተ ንግግር መካከል ያለው ተግባር ከሱ በፊት በቀረበውና ቀጥሎ በመጣው የውሁድ–አህድ አካል መካከል ምክንያታዊ ወይም በጥቅሉ ሰበባዊ ዝምድና መኖሩን ለአንባቢ ማወጅ ነው። በተጨማሪም ከሱ በፊት አብሮት ወይም ለብቻው የቀረበው መረጃ ከሱ በኋላ ለተገለጸው መረጃ መከሰት ምክንያት ወይም ሰበብ መሆኑንም ይጠቁማል። ከዚህ አንፃርም የበለጠ ግንኙነቱ ምክንያቱን ወይም ሰበቡን ከሚገልጸው የውሁድ–አህድ አካል ጋር ይመሰላል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(37)... ነገር ግን ትምህርቱን አጥንቶ ለከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል ያለው ፍላጐት ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ ቤተሰቡንና እራሱን ለመርዳት ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በተጨዳኝ ያለፈውን ትምህርት እያጠና ለፈተና በዝግጅት ላይ ይገኛል።... (006/31)

(38)... ትምህርቴም በእርግዝና ምክንያት በመቋረጡ የተነሳ በጣም ስለቆጨኝና የትምህርት ፍቅርም ስላለኝ አሁንም እንደገና 10ኛ ክፍል በመግባት ትምህርቴን መከታተል ጀመርኩ።... (001/32)

በ(37) ና (38) በቀረቡት ምሳሌዎች "-የተነሳ" የገባው በዐረፍተ ንግግር ውስጥ ነው። በዚህ አገባቡም "-የተነሳ" አብሮት በተቀናጀው ሐረግ መረጃ ምክንያትነት ከሱ ቀጥሎ በመጣው ዐረፍተንግግር የተገለጸው ነገር ሊደርስ/ሊሆን መቻሉን ይገልጻል። በሁለቱም ምሳሌዎች ከ"-የተነሳ" ጋር አብረው የገቡትም የውሁድ-አሀድ አለባዎች በይዘታቸው የተለያዩ ቢሆኑም በአወቃቀራቸው ተመሳሳይነት አላቸው። ሁለቱም "ከ-"/"በ-" ያለባቸው መስተዋድዳዊ ሐረጋት* ናቸው። ስለዚህ በመረጃዎቹ መሠረት "-የተነሳ" በዐረፍተንግግር ውስጥ ሲገኝና የምክንያት ዝምድናን ሲያመለክት "በ-" ወይም "ከ-" ያለባቸው መስተዋድዳዊ ሐረጐች አብረውት ይገባሉ። በዚህ ጥናት በታዩት መረጃዎች ውስጥ በዚህ ዓይነት አገባብ የመስተዋድዶቹ ተሰቢ ሆነው የገቡት አከላት አብዛኞቹ በቀደምት የሰዋሰው መጽሀፍት ውስጥ "አርዕስት" ወይም "መ-ስ" ተብለው የሚታወቁት ሰማዊ ዐረፍተነገሮች** ናቸው። ሁለቱ አገባቦች ግን በመስተዋድዱ "ከ-" የተሰቡ አዘማጅ ሐረጐች ናቸው።

"-የተነሳ" በዐረፍተ ንግግር መከከል ሲገባም የሚከተለውን ይመስላል።

(39)... በዚህ ላይ የምናነሳው ቢኖር ት/ቤቱ እሩቅ ስለነበር ተመላልሰን ለመማር አልቻልንም። ከዚህም የተነሳ በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ዘመዶች ስለነበሩኝ ከእነሱ ጋር ሆኜ ስማር ቆይቼ ወደሚቀጥለው ክፍል ተዘወርኩ።... (016/32)

---

* ስለመስተዋድዳዊ ሀረግ ምንነትና ባህሪያት ዝርዝር ገለፃ በዬ 1987 ዓ.ም. ይመለከታል።
** ስለሰማዊ ዐረፍተነገሮች በዬ 1987 ዓ.ም. ይመልከቱ።

ከላይ የቀረበው ምሳሌ (39) እንደሚያሳየው "የተነሳ" የገባው በዐረፍተንግግሮች መካከል በሁለተኛው ዐረፍተ ንግግር መነሻ አካባቢ ነው። በዚህ አገባቡም ተግባሩ ያው ምክንያታዊ ወይም ሰበባዊ ዝምድናን ማመልከት ነው። በዐረፍተንግግር መካከል ሲገባም (ከተሰበሰቡት መረጃዎች አኳያ) አብረውት የሚነገሩት "ከዚህ(ም)" ወይም "በዚህ(ም)" ናቸው። እነዚህም ቢሆኑ በመዋቅራዊ ቅንጅታቸው መሰተዋድዳዊ ሐረጋት ናቸው። በዚህ መሠረት "–የተነሳ" በዐረፍተንግግር መካከል ይገኛል ሲባል "ከዚህ(ም) የተነሳ" ወይም "በዚህም(ም) የተነሳ" ሆኖ ይገባል ማለት ነው።

በሌላ በኩል በተሰጠው ምሳሌ (39)ና በሌሎችም በውሁድ–አህደቹ ውስጥ በተገኙት **ተመሣሣይ አገባቦች አልፎ አልፎ "–ም" ቅጣይ መስተፃምር ሲገባ ይታያል። በዚህ አገባቡ ግን** ከመረጃው ውሱንነት የተነሳ የሚፈጥረው የተለየ ስሜት ወይም ፍቺ ይኑር አይኑር ለማየት **አልተቻለም። ስለዚህ ይህም እንደሌሎቹ ወደፊት መጠናት ያለበት ጉዳይ ነው።**

"–የተነሳ" ምንም እንኳ ጥገኛ ዐረፍተ ነገር ቢሆንም በውሁድ–አህድ ውስጥ፤ በዐረፍተ ንግግር ውስጥም ሆነ መከከል ገብቶ ሲገኝ ተግባሩ የምክንያት ዝምድናን ማመልከት መሆኑ ከላይ ተብራርቷል። ከመረጃዎቻችን አንፃር ከዚህ የተለየ ተግበር ሲፈጸም አልታየም።

በአገባቡም ረገድ በዐረፍተ ንግግር ውስጥ ሲገኝ ከተለያዩ መስተዋድዳዊ ሐረጉች (መስተዋድደቹ "በ–" ወይም "ከ–" መሆን አለበቸው) ጋር ነው። በዐረፍተ ንግግር መከከልም ሲገኝ ከ"ከዚህ(ም)" እና ከ"በዚህ(ም)" ጋር ብቻ ነው የሚገባው። በሁለቱም አገባብ ግንኙነቱ ምክንያት ወይም ሰበብ ከሆነው መረጃ– ሀሳብ–ጋር ነው።

በጭብጥ መዋቅርም አኳያ፤ "የተነሳ" የገባው በዐረፍተ ንግግር ውስጥ ከሆነ በእንቀጹ ውስጥ ይገኛል። በዐረፍተ ንግግሮች መከከል ሲገባ ግን ከሁለተኛው ዐረፍተንግግር ጭብጥ ቀድሞ ይገባል፤ ከመጀመሪያውም ዐረፍተንግግር ጋር ያለውን የምክንያት ዝምድና ይገልጻል። በጭብጥም መዋቅር የሚገኝበት ቦታ የተወሰነ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ "–የተነሳ" በ"ጭው" ውስጥ ከእንቀጹ ወይም ከጭብጣዊው አከል ጋር ይነገራል። በአብዛኛም የሚከተለው "ጭው–1"ን ይመስላል። በዚህ ሁኔታ በ"ጭው–1" የቀረበው መሠረተ ሀሳብና በዲስኩር አመልካቹ የሚተላለፈው መረጃ ተመሰሰይነት አለው ለማለት ይቻላል። በተለይ የ"ከዚህ(ም) የተነሳ" ወይም የ"በዚህ(ም) የተነሳ" አገባብ የጭብጥ መዋቅሩን እከሄድ የ"ጭው–1"ን መሠረተ ሀሳብ እንዲጠበቅ/እንዲከተል/ የሚያደርገው ይመስላል። የምሳሌ (39) "ጭው" እንደሚከተለው በሥዕላዊ መግለጫ ይቀርባል።



ሥዕል 9፣

የምሳሌ 39 ጭብጣዊ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ

4.2.8. የ"ወይም" ተግባር (ወይ፣ ወይም፣ ወይስ)፣

"ወይም" በሦስቱ ዓይነት ቅርጾቹ (ወይ፣ ወይም፣ ወይስ) በተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ በተለያዩ ቦታ ገብቶ ተገኝቷል። ሆኖም በ4.1.2.8. እንደተጠቀሰው መሠረታዊው ቅርጽ የትኛው እንደሆነ የታወቀ ነገር ባለመኖሩ ለዚህ ጥናት እንደመሠረታዊ ቅርጽ የተወሰደው "ወይም" የሚለው ቅርጽ ነው።

"ወይም" በቀደምት የሰዋስው ሊቃውንት ዘንድ "አማራጭ መስተፃምር" ከሚባሉት የወደረኛ መስተፃምር ዓይነቶች አንዱ ነው። ለ"አማራጭ መስተፃምር" ከተሰጡት ግለጫዎች ውስጥ "በአንድ ነገርና በአንዳች ነገር መካከል የማማረጥ ወይም የማወላወል አኳኋን በተገለጠ ጊዜ መስተፃምሩ አማራጭ ወይም አወላዋይ ይባላል" የሚለው አንዱ ነው (መርስዔሀዘን ወልደቂርቆስ፣ 1948 ዓ.ም.: 147)። በተመሳሳይ ሁኔታም ይትባረክ ወልደሚካኤል፣ "አንድ ነገር ከሌላው ነገር መመረጡን ያመለክታል" በማለት ይገልጹታል (1966 ዓ.ም.: 107)።

እስካሁን ከተዘረዘሩት ደስኩር አመልካቾች ውስጥ በቀደምት የሰዋስው ሊቃውንት በተሸለ ሁኔታ የተገለጸ ቢኖር "ወይም" ነው ማለት ይቻላል። ይህ ማለት ግን በተሰጠው ግለጫ ውሁድ-አሀድን በተለይ፣ ደስኩርን ደግሞ በጥቅል፣ መሠረት ያደረገ ነው ማለት አይደለም። ከሰዋስዋዊ አመለካከት አንፃር የተሰጠ ፍቺ ነው ማለት ይቻላል።

በዚህ ጥናት ውስጥ በተሰበሰቡት መረጃዎች "ወይም" በሦስቱም ቅርጾች ከገባባቸው ውሁድ-አሀዳዊ ዐውዶች አኳያ ተግባሩን ለማሰየት ተሞክሯል። "ወይም" በሁሉም አገባቡ ያለው ተግባር (አገባቡና ቅርጹ ቢለያይም) አንድ ብቻ ነው። ያም አማራጭን በማመልከት መረጃ መጪመር /ማከል/ ነው። ዝርዝር ትንታኔው ቀጥሎ ቀርቧል።

እማራጭ፤

"እማራጭ"ን የሚያመለክተው ቃል ብዙውን ጊዜ የሚታየው በሰዋሰው ውስጥ ነው። ነገር ግን በውሁድ-አሀድ ውስጥ እንደሚታየው አገባቡ ዐረፍተነገር ውስጥ ባሉ አካላት መካከል ብቻ የተወሰነ አይደለም። ስለዚህ በውሁድ-አሀድ ውስጥ ያለውንም ተግባር ለይቶ ማወቁ ተገቢ ይሆናል (ሃሊዴይና ሀሰን፣ 1976ን ያገናዝቧል)።

"ወይም"፣ በመረጃዎቻችን መሠረት መጠነኛ የስሜትና የእጠቃቀም ልዩነት ባለው ሁኔታ በሦስቱም ቅርጸች የእማራጭ ዝምድና ሲያመለክት ተገኝቷል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንውሰድ።

(40)... እንድ ሰው ችግር የሚያጋጥመው ወይም የሚደርስበት በአጋጣሚ እንጂ ሆን ብሎ እሱ የሚያመጣው ወይም ገና ሲወለድ ችግሩ እሱን ብቻ የሚመለከት ሆኖ አይከሰትም።... (009/31)

(41)... እንድ እሣ አጥማጅ ነበር። ከዕለታት እንድ ቀን በእንዲት የሴት ልጅ ፍቅር ይያዘል ወይም ይጠመዳል።... (010/31)

(42)... ነፍስ ማወቅ ወይም ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን ማገናዘብ ስጀምር አበቴ የቄስ ወይም የቶሎ ትምህርት እንድማር የቶሎ ትምህርት ከሚያስተምሩት መምህር ወሰደኝ።... (005/32)

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች (40፣ 41ና 42) እንደሚታየው በሁሉም ቦታ የገባው "ወይም" ነው። በሁሉም ቦታ ያለውም አገልግሎት መጀመሪያ ቀድመው ለተጠቀሱት ነገሮች እማራጭ መኖሩን ማመልከት ነው። በሦስቱም ቦታዎች የገባባቸው የቋንቋ ዐውዶች ግን ይለያያሉ። በ(40) በእዘማጅ ሀረጉች መካከል፣ በ(41) በሚያስሩ ግሶች መካከል፣ በ(42) ደግሞ በስሞችና በእጉላማሾች- ቅጽላዊ ሐረጉች-መካከል ገብቶ ይገኛል። ይሁንና በሁለቱም ቦታ ያለው ተግባር ተመሳሳይ ነው። በእማራጭነቱም የሚያመለክተው አካል የቀደመውን የዐረፍተነገር አካል በተማሣሣይ የሚተካ ወይም የሚለውጥ እንጂ ከመጀመሪያው ጋር ትይዩ ሆኖ በተለየ እቅጣጫ የሚቀርብ አካል አይደለም።

ለምሳሌ ከላይ በመረጃዎቹ እንደታየው በእዘማጅ ሐረጉች መካከል ሲገባ የእዘማጅ ሐረጉቹ (ምሳሌ 40) መሪ አንድ (ችግር) ነው። በሚያስሩ ግሶች መካከል ሲገባ (ምሳሌ 41) የግሶች ሰዋስዋዊ ባለቤት አንድ ከመሆኑም በላይ በዐረፍተነገሩም ውስጥ ያሉት የዐረፍተነገሩ አካላት፣ ግሶቹ ቢለዋወለጡም ሰዋስዋዊ ተግባራቸው ለሁለቱም ያው ነው። በቅጽላዊ ሐረጉችም አካላት፣ ግሶቹ ቢለዋወለጡም ሰዋስዋዊ ተግባራቸው ለሁለቱም ያው ነው። በቅጽላዊ ሐረጉችም መካከል ሲገባ (ምሳሌ 42) መሪው ለሁለቱም ያው "ትምህርት" የሚለው ቃል ነው። ስለዚህ "ወይም" በሚገባበት ቦታ ሁሉ እማራጭን ቢያመለክትም እማራጩ ቀድሞ ከተገለጸው በትይዩነት

የቀረበ ሰይሆን በቀዳሚው መልክ/አቅጣጫ ሊቀጥል የሚችል አማራጭ ነው። በተጨማሪም ቀዳሚውም ሆነ አማራጩ በጥርጣሬ መንፈስ የቀረበ ሰይሆን በእርግጠኝነት የሚቀርብ አማራጭ ነው።

ይህ ሁኔታ ጋሰር (1984) "-ም" ቅጣይ መስተፃምር በገባበት ቦታ ሁሉ በመረጃ አቀራረብ ረገድ የቀጣይነትን (continuity) ባህርይ ያሰያል ካሉት ጋር የሚስማማ ይመስላል። ምክንያቱም በመረጃዎቻችን ውስጥ እንደታየው የ"ወይስ" (መረጃው ከ"ወይም" ቀጥሎ ቀርቧል) አገባብና ስሜት ከ"ወይም" የተለየ ነው። ምናልባት ልዩነቱ የመጣው በመድረሻቸው ላይ ባሉት "-ም" ወይም "-ስ" ሊሆን ይችላል የሚል ግምት በአጥኚው ዘንድ አለ። በመሆኑም በ"-ም" የቀጣይነት ባህሪይ ተጽዕኖ የ"ወይም" አገባብና አማራጭ መረጃን ቀጣይ የማድረግ ባህሪይ ሊከሰት እንደቻለ የምንስማማ ከሆነ የ"ወይም" መሠረታዊ ቅርጽ "ወይ" ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

> (43)... እናም ቦታ ስትመርጥ ከዋለች በኋላ ግታ መኝታ ላይ እንዳሉ ለመንገር ቁርጥ ሀሳብ ወሰና ለመንገር ወሰነች። ግን ምን ይለኝ? ውጭ ይለኝ ወይስ ሊገለኝ? እያለች ስታስብ ከቆየች በኋላ... (018/31)

የ"ወይስ"ን አገባብ ከ(43) እንደምንመለከተው በጥያቄዎች መካከል ነው-ማለትም በጥያቄያዊ ቅለጄ ከቀረቡት ከሚያሰሩ ግሶች መካከል ነው የገባው። ጥያቄዎቹ ግን ምላሽ የሚሹ ሰይሆኑ ለራስ የቀረቡ የስጋት ጥያቄዎች ናቸው። ከዚህ አገባቡም አንባቢ የሚረዳው ከስጋትና ከጥርጣሬ የመነጨ አማራጭ ሊኖር እንደሚችል ነው። በዚህ መልክ የሚቀርበውም አማራጭ መጀመሪያ የቀረበውን የሚተካ ወይም በዚያው መልክ የሚቀጥል (ከላይ በ"ወይም" አገባብ እንደታየው) አይደለም። የመጀመሪያው አማራጭ መረጃ ራሱን ችሎ የሚቀርብ ሲሆን ቀጥሎ የሚቀርበውም አማራጭ በመጀመሪያው ትይዩ ራሱን ችሎ የሚገለጽ ነው። እንዱ እንዱን በሁሉም ረገድ የሚተካው ወይም የሚለውጠው ሆኖ አልቀረበበትም።

በእርግጥ ከቀረበው ምሰሌ አንፃር የሁለቱ አማራጭ አካላት ግሶች ሰዋሰዋዊ ባለቤት አንድ ነው። ሁሌም አንድ ነው ማለት ግን ለጊዜው አደጋች ነው። ነገር ግን አማራጮቹ መነሾዋቸው አንድ ሆኖ የማይገናኙ ናቸው። ከዚህ ሌላ ግን "ወይስ" በተጨማሪ አማራጭ እርግጠኛ ያልሆነና ቁርጡ ያልታወቀ ሥጋትና ጥርጣሬ የተላበሰ መሆኑንም ያመለክታል። እዚህ ላይ ለ"ወይም" የተነሰው ጥያቄ ለ"ወይስ"ም ይነሰል። በ"ወይስ" የቀረበው አማራጭ መረጃ የቀደመውን መረጃ አለመተካት ወይም በትይዩነት በተለየ መልኩ መቀጠል የመነጨው በ"ወይስ" ላይ ከለው ከ"-ስ" የኢቀጣይነት (discontinuity) ባህርይ ይመስላል (ጋሰር፤ 1984ን ይመለከቷል)። ይህንንም እንደ "ወይም" የምንቀበል ከሆነ መሠረታዊው ቃል ወይም ደስኩር አመልካች "ወይ" ነው፤ ሌሎቹ

የ"ወይ" የተለያዩ ቅርጾች ናቸው ማለት ይቻላል። ይሁንና ይህ ጉዳይ በተጨማሪ መረጃዎች ተፈትሾ መረጋገጥ የሚሻ ጉዳይ ነው።

ከ"ወይም" ወይም ከ"ወይስ" በተለየ በውሁድ-አሀዶች ውስጥ ሲገባ የታየው "ወይ" ነው። በጠቅላላ ከተሰበሰቡት መረጃዎቻችን አኳያ "ወይ" ብቻውን የታየባቸው አጋጣሚዎች በአንድ ውሁድ-አሀድ ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። እነርሱም ቀጥለው ቀርበዋል።

(44)... እንደንዱ ወይ እናቴ ሌላ ናት ወይ አባቴ ሌላ ነው ግን ከሁለቱ አንዱ ወላጆቼ አይደሉም ይላል።...

(45)... እንደንዱም የጉዲፈቻ ልጅ ሆኜ መሆን አለበት፣ እናም ወይ አባቴ የተባለው ሰው ወይ እናቴ የተባለች ሴትዮ ተረክበውኝ ይሆናል።... (012/31)

ከላይ በ(44)ና በ(45) የቀረቡት መረጃዎች ከአንድ ውሁድ-አሀድ ከተመሰሰይ ቦታ የተወሰዱ ናቸው። በሁለቱም አገባቦች መከከል የአጠቃቀም ልዩነት አይታይም። ተግባራቸውም ማማረጥ ነው። አማራጩ ግን በ"ወይም" ከቀረበው ይልቅ በ"ወይስ" ከቀረበው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ይመስላል። የሁለቱም አማራጭ ጥርጣሬን የተላበሰ ነው። እርግጠኛ ያልሆነ ጉዳይ/ነገር የሚማረጥበት ሁኔታ ይታያል። ከ"ወይስ" የሚለየው፣ "ወይስ" ከግስ መከከል ብቻ ሲገኝ "ወይ" ግን በዐረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ይገኛል። በተጨማሪም ከምሳሌው አኳያ ከታዩ በአንድ አጋጣሚ "ወይ" የመጀመሪያው ዐረፍተነገር ግስ የማስገደፍ ባህርይም ይታይበታል። ይህ ግን የሚሆነው የሁለቱም አማራጮች ግሶች አንድ የሆኑ እንደሆነ ብቻ ይመስላል። "ወይ" በዐረፍተ ንግግር መነሻ ይገባል ሲባልም ቀድመውት ሊመጡ የሚችሉ ቃላት/ሐረጋት (ለምሳሌ በ(44) "እንደንዱ"፣ በ(45) ዲስኩር አመልካቹ "እናም") እንዳሉ ምሳሌዎቹ ያስረዳሉ።

"ወይም" በሦስቱም መልኩ በውሁድ-አሀድ ውስጥ የተለያዩ ዐውዶች ውስጥ ሲገባ ተግባሩ አማራጭን ማመልከት መሆኑ ከላይ ተገልጿል፤ ሆኖም በዲስኩር አመልካቹ ቅርጽ መለዋወጥ የተነሳ፣ የአማራጩ አቀራረብ ልዩነት የሚታይበት ይመስላል። "ወይም" የሚገባው በእርግጠኝነት የቀረቡ አማራጮችን ለማመልከት ነው፤ ስለሆነም እንበቢ "ወይም"ን በውሁድ-አሀድ ውስጥ በዚህ ዓይነት ገብቶ ሲያገኘው በውሁድ-አሀዱ አላባዎች መከከል ያለው ዝምድና የአማራጭ ዝምድና መሆኑን ከመገንዘቡም በላይ የተገለጸውም አማራጭ በእርግጠኝነት ስሜት የቀረበ መሆኑንም ይረዳል።

በሌላ በኩል ደግሞ "ወይስ"ና "ወይ" በሚገቡበት ጊዜ ደግሞ አንበቢው የሚረዳው የማማረጥ ነገር መኖሩንና የሚቀርበውም አማራጭ ያልተረጋገጠ ስጋትና/ወይም ጥርጣሬን ያዘለ መሆኑን ነው። በ"ወይስ"ና በ"ወይ" መከከል ያለው ልዩነት የአጠቃቀም ልዩነት ብቻ ነው።

በዚህ ንዑስ ክፍል እንደታየው የ"ወይም" ና የ"ወይስ" ልዩነት የተከሰተው በሁለቱ መድረሻዎች ላይ ባሉት "-ም"ና "-ስ" አማካይነት ይመስላል። ይህም ጋሰር (1984) የ"-ም"ና የ"-ስ"ን አገባብና አገልግሎት አጥንተው ከገኙት የ"-ም" ቀጣይነትና የ"-ስ" ኢቀጣይነት ባህርይ ጋር የሚስማማ ይመስላል፤ ሆኖም በበቂ መረጃ የበለጠ መረጋገጥ ስለሚገባው ሌላ ጥናት የሚጋብዝ ጉዳይ ነው።

"ወይም"፤ "ወይስ"ና "ወይ" በጭብጥ መዋቅር ውስጥ ከዚህኛው አካል ጋር የጠበቀ ግንኙነትና ይህ አገልግሎት አላቸው ለማለት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም የሚገቡበት ቦታ ውሱን አይደለም፤ የሚሰጡትም ስሜት ይለያያል። በጥቅሉ ማለት የሚቻለው በመረጃዎቹ ውስጥ በታየው መሠረት በጭብጥ መዋቅሩ ውስጥ፤ በጭብጡም ይሁን በአንቀጹ ውስጥ ባሉ አካላት መካከል በመግበት አማራጭ ዝምድናን ያመለክታሉ የሚለውን ነው።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና ጠቋሚ አስተያየት

5.1. ማጠቃለያ

ጥናቱ እንዲካሄድ ያነሳሱት መሠረታዊ ጉዳዮች፣ በ1.2. እንደተጠቀሰው በተማሪዎች ድርሰቶች ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች፣ ተማሪዎቹ አያየኦችን–መስተፃምራንን–በትክክልና በተገቢ ቦታቸው አለመጠቀማቸው ግጥምጥም የሆነ ጽሁፍ ለመጻፍ እንደ አንድ ችግር መጠቀሱ፣ ቃላዊ/ሐረጋዊ መስተፃምራንን–ዲስኩር አመልካቾችን–በተመለከተ ከልማዳዊ የሰዋሰው መፃህፍት ግለፄዎች ውጪ የተደረጉ ጥናቶች አለመኖራቸው ወይም ጪርሰ አለመጠናታቸውና የመሰሰሉት ችግሮች ነበሩ።

ከዚህ በመነሳት ለችግሩ መፍትሔ መስጠት የሚቻለው ችግሩ ራሱ በተገቢው መንገድ ሲጠና መሆኑን በማመን ይህ የዲስኩር አመልካቾች ትንተና ተደርጊል። ሆኖም በአግርኛ ቋንቋ ጽሁፍ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉትን ዲስኩር አመልካቾች (መስተፃምራዊ ቃላትንና ሐረጉችን) በሙሉ በአንድ ጊዜ ማጥናት በለመቻሉ ጥናቱ የሚመለከታቸው ዲስኩር አመልካቾች በ3.2.4.1. የተገለጹት ብቻ ናቸው።

የጥናቱም ዓለማ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ የዲፕሎማ መርሐግብር የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በጻፏቸው ሁለት ተራኪ ውሁድ–አሀደች ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተደጋግመው የገቡትን ዲስኩር አመልካቾች ውሁድ–አሀዳዊ ሥርጭትና ተግበር መተንተን፣ በመጪ ረሽም የበኩሉን ጠቋሚ አስተያየት መሰንዘር ነበር። ከዚህ ዐቢይ ዓለማም በመነሳት፣ ጥናቱ በሂደት ይመልሰቸዋል የተባሉት ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፤

1ኛ. በተማሪዎቹ ተራኪ ውሁድ–አሀደች ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተደጋግመው የገቡት ቃላዊና ሐረጋዊ ዲስኩር አመልካቾች የትኞቹ ናቸው? ሥርጭታቸውና አጠቃቀማቸውስ እንዴት ነው?

2ኛ. በልማዳዊ የሰዋሰው መፃሕፍት ውስጥ ከተጠቀሰው፣ "ቃለትንና ሐረጋትን፣ ዐረፍተ ነገሮችንና ዐረፍተ ነገሮችን... ከማያያዝ" የተለየ ምን ዓይነት ተግበር አለቸው? የተለየ ተግበርስ ከለቸው ምን ምን ናቸው?

3ኛ. በተማሪዎቹ ውሁድ-አሀደች ውስጥ ተደጋግመው በገቡት ዲስኩር አመልካቾች የተገለጹት ተግባራት በተወሰኑ ምድቦች ሊከተቱ ይችላሉ?

በጥናቱ ሂደት እነዚህን ጥያቄዎች በመመለስ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት፣ ከተማሪዎቹ በተሰበሰቡት 38 ተራኪ ውሁድ-አሀደች መረጃነት ዲስኩር አመልካቾቹ ተተንትነዋል። በትንተናውም ውጤት መሠረት ጥያቄዎቹን በሚከተለው አኳኋን ለመመለስ ተሞክሯል።

5.1.1. <u>የዲስኩር አመልካቾች መጠንና ድግግሞሽ</u>

በተሰበሰቡት 38 ተራኩ ውሁድ-አሀደች ውስጥ የዲስኩር አመልካቾች በጠቅላላው 498 ጊዜ ገብተው ተገኝተዋል። እነዚህም 261 ጊዜ በውሁድ-አሀድ አንድ፣ 237 ጊዜ ደግሞ በውሁድ-አሀድ ሁለት ውስጥ የገቡናቸው (ለዝርዝሩ አባሪ <u>ሀ-1</u> ይመልከቱ)።

ከእነዚህ ውስጥ በ3.2.4.1. በተገለጸው መሠረት ተመርጠው ጥናቱ የተመለከታቸው ዲስኩር አመልካቾች በሁለቱም ውሁድ-አሀደች ውስጥ የሚገኙት፣ (ነገር) ግን፣ (እ)ና፣ (ይሁን) እንጂ፣ ስለዚህ(ም)፣ ከዚያ(-)፣ ደግሞ፣ -የተነሰ እና ወይ(ም/ስ) ናቸው። እነዚህም ከፍተኛ ሥርጭት ያላቸው ዲስኩር አመልካቾች መሆናቸውን ጥናቱ ያመለከታል (አባሪ <u>ሀ-2</u> ይመለከቷል)። ከጠቅላላውም የዲስኩር አመልካቾች በውሁድ-አሀድ አንድ 211፣ በውሁድ-አሀድ ሁለት 180-በድምሩ 391 የሚሆነውን የድግግሞሽ መጠን ሸፍነዋል።

ስምንቱ ዲስኩር አመልካቾች እርስ በርሳቸው ሲነፃፀሩ፣ ምንም እንኳ በሁለቱም ውሁድ-አሀደች ውስጥ ከፍተኛ ሥርጭት ያላቸው ቢሆኑም የሥርጭት ልዩነትና ተማሣሣይነት እንደሚታይባቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል በ4.1.1.1. ና በ4.1.1.2 በተጠቀሰው መሠረት መከከለኛ ሥርጭት ያላቸው ዲስኩር አመልካቾች (እንጂ፣ ደግሞ፣ ስለዚህ፣ ወይ(ም/ስ)...) በሁለቱም ውሁድ-አሀደች ውስጥ የጐላ የሥርጭት ልዩነት አለማሳየታቸውን (ው.አ.1 - χ^2 =0.96፣ P>.05፤ ው.አ.2-χ^2=0.24፣ P>.05) የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

በጣም ከፍተኛ ሥርጭት ያላቸውም "(እ)ና" ና "(ነገር)ግን"፣ በውሁድ-አሀድ አንድ ውስጥ የጐላ የሥርጭት ልዩነት ባይታይባቸውም (χ^2=0.36፣ P>.05)፣ በውሁድ-አሀድ ሁለት ውስጥ ግን የጐላ የሥርጭት ልዩነት እንዳላቸው (χ^2=8.24፣ P<.05) ጥናቱ አመልክቷል። (ለዝርዝሩ "ሠንጠረዥ 3"ንና "ሠንጠረዥ 6"ን ይመለከቷል)።

እነዚህ ስምንት ዲስኩር አመልካቾች በ4.1.1.3. እንደተገለጸው፣ በሁለቱም ውሁድ-አሀደች ውስጥ በጠቅላላ ያላቸው ሥርጭት ሲነፃፀር በP<.05 የጉልህነት ደረጃ ከፍተኛ የሥርጭት ልዩነት ታይቷል። በተጨማሪም እነዚሁ ዲስኩር አመልካቾች በላቸው የሥርጭት ደረጃ ቅደም ተከተል መሠረት ሲነፃፀሩ የተገኘው ውጤት (ρ=.55፣ P>.05) በተቀራራቢ መጠን በሁለቱም ውሁድ-አሀደች ውስጥ መሠራጨታቸውን ያረጋግጣል። (ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ 8ን ይመለከቷል)። በአጠቃላይ ስምንቱ ዲስኩር አመልካቾች በሥርጭታቸው መሠረት በደረጃ ተቀዳድሞ ቢቀመጡ፣ "(ነገር)ግን"፣ "(እ)ና"፣ "ከዚያ(-)"፣ "ደግሞ"፣ "(ይሁን) እንጂ"፣ "ስለዚህ"፣ "ወይ(ም/ስ)" እና "-የተነሳ" ይሆናሉ።

ስምንቱ ዲስኩር አመልካቾች ከመጠን ሥርጭታቸው በተጨማሪ ያላቸው አገባባዊ ሥርጭት የሚከተለውን እንደሚመስል በጥናቱ ተመልክቷል።

-(ነገር)ግን:-"ግን"ም ሆነ "ነገር ግን" በዐረፍተንግግር መካከል ከተከታዩ ዐረፍተንግግር መነሸ ላይ ይገባሉ። በጽሁፍ መክፈቻ ዐረፍተንግግር መነሸና ተከታይ ዐረፍተንግግር በሌለበት ሁኔታ በዐረፍተ ንግግር መድረሻ ላይም አይገቡም። "ግን" ብቻውን ደግሞ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ከጊዜ-ጠቀስ ቃላት/ሐረጋት፣ ከስም፣ ከተውላጠ ስም፣ ከጥገኛ ዐረፍተ ነገሮች፣ ከአዘማጅ ሐረጎች፣ ከዲስኩር አመልካቾች፣ ከመስተዋድዳዊ ሐረጎች ቀጥሎ እንደሚገባ ጥናቱ አሳይቷል። (ለዝርዝሩ 4.1.2.1.3 ይመለከቷል)።

-(እ)ና:-በዐረፍተ ንግግር መካከል፣ በሁለተኛው ዐረፍተንግግር መነሸ ላይ ወይም በመጀመሪያው ዐረፍተንግግር መድረሻ ላይ ይገባል። በዐረፍተነገርም ውስጥ፣ ከጥገኛ ዐረፍተነገር፣ ከአዘማጅ ሐረግ፣ ከመስተዋድዳዊ ሐረግ ቀጥሎ ይገባል። በዐረፍተ ነገር መነሸ ላይ ሲገባ ባይታይም፣ በመድረሻ ላይ ግን እንደሚገባ ጥናቱ ያመለክታል። (ለዝርዝሩ 4.1.2.2.3 ይመለከቷል)።

-(ይሁን) እንጂ:- "ይሁን እንጂ"፣ በጠቅላላ የገባው፣ በዐረፍተንግግሮች መካከል በሁለተኛው ዐረፍተንግግር መነሸ ላይ ብቻ ነው። ከዚህ በስተቀር በሌሎች ቦታዎች ሲገባ አልተገኘም። "እንጂ"፣ ብቻውን ደግሞ እንደ "ይሁን እንጂ"፣ በዐረፍተንግግሮች መካከልና በዐረፍተ ንግግሮች ውስጥ ይገባል። በዐረፍተንግግር ውስጥ ሲገባ፣ ከስማዊ ሐረጎች፣ ከጥገኛ ዐረፍተ ነገሮች፣ ከአዘማጅ ሐረጎች ቀጥሎ ይገባል። (ዝርዝሩን ከ4.1.2.3. ይመልከቱ)።

-ስለዚህ(ም):-ይህ ዲስኩር አመልካች ብቻውንም ሆነ "-ም"ን አክሎ፣ በሚገባበት ጊዜ የሚገኘው በዐረፍተንግግሮች መካከል በሁለተኛው ዐረፍተንግግር መነሻ ላይ ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ በሌላ ቦታ ከሌሎች የቋንቋ አሳባዎች ጋር ሲገባ አልታየም። (ዝርዝሩን ከ4.1.2.4. ይመልከቱ)።

-ከዚያ(-):-በዐረፍተንግግሮች መካከል፣ በተከታዩ ዐረፍተንግግር መነሻ ላይ ይገባል። በዐረፍተነገሮችም ውስጥ ከምስርት ስሞች ቀጥሎ/መካከል ይገባል። (ዝርዝሩን ከ4.1.2.5. ይመልከቱ)።

-ደግሞ:-እንደሌሎቹ ዲስኩር አመልካቾች በዐረፍተ ንግግሮች መካከል ይገባል። በዚህ ጊዜ ግን የሚገኘው በሁለት ዓይነት መልክ ነው፤ እንዱ ብቻውን ከተከታዩ ዐረፍተ ንግግር ጭብጥ ቀድሞ፣ ሌላው ደግሞ፣ ከጭብጡ ቃል/ሐረግ (ከስሑ፣ ከመሐ) ቀጥሎ ይገባል። ከዚህ ሌላ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሲገኝ፣ ከስሑ፣ ከመሐ፣ ከጥገኛ ዐረፍተ ነገሮች ከአዘማጅ ሐረጎች፣ ከተውሰከ ግሶች ቀጥሎ ይገባል። (ለዝርዝሩ 4.1.2.6.ን ይመልከቱ)።

--የተነሳ:-በዐረፍተ ንግግሮች መካከል ይገባል። የሚገባውም "በዚህ(ም)" ና "ከዚህ(ም)" ከተባሉት መስተዋድዳዊ ሐረጎች ጋር ነው። በዐረፍተ ነገርም ውስጥ ሲገባ እንደታየው፣ አብረውት የሚገቡት በሙሉ መስተዋድዳዊ ሐረጋት ናቸው። ራሱን ችሎ ለብቻው ግን ሲገባ አልታየም። (ዝርዝሩን ከ4.1.2.7. ይመልከቱ)።

- ወይ(ም/ስ):-ይህ ዲስኩር አመልካች ("ወይ" የሚለውን ቅርጽ ሰይጪምር) በዐረፍተንግግሮች መካከል ይገባል። ብዙ ጊዜ የሚገባው ግን በዐረፍተንግግር ውስጥ ነው። በዐረፍተንግግርም ውስጥ የሚገባው፣ ከስማዊ ሐረጎች፣ ከአዘማጅ ሐረጎች፣ ከመስተዋድዳዊ ሐረጎችና ከቅጽላዊ ሐረጎች መካከል ነው። "ወይ" የሚለው ቅርጽ ደግሞ፣ በዐረፍተ ንግግር መነሻ ላይ ይገባል። (ለዝርዝሩ 4.1.2.8.ን ይመልከቱ)።

5.1.2. የዲስኩር አመልካቾቹ ተግባራት፣

በዚህ ጥናት ከተነሱት መሠረታዊ ጥያቄዎች ሁለተኛው፣ የዲስኩር አመልካቾቹ (መስተፃምራዊ ቃላቱ/ሐረጋቱ) በልማዳዊው ሰዋስው መፃሕፍት ከተጠቀሰው ተግባር በስተቀር ሌላ ተግባር አላቸው? ካሉስ ምን ምን ናቸው? የሚል መሆኑ ከላይ በ1.3. ተገልጿል። በጥናቱም ሂደት ውጤት እንደታየው እነዚህ ዲስኩር አመልካቾች ከቀደምት የሰዋስው ሊቃውንቱ ግለጌ/ አሰሪጅ ውጪ በርከታ ተግባራት አላቸው።

የዲስኩር አመልካቾቹን ተግባር ለመተንተን የተሞከረው፤ በመሪጃ ውሁድ-አሀደቹ ውስጥ፤ የአንዱ ዐረፍተ ንግግር አተረጓጐም ከተከታዩ ዐረፍተንግግር አተረጓጐም ጋር በለው ዝምድና ላይ በመመሥረት ነው። ይህም ዝምድና አንዱ የግጥምጥምነት መለያ ነው። የዲስኩር አመልካቾቹም ተግባር "ግጥምጥምነቱን ከመፍጠር ይልቅ በሁለቱ የውሁድ-አሀድ አካላት መካከል ያለውን ዝምድና ይፋ (explicit) ማድረግ" እንደሆነ በጥናቱ ተመልክቷል። በዚህ ዓይነት የተተነተኑት የስምንቱ ዲስኩር አመልካቾች ተግባራት በሚከተለው አኳኋን ተጠቃለለው ቀርበዋል።

-(ነገር)ግን:-በጥናቱ እንደታየው የ"ልየታ"፤ የ"ንጽጽር"፤ የ"ማረም"፤ የ"ምክንያት"፤ የ"ጊዜ"ና የ"ማከል" ዝምድናዎችን ያመለክታል። (ለዝርዝሩ 4.2.1.1-4.2.1.3. ይመለከቷል)።

-(እ)ና:-የ"(እ)ና" ተግባር፤ የ"ተለጣጥቆ"፤ የ"ምክንያት"፤ በተጨማሪም የ"ልየታ"፤ የ"ማከል" ዝምድናዎችን ማመልከት ነው። የ"(እ)ና"፤ ተግባራት፤ ከገባባቸው መዋቅራዊ አካላት ጋር አብረው የሚለዋወጡ ሆነው ታይተዋል። (ለዝርዝሩ 4.2.2.1.-4.2.2.4. ይመለከቷል)።

-(ይሁን) እንጂ:-የንጽጽርና የልየታ ዝምድናዎችን ያመለክታል። ሁለቱ ቅርጾች (እንጂ፤ ይሁን እንጂ) የሚያመለክቱት የተለያዩ ተግባራትን እንደሆነም ጥናቱ አመልክቷል። በመሆኑም "እንጂ"፤ የ"ንጽጽር"፤ ይሁን እንጂ፤ የ"ልየታ" ዝምድናዎችን ያመለክታሉ። (ዝርዝሩን ከ4.2.3.1-4.2.3.2. ይመልከቱ)።

-ስለዚህ:-በዲስኩር አመልካችነቱ ሲገባ፤ በውሁድ-አሀዱ አካላት መካከል፤ የ"ምክንያት"፤ የ"ማከል"፤ የ"ተለጣጥቆ" ዝምድናዎችን ያመለክታል። (ለዝርዝሩ 4.2.4.1.-4.2.4.2. ይመልከቱ)።

-ከዚያ(-):-በዲስኩር አመልካችነት በውሁድ-አሀድ ውስጥ ሲገባ የሚያመለክተው ዝምድና የተለጣጥቆ ዝምድና ነው። የ"ተለጣጥቆ"ው ዓይነት በ"ከዚያ" ቅርጾች መለዋወጥ (ከዚያ፤ ከዚያ በኋላና ከዚያም) በመጠኑ እንደሚለዋወጥ በጥናቱ ታይቷል። (ዝርዝሩን ከ4.2.5. ይመልከቱ)።

-ደግሞ:-ሦስት ዓይነት ዝምድናዎችን ያመለክታል እነርሱም፤ የ"ንጽጽር"፤ የ"ሰበብ"ና የ"ማከል" ዝምድናዎች ናቸው። (ዝርዝሩን ከ4.2.6.1.-4.2.6.3. ይመልከቱ)።

-<u>የተነሳ</u>:-ራሱን ችሎ ለብቻው የማይገባ ዲስኩር አመልካች ቢሆንም፣ በውሁድ-አሀድ ውስጥ ከተለያዩ መስተዋድዳዊ ሐረጎች ጋር በመግባት የ"ምክንያት" ዝምድናን ብቻ ያመለክታል። (ለዝርዝሩ 4.2.7.ን ይመልከቱ)።

-<u>ወይ(ም/ስ)</u>:-በየትም ቦታ ከማንኛውም የውሁድ-አሀድ አለባ ጋር ሲገባ የሚያመለክተው ዝምድና የ"አማራጭ" ዝምድና ነው። ሆኖም የቅርጸቹ መለዋወጥ (ወይ፣ ወይም፣ ወይስ) አማራጮቹ የቀረቡበትን ባህርይ የመለዋወጥ ሁኔታ ያሳያል። (ለዝርዝሩ 4.2.8.ን ይመልከቱ)

5.1.3. <u>የዲስኩር አመልካቾች ተግባራት ምድቦች አከፋፈል፣</u>

በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው ስምንት ዲስኩር አመልካቾች፣ በውሁድ-አሀድ ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን እንደሚፈጽሙ ወይም የተለያዩ ዝምድናዎችን እንደሚያመለክቱ በጥናቱ ተገልጿል። ዲስኩር አመልካቾቹ ቢለያዩም ተመሣሣይ ዝምድናዎችን ሊያመለክቱ እንደሚችሉ ጥናቱ አሳይቷል። ስለሆነም ዲስኩር አመልካቾቹን በተለያዩ ምድቦች ከመከፋፈል ይልቅ ተግባራቱን መከፋፈልና ዲስኩር አመልካቾቹን እንደተግባራቸው ማመሳከቱ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል።

በጥናቱ የታዩት የዲስኩር አመልካቾቹ ተግባራትም፣ "ንጽጽር"፣ "ልየታ"፣ "ማከል/መጨመር"፣ "ምክንያት/ሰበብ" "ጊዜ/ተለጣጥቆ"፣ "ማረም"ና "አማራጭ" መሆናቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል። በ2.1.3. እንደተመለከተው ደግሞ፣ እነዚህ ተግባራት በተወሰኑ ምድቦች ሊከፋፈሉ የሚችሉበት የጋራ ባህርይ ያለቸው ይመስላል። ለምሳሌ፣ የ"ንጽጽር"፣ የ"ልየታ"ና የ"ማረም" ዝምድናዎች በጋራ የሚያመሳስላቸው ባህርይ፣ ሦስቱም ከ"ግምት ውጪ (beyond expectation) የሚቀርብን ሀሳብ የሚያመለክቱ መሆናቸው ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ፣ በሀሊዴይና ሀሰን (1976) የልየታ ዝምድና (Adversative relation) ሥር ሊጠቃለሉ ይችላሉ። የናታልም (1982) ምድብ "ሲ" የልየታ ዝምድና ከዚህ ጋር ተመሣሣይ ነው። (ለዝርዝሩ አባሪ <u>ሠ-1</u> ና <u>ሠ-2</u> ይመልከቱ)

በዚሁ ዓይነት ሌሎቹም-ማለትም፣ የምክንያት/የሰበብ ዝምድናዎች በሰበባዊ (Causal)፣ የጊዜ/የተለጣጥቆ ዝምድናዎች በጊዜ-ጠቀስ (temporal)፣ እንዲሁም የማከል/የመጨመርና የአማራጭ ዝምድናዎች በእከላ (Additive) ዝምድና ሥር ሊጠቃለሉ ይችላሉ። በመሆኑም የስምንቱ ዲስኩር አመልካቾች ተግባራት በሀሊዴይና ሀሰን (1976) አራት ዋናና ሌሎች ንኡሳን "የመስተፃምራዊ ዝምድናዎች" (conjunctive relations) ምድቦች መሠረት መከፋፈልና መመደብ የሚቻል ይመስላል።

ዋና ምድብ	ንኡስ ምድብ	ደስኩር አመልካቾች
	ንጽጽር	ግን፣ ነገርግን፣ እንጂ፣ ደግሞ
ልየታ	ልየታ	ግን፣ ነገርግን፣ ይሁንእንጂ፣ እናም
	ማረም	ግን፣
	ማከል	ነገርግን፣ (እ)ና፣ ስለዚህ፣ ደግሞ
እከላ		
	አማራጭ	ወይ፣ ወይም፣ ወይስ፣
	ምክንያት	ነገርግን፣ እና፣ እናም፣ ስለዚህ፣ ከ/በዚህ የተነሳ
ሰበባዊ		
	ሰበብ	(እ)ና፣ ደግሞ፣ –የተነሳ፣
	የጊዜ ተለጣጥቆ	ነገርግን፣ ከዚያ፣ ከዚያ በኋላ
ጊዜ–ጠቀስ		
	የድርጊት ተለጣጥቆ	(እ)ና፣ ስለዚህ፣ ከዚያም

